# ጥያቄ እና መልስ
# በዕብራውያን ላይ ክፍል III

... ዛሬ ማታ እንደገና በዚህ ተበርናክል ተገኝተን፡ በነፃነት በተሰጠን በእግዚአብሔር ቃል ዙሪያ በዚህ አስደናቂ ህብረት እና አምልኮ ውስጥ መገኘት ደስታ ነው። የዚህ በረከት ተካፋዮች መሆናችን... ደስ ብሎናል።

554 እናም እግዚአብሔር እንደ ዛሬው ጠዋት መልእክት፡ በዛሬው ምሽትም እንደሚባርከን እተማመንበታለሁ። እና ከጥቂት ጊዜ በፊት፡ ከጎረቤቴ ከወይዘሮ ውድ ጋር፡ እየተነጋገርን ነበር፡ እነ ሚስተር ዉድ እና ሌሎቹ ጋር በመሆን፡ ተነጋግረን ነበር። እናም ያ ወንድም ኔቪል ከሰበካቸው መልካም ስብከቶች ሁሉ የላቀው ስብከት እንደነበረ አምናለሁ፡ እሱ እስካሁን ከሰበከላቸው ሁሉ ለእኔ የሚሻለው ይህ ነበር። ያን ድንቅ ስብከት በእርግጠኛነት አድንቄዋለሁ እናም አመሰግናለሁ። ድፍረት አግኝቼበታለሁ፡ በደንብ አስማምሮኛል። ስለዚህ፡ ለእውነት መገዛት ደስ ይ—ይለኛል። ስለ፡ ስለሚያበረታታው፡ አያችሁ፡ ደፋር እንድትሆኑ የሚያደርግ ክፍሉ፡ እና ዳዊት... በዚያ ሁኔታ ውስጥ ሆኖ፡ ያንን ሁሉ... በዚያ ታላቅ ፈተና ውስጥ ሆኖ፡ "ጌታ ሆይ፡ ሄጄ ይሄን አደርጋለሁና፡ አቤቱ፡ እርዳኝ" እንደማለት፡ ጠበቀ፡ ሄዶ ምን ማድረግ እንዳለበት ጌታን ጠየቀ። እና፡ ኤፋዱን አምጥቶ፡ እንዲህ ይጠይቃል፡ "'በዚህ ቀውስ ውስጥ ምን ማድረግ አለብን?' እስኪ ቆመን እግዚአብሔርን እንለምነው፡" ኦህ፡ በእውነቱ ይህ ማለት የበለጸገ ነገር ነው። በአገሪቱ ውስጥ ከሚገኙት የመድኃኒት መደብሮች በበለጠ ቪታሚኖች ያሉት ነው። ወዳጆች፡ ሆይ፡ ያም በትክክል ይጠግናችኋል።

555 አሁን፡ ዛሬ ማታ፡ በእነዚህ ጥያቄዎች ላይ፡ ከቻልን፡ ከእኩለ ሌሊት በላይ ለመቆየት አላማ የ—የለንም። ስለዚህ—ወዲያውኑ፡ ወደ እነርሱ እንገባለን። የእነዚህን ጥያቄዎች ማጠናቀቂያ ነው፡ እና እነሱን መጨረስ በጀመርኩ ቁጥር... አሁን፡ እህት ሃቲ፡ ያን ማለቴ አይደለም፡ አንቺም ታውቂያለሽ። እ—እንዲሁ ለማለት ያክል ብቻ ነው፡ አየሽ፥ እሺ፡ መልካም። ነገር ግን ከአንድ አገልጋይ እጅግ ከባባድ ጥያቄዎች ደርሰውኛል፡ እና እነሱን ለመመለስ በጣም ከባባድ ናቸው። ታውቃላችሁ፡ ሰባኪዎች፡ መጽሐፍ ቅዱስን በራሳቸው ያጠሙታል በዚያም፡ መጥተው ከመጠየቃቸው በፊት የራሳቸውን መልስ ለማግኘት ይጥራሉ። እና... ይህ ነገር ጆርጂያ ወዳለው አንድ አገልጋይ ወዳጄ ለመላክ፡ እየተቀዳ ነው እርሱም ድንቅ የሆኑ ሰምንት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥያቄዎች አሉት፡ እጅግ ጥልቅ ናቸው።

556 አሁንም፡ በዚህ ሳምንት፡ ስለ እኛ መጸለይን አትርሱ።

557 እና ባለቤቴም እጅግ ተሽሏታል፥ ተነሥታለች፡ ዛሬ፡ ምግብ በማብሰል ረድታናለች። ከካናዳ ውድ ወዳጆቻችን፡ ወንድም፡ እና እህት ሶትማን፡ በእንግድነት እዚህ ከእኛ ጋር ናቸው፡ እኛም ስለጠየቁን እጅግ እናመሰግናለን። ሚስቴም፡ እየመጡ መሆናቸውን አውቃለች፡ እና፡ የእነዚህን ውድ ክርስቲያን

ሰዎች በአንዳንድ ጨዋታቸው እና ኅብረታቸውን ለመባረክ ትነሳለች። ዛሬ ማታ ወንድም ፍሬዲ ከእኛ ጋር ሆኖ በማየታችን ደስ ብሎናል፡ እሷም ከ... ዛሬ ጥዋት እዚህ ነበረች፡ እንደሚመስለኝ ግን ከ... ከ፡ አዎን፡ ከሚዳ ጋር ቀርታለች፡ እኛ ወደዚህ ስንመጣ እብራት ለመሆን ነው፥ ምክንያቱም ዛሬ ማታ የጌታ እራት እና እግር ማተጣጠብ ስለሚኖረን፡ ትንሽ እንደምናረፍድ አውቃለሁ። ስለዚህ እነርሱን እና እንግዶቻችንን ሁሉ መቀበላችን ደስ ይለናል።

558 አሁን፡ ለጥያቄዎች መልስ ለመስጠት ከመሞከራችን በፊት... እኔም ልሳሳት እንደምችል—ይሄን እንድታስታውሱ እፈልጋለሁ፡ እያችሁ፡ በማደርገው ነገር ሁሉ ልክ ነኝ ብዬ እ—አልልም። ትክክል ለመሆን እ—እሞክራለሁ፡ ምናልባት ግን ልሳሳት እ—እችላለሁ። ከ—ከተሳሳትኩም፡ ይቅር በሉኝ፥ እግዚአብሔርም፡ ይቅር እንዲለኝ እጸልያለሁ፡ ለመሳሳት ፈልጌ አይደለምና። በጭፍንነት-... ወይም እንዲሁ እንደመሰለኝ... መልስ መስጠት አልፈልግም፡ ባለኝ እውቀት ሁሉ በተቻለኝ እመልሳቸዋለሁ፡ እያችሁ። እና በመጽሐፍ ቅዱስ ጥያቄ ላይ ሀሳቤን መለወጥ ካለብኝም፡ ማድረግ ያለብኝ ያ ብቻ ይመስለኛል። የእግዚአብሔር ቃል ሲናገር፡ በማንኛውም ጊዜ፡ መለወጥ አለብን፡ የእግዚአብሔር ቃል ነውና።

559 አሁንም፡ ዛሬ ማታ፡ እንደተለመደው ለታመሙት እንጸልያለን። እና አንዳንዴ ግራ ያጋባል፡ እና፡ ከዚህ ከትንሿ ተበርናክል፡ እጅግ ያነሰ፡ አንሰተኛ ሕብረት ትይዙና፡ አንዳንዴ ማየት የምትፈልጉትን ውጤት አታዩም። ነገሩ ግን፡ የምታደርጉትን ነገር፡ ስህበታችሁ ምናልባት ከሁለት መቶ ሰዎች እየሳባችሁ ነው። እና ከትልቅ ስብሰባዎች አንዱ ላይ፡ ስህበታችሁ ምናልባት ከሶስት እስከ አሰር ሺ ሰዎች ይደርሳል፡ እያችሁ፡ ም—ምናልባት ከዚያ በላይም ይሆናል። ስለዚህ የበለጠ ግዙፍ ማየት የሚቻላችሁ፡ በዚህ መንገድ ነው። ዛሬ ማታ ግን፡ አንዳንድ ነገሮች እየመለስኩ ነበር... እርግጥ ነው ሰልካችን በየጥቂት ደቂቃዎች በቀን እና በሌሊት ይጮኻል።

560 እዚህ ቁጭ ብላ የምትታየኝ፡ ወይዘሮ ሬሰርት ናትን? መጽሐፍ ቅዱስሽ፡ እዚያ ጋር እህት፡ እህት ውድ ይዛልሻለች። ዛሬ ጠዋት ነው ያመጣሁልሽ፡ እናም ላ—ላቀብልሽ አልቻልኩም ነበር። ዛሬ ጥዋትም አ—አላየሁሽምና፡ ወይዘሮ ውድ ይዛልሻለች።

561 ስለዚህ የሰልክ ጥሪ እየመለስን እና የ—የተደረጉትን ታላላቅ ነገሮች እየተገነዘብን ነበርን። አንዲት ሴት ደውላችና፡ እንዲህ አለች፡ "ወንድም ብራንሃም፡ እኔ **በዚህ-በዚያ** ጉባኤ ነበርኩ እና **ለብዙ** ዘመን **በእንዲህ-በእንዲያ** ህመም በሰቃይ ኖሬ ነበር። እና፡ ታውቃለህ፡ ባለህበት ሆነህ ቃል ተናገርክ፡ ወዲያውም... " "ያለፈውን ህይወቴን በተነገረ ጊዜ ራሴን ልስት ነበር፡" አለች። እና "ከዚያ ጊዜ ወዲህ ተሠቃይቼ አላውቅም፡" ብላለች።

562 ሌላም አንዲት ሴት ገብታ እንዲህ አለች... ዛሬ ማታ እዚህ ትኖራለች ብዬ አስባለሁ፡ ወይም ከቤድፎርድ፡ ወይም ከዚያ አካባቢ ይመስለኛል፡ መኪና እየነዳች ትመጣለች። ይመስለኛል፡ የልብ ህመም የታመመው ልጃቸው፡ በከባድ ሁኔታ ውስጥ ሆኖ፡ እዚህ መጥቶ ነበር። እና እዚህ ሰብሰባው ውስጥ ተቀምጦ ሳለ፡ ጌታ ተንቀሳቀሰ እ—እና ልጁን ዳሰሰው... ልጁን ስለ ችግሩ ነገረው፡ እና እጁን እንኳ ማንሳት አልተቻለውም፡ እና በልብ ድካም፡ እና እጆቹም ሸባ የሆነ፡

ልቡም እንዲሁ ነበር። እና ወዲያውኑ መኪናው ውስጥ ገብቶ እየነዳ ወደ ቤቱ ተመለሰ፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ምንም አልተቸገረም። ከቤድፎርድ የመጣችው እመቤት እዚህ አለች? እዚህ አለሽ፡ እመቤት? ያቻትና፡ ከኋላ አለች። አዎን፡ ከጥቂት ጊዜ በፊት፡ ደውላልኛለች።

563 ሌላም ከኢቫንስቪል የሆነች ሴት ደውላልኝ ነበር። በጣም ሩቅ ስለሆነች እዚህ መድረስ አልቻለችም፡ ዛሬ ማታ የፈውስ አገልግሎት እንደሚኖረን አላወቀችም ነበር። እርሰዋም፡ "ወንድም ብራንሃም ሆይ፡ በኢቫንስቪል ጉባኤው ላይ ነበርኩ፡" እንዲህም አለች፡ "ህዝቡን ወደ ኋላ መለሰ ብለህ ተመልክተህ... እኔ ማን እንደሆንኩ፡ እና ምን እንዳደረግሁ ነገርከኝ፡ የምሰቃይባቸው ነገሮች እና፡ ሌሎች ነገሮች ነገርከኝ።" እርሰዋም፡ "የእስም በሽታ ነበረብኝ፡ እና ልክ ከትንሽ ልጅነቴ ጀምሮ በክፍሌ ውስጥ እሰማድርገን እና ሌሎች ነገሮችን እጥን ነበር።" "አሁን ሁለት አመታት አልፏል፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ አንድ ቦታ ተቸግሬ አላውቅም፡" አለች። አያችሁ?

564 እና ዛሬ እዚህ ለተገኛችሁ ሁላችሁ፡ ዛሬ ጥዋት ምስክርነቶቹ ላይ አልደረስኩም፥ ትላንትና፡ አሻንጉሊት ለመግዛት፡ ወደ ቴን-ሴንት ስቶር ሄጄ ነበር። እንግዲህ፡ ለራሴ አይደለም፡ አያችሁ። ለትንሿ ልጄ፡ ለርብቃ፡ ነው። ሳ—ሳራም፡ ዛሬ፡ የምትሄድበት ጉዳይ ነበራት። አንዳንድ ትንንሽ የትምህርት ቤት ጓደኞቿ፡ የልደት-ቀን ወይም የሆነ ነገር ትንሽ ስብሰባ ነበረባቸው፡ እና ትንሽ ስጦታ ነገር ይዛላት ሄደች፥ እና **ይሄን** የምታክል፡ አነስ ያለች አሻንጉሊት መግዛት ነበረብኝ። አንዲት ሴት ወደዚያ ቀርባ፡ እንዲህ አለችኝ፡ "ታስታውሰኛለህ?"

565 እኔም "አይመስለኝም፡" አልኳት።

566 በኋላ ግን አወቅኳት፡ የወንድም ኔቪል ዘመድ ነበረች፡ ወደ... ወደ ሰዊድን በመንገዴ ላይ ሳለሁ፡ ወደዚህ... መጥታ ነበር፡ በዊልቼ የሚሄድ ህጻን ልጅ ነበራት፡ ልክ እንደ ህጻን ኢዲት፡ ህጻኑም ካንሰር ነበረበት፡ በአንጎሉ ላይ ማሊግናንት እብጠት ነበረው። ትንሽ ጭንቅላቱ እንዲህ ተጣሞ ነበር፡ እና... ዶክተሮቹም በሕይወት እንዲኖር ሶስት ሳምንታት ሰጥተውት ነበር። አውጥተውም መርምረው አይተውታል... ምን ነበር፡ እና ለመኖር፡ ሶስት ሳምንታት ብቻ ሰጡት። በወንበርም ማሽከርከር ነበረባቸው፡ ከዚያም ወደ ክፍሉ ሲሄድ በቃሬዛ ላይ ያስቀምጡታል፡ እና ከምርመራ በኋላ ወደ ታች ያወርዱት ነበር። ሄደን ለብላቴናው ጸለይንለት፡ ጌታም እንዲፈውሰው ጠየቅን። በማግስቱም፡ ወደዚያ ይዘውት ሲሄዱ፡ "ዊልቸሩን አልፈልግም፡" አላቸው።

567 መኪናው ውስጥ ገባና ወሰዱት፡ ዶክተሩ ስትሬቸር ይዞ መጣና፡ ዶክተሩንም "ስትሬቸሩን አልፈልገውም፡" አለው።

568 ወደዚያ ፈጥኖ ተቀመጠ፡ ሐኪሙም መረመረው፡ እንዲህ አለው፡ "እንግዲህ፡" "ሦስት ሳምንት ከመስጠት ይልቅ፡ አንድ መቶ ሰምንት ዓመታት ሰጥቼሃለሁ፡" አለው።

569 እና፡ ትላንትና፡ እናቲቱ አገኘችኝ። እና እስከማውቀው ድረስ፡ ዛሬ ማታ፡ እዚህ ያለች ይመስለኛል። እና ትንሹ ልጅ አሁን ወጣት ሆኖ፡ እግር ኳስ በመጫወት ላይ ነበር። ማሊጋንት፡ የጭንቅላት ካንሰር፡ እስኪታይ ድረስ ሆኖ ነበር...

570 ኦህ፡ ሺዎች ነገሮች፡ እያችሁ። እግዚአብሔር ፈጽሞ አይወድቅም። በ—በፍጹም አይወድቅም።

571 ወንድም ጆን፡ ዓይንህ ተሻለህ፡ ወንድሜ? አደጋ አጋጥሞት ነበር፡ ሚስማር እየመታ ሳለ አይኑ ላይ ተፈናጥረበት። እናም ሁላችንም ለወንድም ጆን ኦባንኖን እየጸልይንለት ነበርን፡ ይህ ሚስማር አይኑ መትቶት አደጋ የገጠመው ወንድማችን ከሎይቪል ነው።

572 አሁን፡ እነዚህ ጥያቄዎች—የአንድ ሰው የልብ ጥልቅነት ጥያቄዎች ናቸው፥ መጽሐፍ ቅዱስን ሲያነቡ እነዚህን ነገሮች አገኙና፡ ምናልባትም... በራሳቸው አልረኩም ይሆናል፡ ስለዚህ መልስ እንድንሰጥባቸው ወደዚህ ወደኛ አምጥተውታል። እና ምን አይነት ችግር ውስጥ እንዳስገባን ታያላችሁ፥ ምክንያቱም፡ እናንተ በምትሉት ነገር ላይ፡ ያርፋሉና። ስለዚህ ትክክል መሆናችሁን እርግጠኛ መሆን ይጠበቅባችኋል፡ እኔም... እንደ እናንተ እርግጠኛ ነኝ። ስለዚህ፡ እኛ ትክክል መሆናችንን ማረጋገጥ ያለብን ነገር፡ እራሶቻችንን ዝቅ አድርገን፡ ይህን እንዲተረጉምልን አሁን መንፈስ ቅዱስን እንለምነው።

573 አሁን፡ የሰማይ አባት ሆይ፡ አቤቱ፡ ታላቁ የሰማይና የምድር ፈጣሪን “አባ” ብለን መናገር መቻላችን እንዴት ያለ መታደል ነው። የእነዚህን ጥያቄዎች አሁን ኃላፊነት እንድትወስድ እንጠይቃለን። በጥልቅ ቅንነት በእኛ ፊት አቅርበዋቸዋልና። እግዚአብሔር ሆይ፡ እነዚህ ጥያቄውች ለመመለስ፡ ከልባችን በመነጨ በጥልቅ ትህትና፡ የአቅማችንን መመለስ እንችል ዘንድ፡ እርዳን።

574 ምሕረትህም በእያንዳንዱ ላይ ይደር። እና ዛሬ ማታ እዚህ ያለውን ሁሉ የሚረዳ አንዳች ነገር ይባል። ለሕሙማን ጸልየን፡ የጌታን እራት ወስደን እና የመሳሰሉትን አድርገን ከወጣን በኋላ በኋላ፡ እንደ ኤማሁስ መንገደኞች እንዲህ ማለት ይሁንልን፡ “በመንገድ ሲናገረን ልባችን በውስጣችን ይነድብን አልነበረምን? ” በኢየሱስ ስም እንጠይቃለን። አሜን።

575 አሁን፡ ብዙ ጊዜ እንዳልኩት፡ እ—እነዚህ ነገሮች—እንደ እኔ አስተያየት በጣም የተሻሉ የተባሉ ናቸው፡ እና አንዳንድ ጊዜም ትንሽ ውይይት ያስነሳል። እንደኛው፡ ከዚህ በፊት በተናገርኩት ጉዳይ እንደሆነ አይቼዋለሁ፡ በድጋሚ መጥቷል። እንግዲህ... ከፈቀዳችሁልኝ፡ አሁን ላነበው እፈልጋለሁ።

## 65. አዳምና ሔዋን ልጆቻቸውን በኤደን ሲወልዱ፡ ያን ጊዜ በምድር ላይ ሌሎች ሰዎች ነበሩን? በዘፍጥረት ምዕራፍ 5 እና 16 ኛ ቁጥር ላይ፡ ቃየን በኖድ ምድር ተቀመጠ ሚስቱን አወቀ ይላልና።

576 አሁን፡ ይህ እጅግ—ድንቅ ጥያቄ ነው። አሁን፡ የተማርነው መጽሐፍ ቅዱስ ነው... እና ብዙ ጊዜ እነዚህ... አንዳንድ ጊዜ በግዴለሽነት... ትንሽ ወረቀት ላይ ጽፌ፡ “ማንኛውንም የመጽሐፍ ቅዱስ ጥያቄ ለመመለስ። ጠይቁ፡” እል ነበር።

577 አንድ ሰውም እንዲህ አለ፡ “እሺ፡ የቃየን ሚስት ማን ነበረች? ”

578 በእሱ ወይም በሌላ ነገር ትንሽ እቀልድበታለሁ፡ ኦህ፡ “ኦህ፡ የአማቱ-ሴት-ልጅ ነበረች፡” ወይም እንደዚያ ያለ ነገር፡ ያው እንደምታውቁት፡ ወ—ወይም “ወይዘሪት ቃየን ነበረች።” ያ ግን ለጥያቄው መልስ አይሰጥም። እ...

579 በዚያም ቃየን ሚስት ነበረችው፡ መጽሐፍ ቅዱስ እንደነበረችው ይናገራልና። ቃየንም ሚስት ከነበረው፡ ከሆነ ቦታ ያመጣት መሆኗ የማይቀር ነው። ስለዚህ ይህ ከዚህ ጋር በቀጥታ ይካተታል፥

**አዳምና ሔዋን በኤደን ገነት ልጆቻቸውን ሲወልዱ በምድር ላይ ሌሎች ሰዎች ነበሩን?**

580 አሁን፡ ልብ ካላችሁ፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለ ሴት መወለድ አልፎ አልፎ ተመዝግቧል። በመጽሐፍ ቅዱስ መዝገብ ውስጥ የሚጠራው ሴቲቱ ሳትሆን፡ ወንዱ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፡ ስለ ሴት ልጅ መወለድ አልፎ አልፎ ተጠቅሷል። ወይም፡ እውነቱን ለመናገር፡ በእእምሮዬ ውስጥ፡ ልጅ የተወለደበት መዝገብ፡ "ወንዶችና ሴቶች ልጆችን ወለዱ፡" የሚል፥ አሁኑኑ ማስታወስ እችል እንደሆነ አላውቅም።

581 አሁን፡ መጽሐፍ ቅዱስ ለአዳምና ሔዋን ሦስት ልጆች እንደተወለዱላቸው ይናገራል፡ እነርሱም ቃየን፡ አቤል፡ እና ሴት ነበሩ። አሁን፡ ሦስቱም ወንዶች ከነበሩ፡ ሴት ልጆች ባይወለዱ ኖሮ፡ እና ብቸኛዋ ሴት (ሔዋን) ስትሞት፡ የሰው ዘር ያን ጊዜ ሕልውናውን ባቆመ ነበር፡ ምክንያቱም ማናቸውም ቢሆኑ የሰው ዘር የበለጠ የሚያስፋፉበት... ሌላ መንገድ አ—አልነበራቸውም፡ ምክንያቱም እንሥት ባልተገኘች ነበር። ሔዋን ብቸኛዋ በሆነች ነበር። ነገር ግን፡ እያችሁ፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የ—የሴት ልጅ መወለድ፡ አይመዘገቡም ነበር፡ ስለዚህ ወንዶች እንደነበሯቸው ሁሉ ሴቶችም ነበሯቸው።

582 አሁን፡ ከጥንታውያን ጸሐፊዎች መካከል አንዱ የነበረው፡ ጆሲፈስ የተባለው፡ ጥንታዊ ጸሀፊ፡ ለአዳም እና ለሔዋን፡ ሰባ ልጆች እንደተወለዱላቸው ይናገራል፡ እጅግ ጥንታዊ ጸሀፊ ነው፡ "ሰባው ልጆች፡ ወንዶችም ሴቶችም ነበሩ።"

583 አሁን፡ ቃየን... ወደ ኖድ ምድር ከሄደ... አሁን፡ ልብ ካላችሁ፡ ጸሃፊው እዚህ ጋር በጣም፡ እጅግ ድንቅ ጽሑፍ ጽፏል። እንዴት እንደጠቀሰው አውቃችኋል?

> **በኤደን፡ ልጆቻቸውን በኤደን በወለዱ ጊዜ...** አሁን፡ ጸሐፊው በኤደን ገነት ውስጥ አላለም፡ ጸሐፊው ይሄን ያውቃል። ይህን ማስታወሻ የጻፈው ሰው ማንም ይሁን ማን፡ እንዲህ ይላል፥ **አዳምና ሔዋን ልጆቻቸውን በኤደን በወለዱ ጊዜ...**

584 በኤደን ገነት ውስጥ አይደለም፡ ምክንያቱም ከኤደን ገነት ስለተባረሩ። ይሁን እንጂ አሁንም ገና በኤደን ውስጥ ነበሩ፡ እና የኤደን ገነት በኤደን ምስራቅ በኩል ነበረች። ኤደን እንደ ከተማ ወ—ወይም እ... እንደ ግዛት ነበረች፡ ኖድም እንዲሁ ቀጥላ የምትገኝ ሌላ ግዛት ወይም ከተማ ነበረች።

585 አሁን፡ ቃየን ሊያገኛት፡ ወይም ሊያገባት የሚችለው ብቸኛ ሰው፡ የገዛ እህቱ መሆን ነበረባት። ግድ ነው። ምክንያቱም ይህ ወንድና ሴት ሊመጡ የሚችሉበት ብቸኛው መንገድ አንድ ብቻ ነው፡ እያችሁ፡ እርሱም የራሱን እህት በማግባት ነው። ይህም፡ በዚያ ዘመን ህጋዊ ነበር።

586 በእግዚአብሔር የተለየው፡ ይስሐቅም፡ የበኩር የአጎቱ ልጅ ርብቃን አገባ። ሣራ የአብርሃም እኅት፡ የገዛ እኅቱ ነበረች፡ በእናቱ ሳይሆን፡ በአባቱ። እያችሁ፡

አብራሃም—የገዛ እህቱን አገባ፥ በእናታቸው ይለያያሉ፡ አባታቸው ግን አንድ ነበረ።

587 ስለዚህ፡ አያችሁ፡ የ—የደም ሐረግ በሰው ዘር ውስጥ ከመዳከሙ በፊት፡ ዘመድህ ማግባት፡ ሕጋዊ እና ትክክል ነበር። አሁን ግን አይደለም። ዛሬ እህትህን ብታገባ፡ እና ልጆች ከወለድክ፡ ምናልባት የሆነ ነገር ይሆናሉ... እንዲሁ፡ በሽተኞች ይሆናሉ። እስከ አንደኛ እና ሁለተኛ የአጎት ልጅ እንኳን ፈጽሞ መጋባት የለበትም፡ አያችሁ፡ ምክንያቱም የደም ሐረጉ እየቀነሰ እና እየቀነሰ ሄዷል።

588 ነገር ግን ቃየን ሊያደርግ የሚችለው፡ ብቸኛው ነገር፡ የራሱን እህት ማግባት ነበር። ልጆች የተወለዱትም በዚህ መንገድ ነው... ሚስቱን አግብቶ፡ ወደ ኖድ ምድር ሄደ አወቃትም፡ በዚህ መንገድ—ልጆቹ ተወለዱ። አያችሁ፡ እ...

589 እና ልብ ብላችሁ ከሆነ፡ ከቃየል ሐረግ ውስጥ ብልህ ሰዎች ተወለዱ። ከሴት የዘር ሐርግ ሃይማኖተኛ ሰዎች ተወለዱ፡ ማለቴ፡ የ—የጽድቅ ሐረግ ተወለዱ። አሁን እኛ ያለን የዘር ሐርግ፡ ዋናው ምንጩ፡ ከእነዚህ ሁለቱ የመጣ ነው።

590 (ይህን ጥያቄ በማገባደድ ላይ) ዛሬ ልብ ካላችሁ፥ ያንን የቃየል የዘር ሐረግ አሁንም አለ፡ የሴት የዘር ሐረግም አለ። ሁለቱም በአንድ አይነት አወራረድ መጥተዋል። የቃየን ልጆች ዛሬ ማታ እዚህ ጄፈርሰንቪል ውስጥ ይገኛሉ፡ የሴት ልጆችም ዛሬ ማታ እዚህ ጄፈርሰንቪል ውስጥ አሉ። የደም ሐረጉ እየተዳከመ እና እየደበዘዘ ቢሄድም፡ የዘር ሐረጉ ግን አሁንም ይቀጥላል።

591 አሁን፡ ተመልከቱ። የቃየን ልጆች ሁሌም እንዲህ ነበሩ... ከአንቲሉቪያን ጥፋት በፊት፡ ብልህ ሰዎች ነበሩ፥ ሳይንቲስት፡ አስተማሪዎች፥ እና በጣም ሃይማኖተኞች ቢሆኑም፡ ነገር ግን የተወገዙ ስብስብ ነበሩ። አያችሁ? አሁን ተመልከቱ፡ እነሱም ልክ እንደ አባታቸው እንደ ቃየል ነበሩ። ቃየን፡ ሃይማኖተኛ ሰው ነበር። ያማረ መሠዊያን ሠራ፡ የሚያምር ቤተ ክርስቲያንም አደረገ፡ እና የሴት ከነበረችው ትንሿ ተልእኮ በበለጠ ቆንጆ እንድትመስል ለማድረግ ሞከረ። ይህን ታውቃላልችሁ? እውነትም ሞክሯል... መሠዊያውን በአበባ አስጌጠው፡ አስማመረውም፡ ቆንጆ አደረገው፥ ይህን በማድረግ በእግዚአብሔር ፊት ሞገስን እንደሚያገኝ ሰላሰበ፡ ታላቅ፡ እና ድንቅ፡ ያበጠች ቤተ ክርስቲያን ሠራ።

592 አቤልም ሄዶ ታናሽ በግ አመጣ፡ ወደ መሠዊያውም ጎትቶ፡ በዓለት ላይ አጋድሞ ገደለው።

593 እንግዲህ አሁን፡ እግዚአብሔር ጻድቅ ነው ከተባለ፡ የሚፈልገውም አምልኮ ከሆነ፡ ቃየን ልክ እንደ አቤል በቅንነት ወደ እግዚአብሔር አምልኮን አቀረበ። ሁለቱም ቅኖች ነበሩ። ሁለቱም በእግዚአብሔር ፊት ሞገስን ለማግኘት እየሞከሩ ነበር። አንዳቸውም አረማውያን አልነበሩም። ሁለቱም፡ ሙሉ በሙሉ፡ ያሕዌ የሚያምኑ ነበሩ። አሁን፡ እዚህ ውስጥ፡ ልናስብበት የሚገባን ነገር ይስጠናል።

594 ዛሬ ማታ እዚህ ያላችሁ፡ አንዳንድ ሰዎች፡ ከዚህ በፊት አይቻችሁ አላውቅም፡ ከዚህ በፊት ፍጹም አይቻችሁ አላውቅም። ይሁን እንጂ ይህን

መገንዘብ አለባችሁ፡ በልባችሁም ውስጥ እኑሩት። እያችሁ? የቱንም ያህል ሃይማኖተኛ ብትሆኑ፡ ያ ምንም ግንኙነት የለውም። መኖሪያችሁ በቤተክርስቲያን ውስጥ ሊሆን ይችላል፡ ሁሌም በጣም ቅኖች ልትሆኑ ትችላላችሁ፡ ቢሆንም አሁንም የጠፋችሁ ናችሁ! እያችሁ?

595 እንዲህም ትላላችሁ፡ "እንግዲህ፡" ትላላችሁም፡ "ፓስተሮቻችን እጅግ ብልሆች ናቸው፡ የተሻለውን ትምህርት ለማግኘት በሴሚናሮች ተምረው አልፈዋል። የቲኦሎጂ ምሁራን ናቸው፡ ቲኦሎጂውን እና ሌ—ሌላውን በሙሉ ያውቁታል። እጅግ የሰለጠኑ፡ ብልሆች፡ አለ ከተባለው ሁሉ... የተመረጡ ናቸው።" እያችሁ? በዚህ ሁሉ ግን ሊጠፉ ይችላሉ!

596 አሁን በቃየን፡ የዘር ሐረጉ ላይ፥ ሁሉም፡ በጣም ሃይማኖተኛ፡ ነበሩ፥ በጣም ታዋቂ ሰዎች ነበሩ፥ ሳይንቲስቶች፡ እና ዶክተሮች፡ አናጢዎች፡ ሰራተኞች፡ እና ብልህ ሰዎች ነበሩ። ይሁን እንጂ ከቃየን ጀምሮ፡ እስከ ታች ድረስ የዘር ሐረጉ በሙሉ ተቀባይነትን አጡ።

597 በአቤልም በኩል፥ ግንበኞች ወይም አስተማሪዎች ወይም ብልህ ሰዎች አልነበሩም፥ ይብዛም ይነስም፡ በመንፈስ ብቻ የሚመላለሱ፡ ትሁታን፡ በግ አርቢዎች፡ እና ገበሬዎች፡ ነበሩ።

598 አሁን፡ መጽሐፍ ቅዱስ፡ "በክርስቶስ ኢየሱስ ላሉት ኩነኔ የለባቸውም፡ እንደ መንፈስ ፈቃድ እንጂ እንደ ሥጋ ፈቃድ አይሄዱምና።" መንፈሳዊ ሰው ፈጽሞ ሊሞት የማይችል መንፈሳዊ ነፍስ አለው። ሥጋዊ ሰው በዙሪያው ሃይማኖታዊ ድባብ አለው (እና ማምለክ ይፈልጋል ወዘተ) ግን ሥጋዊ ነው፥ ሥጋዊ አማኝ ነው እንጂ፡ የማያምን አይደለም፥ ስለዚህ ተቀባይነት ያላገኘ አይነት ነበረ።

599 አሁን፡ ቃየን፡ ከዚያ ሄዶ ሚስቱን በኖድ ምድር አገባ። አሁን፡ ሴት ማን እንዳገባ፡ ወይም ሌሎች ማን እንዳገቡ አይናገርም። እና እዚህ ውስጥ ልናውቀው የሚገባን እጅግ ድንቅ የሆነው ነ—ነገሩ፡ ቃየን ማግባቱ ነው፡ በዚህ ጉዳይ ላይ መልስ ይዘናል። ምክንያቱም እህቱን ማግባቱ የማይቀር ነገር ነው፡ ወይም ካ... ካልሆነ ግን...

600 ከሔዋን የተወለዱ ካልሆኑ በቀር፡ በምድር ላይ ሌሎች ሴቶች አልነበሩም። እሷም የሕያዋን ሁሉ እናት ነበረች። ይህ ማለት፡ በህይወት ለሚኖሩ ሰዎች ሁሉ፡ እናታቸው ነበረች ማለት ነው። የዚህ ምክንያት ይህ ነው... ማለት **ሔዋን** የሚለው ቃል ትርጉሙ "የሕያዋን ሁሉ እናት ማለት ነው።" እሷም ይችን ልጅ ወለደች። ቃየንም የገዛ እህቱን አገባ፡ እኔ የማየው ብቸኛው መንገድ በዚህ ነው። ስለዚህ በዚያ ዘመን የሚኖሩ ሰዎች ነበሩ፡ በትክክል። እያችሁ? እሺ፡ እ...

> **አዳምና ሔዋን ልጆቻቸውን በኤደን በወለዱ ጊዜ...** አሁን ተመልከቱ፡ ጥያቄው ይህ ነው፥ **ልጆቻቸውን በኤደን በወለዱ ጊዜ፡ በዚያ ጊዜ በምድር ላይ ሌሎች ሰዎች ነበሩን**? አልነበሩም! **በዘፍጥረት 5፡ 16 ላይ፡ እያችሁ፡ ቃየን በኖድ ምድር ተቀመጠ ሚስቱንም አወቀ።** በትክክል። እያችሁ?

601 ሰውን በራሱ አምሳል የፈጠረበት፡ በዘፍጥረት 1 ላይ ነው፡ ይህም በቲዎፋኒ ውስጥ ነበር። በዘፍጥረት 2 ላይ ደግሞ፡ ሰውን ከምድር አፈር አበጀው፡ ይህም አሁን የምናውቀው የሰዎች ልጆች ሰው ነው። በመቀጠል፡

በ3 ላይ ውድቀት ገባ፡ ከኤደን ገነት ተባረረ፥ ከዚያም ልጆቹ ልጆችን ወለዱ። ቃየንም ሚስቱን ወስዶ ከእርስዋ ጋር በኖድ ምድር ኖረ፡ እግዚአብሔር ከገዛ ወንድሙ ጋር ካለው ሕብረት ስለለየው፡ ከዚያ ወጣ (ይህም በ—በአቤል ሞት ምክንያት ነው)። እና እርሱም ያገኛት ያቺን ነው፡ የገዛ እህቱ፡ እሷንም አገባት፥ እኔ ራሴ፡ ማግባቱን—ማየት የምችልበት ብቸኛው መንገድ፡ ይህ ነው።

602 አሁን፡ እንደሚወራው... እንግዲህ እዚህ ያሉ ጥቁር ወዳጆቼ ስለዚህ አስተያየት በይቅርታ እንዲያልፉት ተሰፋ አደርጋለሁ፡ ምክንያቱም ፍጹም ትክክል አይደለም። ከተለወጥኩ በኋላ፡ በህይወቴ ለመጀመሪያ ጊዜ የተገናኘሁት... እነ... ወንድም ጆርጅ ዲያርክ እና ሌሎች ነበሩ። እና እየተጓዝኩ፡ ጌታ ወደ አንዲት ትንሽ ቦታ መራኝ። እና ጥቁር ሰዎች ከምን የመጡ ስለመሆናቸው እየተወያዩ ነበሩ። እና ስለ ጥቁር ሰው እንዲህ ለማለት እየሞከሩ ነበር፡ ይህም ቃየን እንደ ዝንጀሮ የመሰለች እንስሳ እንዳገባ፡ እና በዚያም የጥቁር ዘር መጣ እያሉ ነበር። አሁን፡ ያ ስህተት ነው! በፍጹም፡ ስህተት ነው! እና ያንን በጭራሽ አትያዙ። ምክንያቱም እስከ ጥፋት ውኃ ድረስ፡ ጥቁር ወይም ነጭ፡ ወይም ሌላ የተለየ የሰው ዘር አልነበረም። ከዚያም ከጥፋት ውኃ እና ከባቤል ግንብ በኋላ፡ መበተን በጀመሩ ጊዜ፡ ቀለሞቻቸውን እና የመሳሰሉትን ነገሮች መያዝ የጀመሩት ያኒ ነው። ሁሉም ከአንድ ዛፍ የመጡ ናቸው። በትክክል ትክክል ነው። አዳምና ሔዋን፡ በምድር ለነብሩ የሰው ልጆች ሁሉ፡ ምድራዊ አባታቸው እና እናታቸው ነበሩ። ይህም እውነት ነው። ለጥቁር፡ ነጭ፡ ግራጫ፡ ቡኒ፡ ቢጫ፡ ምንም አይነት ቀለም ቢሆኑ፡ ይህ የሆነው ከምትኖሩበት አካባቢ የተነሣ ነው፡ ይህም ሲሆን—እ... እንደ...

603 ከዚህ ሳልወጣ ባብራራው የተሻለ ይመስለኛል። አሁን ያሉት ሰዎች በእነዚህ ልዩነቶች እና ህጎች እና በሚያልፏቸው ነገሮች ውስጥ መለያየታቸው፡ አስቂኝ ይመስለኛል። የእውነቴን ነው። ስሙኝ፡ እነዚህ ሰዎች ተወአቸው፡ የሚያስፈልጋቸው የሚያውቁ ናቸው። እግዚአብሔር አንድን ሰው ጥቁር አድርጎ ሰራው፡ በሰራውም ደስተኛ ነው። በትክክል! እግዚአብሔር ጥቁር አድርጎ ቢሰራኝ፡ ደስተኛ እሆናለሁ፥ ቡኒ አድርጎ ቢሰራኝ፡ ደስተኛ እሆናለሁ፥ ቡኒ አድርጎ ቢሰራኝ፡ ደስተኛ ነኝ፥ ቡኒ አድርጎ ቢሰራኝ፡ ደስተኛ እሆናለሁ። እግዚአብሔር በየቀለማችን አደረገን፡ እኛም እሱ በሚፈልገው መንገድ አድርጎናልና፡ ሁላችንም ልጆቹ ነን። በትክክል! እና እንደዚያ ማሾፍ እና መንቀጥቀጥ የለባቸውም። ያንን ማድረግ ስህተት ነው። ሊያደርጉት አይገባም። በሚያስፈልገን መንገድ... እግዚአብሔር አደረገን።

604 ስለዚህ ጥቁሩ ሰው፡ እየተነሣ ነገሩን ማፍረስ—ትውልዱን እና ቀለሙን ማጥፋት፡ ከነጭ ጋር እና እንደዚያ ከመሳሰሉ ሌሎች ጋር መደባለቅ የለበትም። እኔ አልወቅሳቸውም። በጭራሽ። ጥቁር ሰው ለነጭ የሌለው ነገር ያለው ሰው ነው። በትክክል! ይህ በእውነት ትክክል ነው። አምላክም እንደዛ እንዲሆኑ አላሰበም።

605 እንግዲህ፡ ተመልከቱ። ጥቁር ሰው... እ—እ... አንድ ነገር—አንድ ነገር አለው ነጩ ሰው ፈጽሞ የሌለው አቋም አለው። ደስተኛ-ሆኖ-በዕድል ይሄዳል፡ እና “እግዚአብሔርን እምኖ፡ ሌላውን የሚተው ነው።”፥ አገኘም አላገኘም፡ እንዲሁ ደስተኛ ነው። በዚህ ምሽት፡ ይህ ነገር በብዛት እንዲሆንልኝ እመኛለሁ፡

በእውነት እመኛለሁ። እንግዲህ፡ ይህ ነገር አላቸው፡ ርስታቸውም ነው፥ እነርሱም፡ ከሌላ ዘር ጋር መቀላቀል እና ማጥፋት አይፈልጉም። ትክክል ነው።

606 የሽርቬፖርትዋ ሴትዮ የተናገረችው ነገር—በህይወቴ ከሰማኋቸው ምርጥ አስተያየቶች አንዱ እንደሆነ ይሰማኛል። አስተያየት ሰጠች፡ እና ጋዜጣ ላይ አሰፈሩት። ወጥታ፡ እንዲህ አለች፡ "እነዚህ አሁን እየሆኑ ባሉ፡ በእነዚህ መገለሎች ምክንያት፡ ልጆቼ ነጮች በሚማሩበት ትምህርት ቤት እንዲማሩ አልፈልግም።" "ጥቁር መምህር ቢኖራቸው ኖሮ አሁን ያላቸው ምልከታ አይኖራቸውም ነበር፡" አለች። ሴቲቱ ብልህ ሴት ነች። የምትናገረውን ታውቃለች፡ የተሻለ ትምህርት አግኝተዋል። ትክክል ነው። ስለዚህ ህዝቡ ያንን በማድረግ ስህተት የሚሰራ ይመስለኛል።

607 ስለዚህ እንዲህ ይላሉ፡ "ቃየን እና አቤል... " ወዘተረፈ ይላሉ። አይደለም፡ ወዳጄ! ቀለም ከዚህ ጋር በምንም አይገናኝም። ከዚህ ጋር የሚያገናኘው በውስጡ ያለው መንፈስ ነው። በትክክል ልክ ነው።

608 ስለዚህ ቃየን ሚስቱን አወቀ፡ እሷም እህቱ ናት። እርሱም... ወደ ኖድ ምድር ወሰዳት፡ በዚያም የምድርም ታላላቅ ነገዶች፥ ሃይማኖተኞችና አምልኮ አቅራቢዎች ወጡ።

609 እስኪ ዛሬ አስብበት፡ ወዳጄ፡ ቆም ብለህ አስበው። በአሥር ሺዎች ጊዜ በአሥር ሺዎች እና በሺዎች የሚቆጠሩ፡ በፍጹም ቤተ ክርስቲያን-የሚሄዱ ሰዎች አሉ፡ በቻሉት ሁሉ ለቤተክርስቲያኒቱ ትጉሃን ናቸው፡ ቃየንም ይሄን ያክል ጠፍቶ ነበረ። አያችሁ? የሚመርጠው እግዚአብሔር ነው! ምርጫ የእግዚአብሔር ነው! አያችሁ? ምሕረትን የሚሰጥ አምላክ! ጭቃው ሸክላ ሠሪውን አያዘውም፡ በሸክላው ላይ ሸክላ ሠሪው የበላይ ነው። ትክክል ነው።

610 አሁን ደግሞ፡ ቀጥሎ ያለው እጅግ ድንቅ ነው፥

> **በሁለተኛው ጴጥሮስ 2፡4—2፡4...**

611 መጽሐፍ ቅዱስ የያዘ ሰው ካለ፡ ከፈለጋችሁ፡ እኔ መጽሐፉን እያነበብኩ እናንተም ክፈቱ፡ እና ወደ ጥያቄው ስንገባ ሳለን፡ እናንተም ተባበሩኝ።

612 አሁን፡ በዚህ በቃየን ላይ እና—እና ወዘተ፡ ያ ካላረካችሁ፡ ደግመን ለማየት ፍቀዱልን። ደስ ይለናል...

613 አሁን ሁለተኛ ጴጥሮስ 2፡4። እሺ፡ ወዳጄ፡ ይኸው፥

**66. ሁለተኛ ጴጥሮስ 2፡4፣ "እግዚአብሔር... እግዚአብሔር ኃጢአትን ላደረጉ መላእክት ሳይራራላቸው፡ ወደ ገሃነም ከጣላቸው፡" ታዲያ ክርስቶስ በእስር ለነበሩት ነፍሳት ለምን ሰበከላቸው፡ 1ኛ ጴጥሮስ 3፡19?**

614 አሁን፡ በመጀመሪያ፡ ጴጥሮስ 2፡4 ላይ። እሺ፥

> **እግዚአብሔር ኃጢአትን ላደረጉ መላእክት ሳይራራላቸው፡ ወደ ገሃነም—ጥሎ፡ በ—በጨለማ ጉድጓድ ለፍርድ ሊጠበቁ፡ አሳልፎ ከሰጣቸው፥**

615 አሁን፡ አሁን በአንደኛው ጴጥሮስ እንመልከተው (ያ በሁለተኛው ጴጥሮስ ነው)፡ 1ኛ ጴጥሮስ 3፡19 ላይ፡ ይህን አድምጡ። ይኸው፡ እዚህ ጋር ነው። ጽፌ አልያዝኩትም፡ ምክንያቱ አሁን ነው ትዝ ያለኝ።

**… እርሱም ደግሞ… ሄዶ በወኅኒ ለነበሩ ነፍሳት ሰበከላቸው፥**

616 ኦህ፡ አዎን፡ እዩት እንግዲህ። እስኪ ትንሽ ከፍ ብለን፡ ከቁጥር 18 እንጀምር፥

**ክርስቶስ ደግሞ… ወደ እግዚአብሔር እንዲያቀርበን፡ እርሱ ጻድቅ ሆኖ ስለ ዓመፀኞች፡ አንድ ጊዜ በኃጢአት ምክንያት ሞቶአልና፡ በሥጋ ሞተ፡ በመንፈስ ግን ሕያው ሆነ፡**

**በእርሱም ደግሞ ሄዶ በወኅኒ ለነበሩ ነፍሳት ሰበከላቸው፥**

**ቀድሞ አልታዘዙም ነበርና፡…**

617 ውድ ወዳጄ ሆይ፡ የሚቀጥለውን ቁጥር ብታነብ፡ በደንብ አብራርቶታል። አየህ?

**ጥቂቶች** ማለት **ሰምንት ነፍስ፡ በውኃ** የዳኑበት **መርከብ ሲዘጋጅ፡ የእግዚአብሔር ትዕግሥት፡ በኖኅ ዘመን፡** በቈየ ጊዜ፡ **ቀድሞ አልታዘዙም።** አያችሁ?

618 አሁን፡ እዚህ ውስጥ ካስተዋላችሁ፡ ይህ ሰባኪ በዚህ ተመሳሳይ ርዕስ ላይ… ተጨማሪ ያለው ይመስለኛል፡ ከአፍታ በኋላ እመልሰዋለሁ።

619 አንደኛ ጴጥሮስ 4… ወይም 2፡4፣ ልብ በሉ፡ “እግዚአብሔር ለመላእክቱ ሣይራራላቸው፡” angel መልአክ ሲጻፍ አጻጻፉ እንዴት ነው? ትንሿ “a.” አያችሁ? አሁን፡ እዚህ ጋር፡ “በኖኅ ዘመን በቈየ ትዕግሥት ንስሐ ያልገቡ በእስር የነበሩት ነፍሳት፡” መላእክቱ እነሱ ናቸው። ሰዎች፥ መልእክተኞች፡ ሰባኪዎች ናቸው፥ “እነዚያን መላእክት አልራራላቸውም።” **መልአክ** የሚለው ቃል… የመጣው “መልእክተኛ” ከሚለው እንደሆነ ታውቃላችሁ? **መልአክ** ማለት “መልእክተኛ” ማለት እንደሆነ ሰንቶች ታውቃላችሁ? መልአክ ማለት፡ መልእክተኛ ማለት ነው፡ “ለእነዚያ መላእክትም አልራራላቸውም።” አያችሁ?

620 እና እዚህ በዕብራውያን ላይ፡ ከጥቂት ሳምንታት በፊት እንዳየነው ትዝ ይላችኋል፡ “መላእክት”?

621 እዚህ ጋር-… ራእይ ዮሐንስ ላይ፡ “ይህን ወደ ሰርዴስ ቤተ ክርስቲያን መልአክ ጻፍ። በኤፌሶን ወዳለው ወደ ቤተ ክርስቲያን መልአክ ይህን ጻፍ። ለቤተ ክርስቲያኒቱ መልአክ ይላል… ” ትዝ ይላችኋል? እና **መልአክ** የሚለውን ቃል ወስደን፡ ከመዝገበ ቃላት አይተነዋል፡ ትርጉሙም “መልእክተኛ” ሆኖ አግኝተነዋል። **መልአክ** የሚለው ቃል “በምድር ላይ ያለ መልእክተኛ፡ መለኮታዊ የሆነ መልእክተኛ፡” ሊሆን ይችላል።

622 ስለዚህ በዚህ ጉዳይ፡ ከመዝገበ ቃላት ወስደን ብንመረምረው፡ “መልእክተኞች፡ የመጀመሪያዎቹ መልእክተኞች” በማለት ይጀምረዋል። አያችሁ፡ “ሣ… ሣይራራላቸው… እግዚአብሔር ኃጢአትን ላደረጉ መላእክት ሣይራራላቸው፡” (አያችሁ? ) “እና መለኮታዊ የሆኑ ፍጥረታት፡” (አያችሁ? ) “ከዚያ ትዕግስት በኋላ… ”

አሁን ተመልከቱ፡ እንዲህ አለ፥

**እግዚአብሔር ኃጢአትን ላደረጉ መላእክት ሳይራራላቸው፡ ወደ ገሃነም… ከ… ከጣላቸው፡ በጨለማ ጉድጓድ ለፍርድ** ሊጠበቁ፡ **አሳልፎ ከሰጣቸው፥**

623 እንግዲያውስ በአንደኛው ጴጥሮስ 3:19 ላይ፡ እንደገና ተመልከቱ፡ ይህ እንዴት እንደሚነበብ ተከታተሉ፥

> **በእርሱም ደግሞ ሄዶ በወኅኒ ለነበሩ ነፍሳት ሰበከላቸው፥**
>
> **የእግዚአብሔር ትዕግሥት በኖኅ ዘመን በቈየ ጊዜ፡ ቀድሞ አልታዘዙም ነበርና፡...** (አያችሁ፡ የዚያን ዘመን መልክተኞች ናቸው፡ መልክተኞች ነበሩ)... **ጥቂቶች... ማለት፡ ስምንት ነፍስ በውኃ የዳኑበት መርከብ፡** ሲዘጋጅ።

624 አሁን ልብ ብላችሁ ከሆነ እነዚያ ግለሰቦች በገነት ነበሩ። አሁን፡ በራዕይ 11 ላይ... ወይም 7 ኛው ምዕራፍ፡ ይመስለኛል... ወይም አይደለም፡ አይደለም፡ 12 ኛው ምዕራፍ ነው። በራሷ ላይ ጨረቃ ወይም ጸሀይም፡ በራሷ ላይ... ወይም፡ ጸሐይ በራሷ ላይ ጨረቃም ከእግሯ በታች የነበረች ሴት ተምሣሌት ይሰጣል። ቀይ ዘንዶውም ሕፃኑን እንደ ተወለደ ሊበላው ቆመ፡ በጅራቱም የሰማይን ከዋክብት ሲሶ ሰቦ ወደ ምድር ጣላቸው። ይህን ልብ ብላችኋል? አሁን፡ ያ ማለት ሰይጣን በሰዎች ላይ የሚጠመጥመው ረ—ረጅም ጅራት አለው ማለት ሳይሆን፡ "**የሚነግራቸው** ተረት" ነው፡ በዚያም ከከዋክብቱ ሲሶ ሳባቸው። እነዚያ ከዋክብት የአብርሃም ዘር ናቸው።

625 አብርሀም እንዲህ አለ፡ "ኦህ... "

626 እግዚአብሔር ለአብርሃም እንዲህ አለው፡ "ወደ ሰማይ ተመልከት፡ ከቻልክ ከዋክብትን ቁጠራቸው።"

627 እርሱም "አልችልም፡" አለ።

628 እንዲህም አለው፡ "እንዲሁም ዘርህንም መቁጠር አይቻልህም፡" ስለ ኮከቦቹ።

629 ብሩህ እና የንጋት ኮከብ ማን ነው? የናዝሬቱ ኢየሱስ፡ በሰው አካል ከተመላለሱት ሁሉ እርሱ ብሩህ ነው። ብሩህ የንጋት ኮከብ እርሱ ነው። እርሱም በይስሐቅ በኩል የመጣ፡ የአብርሃም ዘር ነው። እኛም፡ በክርስቶስ ሞተን፡ የአብርሃምን ዘር ይዘናል እንደ ተሰፋውም ቃል ወራሾች ነን።

630 ስለዚህ የሰማይ ከዋክብት እዚህ የሰውን መንፈስ ተምሣሌት ናቸው። እና ቀዩ ዘንዶ (ሮም፡ በታላቁ መከራ) ሁለት-ሶስተኛውን... ወይም ከዋክብት አንድ ሶስተኛውን ጎትቶ፡ ወደታች ወረወራቸው፡ ያም በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስቅለት ላይ እነሱ አንፈልግህም ባሉት ጊዜ ነበር... እርሱንም ያን ጊዜ ወረወረው በእርሱ ዘንድ እድል ፈንታ የለውም፥ የመላእክቱ ከዋክብት ሲሶው፡ የመላእክት ፍጡራን ነበሩ።

631 አያችሁ፡ በሰውነታችሁ ውስጥ፡ በውስጣችሁ... (በዚያ ጉዳይ ላይ፡ በቀጥታ በተሻለ መልኩ ለመመለስ፡ ሌላ ጥያቄ አለን)። ስለዚህ... ውስጣችሁ ላይ መንፈስ አለ፡ ሌላ ሰው። ውጫዊ አካላችሁ አንድ ሰው ነው፡ ውስጠኛው አካላችሁም ሌላ ሰው ነው። ስለዚህ ውስጠኛው አካላችሁ መለኮታዊ ነው፡ ውጨኛው አካላችሁ ስጋዊ ነው። አያችሁ? እና ይህ አካል፡ በእግዚአብሔር ዘንድ፡ በመንፈስ-የምትመሩ ከሆናችሁ፡ የእግዚአብሔር መልእክተኛ፡ ወይም መልአክ ትሆናላችሁ። የእግዚአብሔር **መልእክተኛ**፡ የእግዚአብሔር **መልአክ**፡

ሁለቱም ተመሳሳይ ቃል ናቸው፡ ልንለያያቸው አንችልም፥ የእግዚአብሔር መልእክተኛ፡ ወይም፡ የእግዚአብሔር መልአክ።

632 እና ከሁሉ የላቀ ስልጣን ያለው የትኛው ነው? ከሰማይ የሚመጣ መልአክ ወይስ የፑልቢት መልአክ? የትኛው ነው? በፑልቢት ላይ ያለው መልአክ! ጳውሎስ እንዲህ አለ፡ "የሰማይ መልአክ መጥቶ እኔ ከሰበክሁት ወንጌል የሚለይ ወንጌል ቢሰብካችሁ፡ የተረገመ ይሁን።" ስለዚህ ይህ መልአክ በመንፈስ ቅዱስ እና በቃሉ የተቀባው ከእግዚአብሔር አጠገብ የሚቆም ነው። ትክክል ነው። በመንግሥተ ሰማያት፡ ሥልጣኑ...

633 "በሰማይና በምድር ሥልጣን ሁሉ ለእኔ ተሰጠኝ። ሂዱ፡ እኔም ከእናንተ ጋር እሄዳለሁ። በምድር የምታስሩት ሁሉ፡ እኔ በሰማይ አስረዋለሁ። በምድር የምትፈቱት ሁሉ፡ በሰማይ እፈታዋለሁ።"

634 ኦህ፡ ታላቂቱ የተቀደሰች ቤተ ክርስቲያን እነዚህን ነገሮች ለማድረግ ሥልጣኗን ባወቀች! ነገር ግን ይህ ይሆንልኝ ይሆን የሚል፡ በጣም ብዙ ጥርጣሬ እና ፍርሃት እና መንቀጥቀጥ አለ፡ "ይህ ሊሆን ይችላልን? " ያ እስካለ ድረስ፡ ቤተክርስቲያን በፍጹም ቀና ማለት አትችልም። እና እያንዳንዱ የፍርሃት ንግግር ሲጠፋ እና መንፈስ ቅዱስ ቤተክርስቲያንን ሙሉ በሙሉ ሲቆጣጠራት፡ ፍርሃት ሁሉ ይወገዳል፡ ያን ጊዜ ቤተ ክርስቲያን ሥልጣን ይኖራታል። አያችሁ? ለምን፡ ሰማያት የያዙት ሁሉ ከበስተጀርባቸው አለላቸው። የዙፋኑ አምባሳደሮች ናቸው። በትክክል! የክርስቶስ አምባሳደር ሥልጣን አለው፡ የክርስቶስም የሆነው ሁሉ የዚያ አምባሳደር ነው። እርሱም "ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ፡ መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ ከወረደ በኋላ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ፡" አላቸው። ምስክር ምንድን ነው? አምባሳደር ነው፡ አንድ ነገር መጥቶ የሚመሰክር ነው። የሰማይ ሥልጣን ሁሉ በእጆቻችሁ ውስጥ ናቸው! ኦህ፡ ለምን እንፈዛለን? ቤተ ክርስቲያንም መካን ናት፡ እኛም ፈዘናል። እነዚህን ነገሮች ስለማናውቃቸው ነው።

635 አሁን፡ በእስር ላይ የነበሩት (ንስሐ ያልገቡ) ነፍሳት፡ በመላእክት ተምሣሌት ከሰማይ የወረዱ—መላእክቶች አልነበሩም፡ ነገር ግን ዓለም ሳይፈጠር በፊት ያኔ ድሮ በሰማይ በተደረገ ሰልፍ፡ የወደቀው የእነዚያ መላዕክት ፍጥረታት መንፈሳቸው ነው። እና ሰይጣን እና—እና ዘንዶው ተዋጋቸው፡ እና ከዚያ... ወይም ሚካኤል እና—እና የ—ዘንዶው (እና ሉሲፈር) ተዋጉ። ሉሲፈርም ከልጆቹ ሁሉ ጋር (ካሳታቸው መላእክቱ ጋር) ተጣለ፡ እነዚያም መላእክት ወደ ምድር መጥተው በዚያን ጊዜ ሰው ለመሆን ተባበሩ። ይህ ሲያደርጉ፡ ያን ጊዜ "የእግዚአብሔርም ልጆች የሰውን ሴቶች ልጆች መልከ መልካም እንደ ሆኑ አይተው፡ ሚስቶችን አገቡ።"

636 የእግዚአብሔር ልጆች ናቸው። በዚህ ምድር ላይ የተወለደ ሰው ሁሉ የእግዚአብሔር ልጅ ነው። ኃጢአተኛ ይሁን ምንም ይሁን ምን፡ የእግዚአብሔር ልጅ ነው። ለእግዚአብሔር ውዳሴ በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠረ ነው፡ በዚያ መንገድ ነው የፈጠረው። እግዚአብሔር ግን ማን እንደሚቀበለውና ማን እንደማይቀበለው አስቀድሞ ያውቃል። ስለዚህ አስቀድሞ የተወሰነ፡ ወይም፡ አስቀድሞ አለመወሰን ይችላል፡ አስቀድሞ በማወቁ ግን ማን እንደሚድን እና

ማን እንደማይድን ሊያውቅ ይችላል። ማን የትኛውን መንፈስ እንደሚቀበል ያውቅ ነበርና።

637 እነዚያም ከእግዚአብሔር ዙፋን ወጥተው፡ በእግዚአብሔር ዙፋን ፊት የቆሙት መናፍስት፡ እና ሊብዙ... ቢልየን እና ቢልየኖች እና ሰፍር ቁጥር ለሌለው ዘመናት ገና ዓለም ሳይጀመር፡ በእግዚአብሄር ህልውና በፊቱ የኖሩ፡ ስለ አምልኮ ምንም የማያውቁ ይመስላችኋልን? እነሱም ወርደው ወዲያው ወደ ሰው ገቡ፡ እግዚአብሔርንም ያመልኩታል! በትክክል፡ እግዚአብሔርን አመለኩ፥ እና ስለ እግዚአብሔር እውቀት አላቸው፡ ሁልጊዜም፡ ብልህ፡ እና አስተዋይ፡ እና የተማሩ ናቸው። እግዚአብሔር ግን ከመጀመሪያው ጥሏቸዋል!

638 ስለዚህ፡ ወዳጄ ሆይ፡ የቤተ ክርስቲያን አባልነት፡ ወ—ወይም የቲኦሎጂ ወይም የሆነ ነገር እውቀት፡ ከእሱ ጋር ምንም ግንኙነት የለውም። እና እንደ አንድ አካል ከእርሱ ጋር የሚገናኛችሁ የኢየሱስ ክርስቶስ ደም እና ዳግም ልደት ብቻ ነው። ይኸው ነው።

639 እግዚአብሔር፡ በመጀመሪያ ይህንን ባወቀ ጊዜ... ወንዶችና ሴቶች አንድ ነበሩ፡ ሁለት አልነበሩም፡ አንድ እንጂ። ተለያዩ፡ አንዱ በሥጋ አንዱም በቲዮፋኒ አኖራቸው። ያንን ያውቃል። ስለዚህ ለእናንተ ይህን ያረጋግጥላችሁ ዘንድ፡ እግዚአብሔር ሴቲቱን በፈጠረ ጊዜ፡ እንደ ወንዱ ከምድር አፈር አላደረጋትም፥ ከአዳም ጎን የጎድን አጥንት ወሰደ፡ እሷም የወንድ ተረፈ-አካል ሆነች (አካሉ ናትና)። አሁንስ ገባችሁ? አያችሁ? ይኸው።

640 መላእክት አሉ። እግዚአብሔርም ከእግዚአብሔርም ጋር የሚዋሐደው ያ መንፈስ አንድ መንፈስ ነው። እውነት ነው። ስለዚህ፡ በቤተክርስቲያን ውስጥ የሚኖረው የእግዚአብሔር መንፈስ፡ ከሰማይ የመጣው መንፈስ ነው፡ ይህም እግዚአብሔር ዓለም ሳይፈጠር በፊት፡ ያወቀው የዲያብሎስን ውሸት የካደ ነው። እናም ያ መንፈስ... ለመፈተን የሥጋ አካልን መልበስ ነበረበት። እንደሌሎቹ ሥጋ መሆን ነበረበት፡ ሁሉም ተመሳሳይ ቀንበር ተሸክመዋል። እግዚአብሔርም፡ ከጥንት ጀምሮ፡ የትኞቹን መናፍስት እንደሚቀበሉ፡ እና እንደማይቀበሉ ያውቃል። ይኸው። ዲያቢሎስ በጣም ብልህ ስለሆነ፡ ከተቻለው የተመረጡትን እንኳን ያታልላል።

641 ስለዚህ እነዚህ መናፍስት፡ እነዚህ የሰበኩ መላእክቶች፡ በእስር ነበሩ፥ angels፡ መላእክቶች እዚህ ጋር ልብ በሉ፡ ትንሽ ሆሄ "a" ነው። ትርጉሙም "ሰው" ማለት ነው፥ መላእክቶች፣ መልእክተኞች በምድር ላይ። ኃጢአት ሠርተዋል፡ እና ኃጢአት ሊሠሩ የሚችሉበትት ብቸኛው መንገድ በአለማመን ነበር! አደራረጋጀውም... የራሳቸው ሃይማኖት ነበራቸው፡ እና የኖህን መልእክት አላመኑም። የሄኖክን መልእክት አላመኑም። መጽሐፍ ቅዱስ መልእክታቸውን አልተቀበሉም፡ "እንዲሁም ተኮንነዋል፡" ይላል።

642 ሄኖክም፡ "ጌታ ከእእላፋት ቅዱሳኑ ጋር ይመጣል፡" በማለት ተነበየላቸው።

643 ትንቢትም ተናገሩ። ኖኅም መርከብ ሠራ፡ እነርሱም፡ "እርሱ ሆሊ-ሮለር ነው! እሱ አክራሪ ነው! ዝናብ ይዘንባል የሚባለው ነገር ውሸት ነው።" መቶ ሃያ ዓመታት አለፉ፡ እናም መዳን ያዘለች ሃይማኖት ነበረችው፡ የማምለጫ መንገድ ተዘጋጅቶላቸው ነበር፡ ይሁን እንጂ በራሳቸው መንገድ ረኩ።

644 ዛሬ እንዲህ ነው፡ ሰዎች በራሳቸውን ሁኔታ ረክተዋል። ነገር ግን የማምለጫ መንገድ አለ፡ መንገዱም በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ነው። ኣሜን። ይኸው፥ አንድ አይነት ኀሳ፡ አንድ አይነት መናፍስት።

645 ፍጹም ሃይማኖተኛ ሰዎች፡ በጣም ሃይማኖተኛ ነበሩ፡ ነገር ግን የቃል ኪዳኑን ስእለት አላገኙትም።

646 ዛሬም እንዲሁ ነው። ሰው ወደ ቤተ ክርስቲያን ሄዶ፡ ትልልቅ አብያተ ክርስቲያናትን ተቀላቅሎ፡ በከተማው ውስጥ በጣም ተወዳጅ ሰው ለመሆን ይሞክራል። ወደ ቤት ክርስቲያን መቀላቀል ከፈለጉ፡ በከተማው ውስጥ ትልቁን፡ በከተማው ውስጥ ጥሩውን እና በደንብ-ታዋቂ-የሆነውን ይፈልጋሉ። ጥሪያቸው እንዴት ሳቱት! ምን ያህል ሳቱት!

647 ኢየሱስ ክርስቶስን ማወቅ የምትችለው በመንፈሳዊ መገለጥ ነው እንጂ፡ በሥነ መለኮት ወይም መጽሐፍ ቅዱስን ምን ያህል እንደምታጠና አይደለም። የክርስቲያን ሳይንስ፣ ሜቶዲስት፣ የይሖዋ ምሥክር፣ ወይም ምንም ይሁን ምን፥ ምንም ብትሆኑ፡ በቃል በፍጹም አታውቁትም፡ እርሱን በሚገልጥላችሁ በእግዚአብሔር መንፈስ ነው እንጂ። በመንፈሳዊ መገለጥ ነው!

648 አዳም፡ እና ሔዋን፡ በኤደን ገነት፡ እነዚያ ልጆች በተባረሩ ጊዜ፡ ያኔ ቃየን በጥሩ ሥነመለኮት ተገለጠ። እንዲህ አለ፡ “እኛ እዚህ የምናደርገውን ነገር በሙሉ—ልቤ እንደማደርገው እግዚአብሔር ያውቃል። ግሩም መሠዊያ እሠራለሁ፡ በላዩ ላይ አበባዎችን አደርጋለሁ፡ በላዩ ላይ ፍራፍሬ አደርግበታለሁ፡ እሰውበዋለሁ። በእርግጥ በዚህ እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት እና ልቤ ቅን መሆኑን እንዲያውቅ ማድረግ እችላለሁ።” ስለ ቃሉ ትክክል ነበር፥ እግዚአብሔር አምልኮን ይፈልጋል፡ ወደ ማምለክ ሄደ። ድንቅ የሆነ የአምልኮ ቦታ፡ ያማረ ትልቅ ካቴድራል፡ (ዛሬ እንደሚሉት) ሠራ። አስተካክሎ በትክክል ሠራው፡ በውስጡም መሠዊያ አኖረ፥ እርሱ ከሓዲ አልነበረም።

649 አቤል ግን፡ በእግዚአብሔር ቃል ላይ በመታመን... በዚያን ጊዜ የተጻፈ መጽሐፍ ቅዱስ አልነበረም፡ ነገር ግን እግዚአብሔር ከኤደን ገነት የወጣነው በፍሬ ምክንያት እንዳልሆነ **ገለጠለት**፡ አዳምና ሔዋን የበሉት ፖም አይደለም፡ የለያቸው እና ያቆራረጣቸው ፍፁም ፆታዊ ግንኙነት ነው። ሟቾች እንደ ሆኑና፡ ይህንንም የጀመረው በአዳም ደም፡ ማለቴ በእባቡ ደም መሆኑን አውቆ፡ አቤል፡ በመለኮታዊ መገለጥ፡ ሄዶ በግ ወስዶ አቀረበው። እግዚአብሔርም “ይኸው ነው፡” አለ! በትክክል።

650 ከተአምራዊው ተራራ በወረዱ ጊዜ፡ ኢየሱስ “ሰዎች የሰውን ልጅ ማን ይሉታል፡” አላቸው?

651 “አንዳንዶች ‘ሙሴ’ ነህ ይላሉ፡ ሌሎችም ‘ኤልያስ፡’ ሌሎችም ‘ኤርምያስ’ ነህ ይላሉ፡ ሌሎችም ‘ያ ነቢይ’ ነህ ይላሉ።”

652 እርሱም፡ “እናንተስ እኔ ማን እንደ ሆንሁ ትላላችሁ? ”

653 ጴጥሮስም፡ “አንተ ክርስቶስ፡ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ” አለ።

654 “የዮና-ልጅ ስምዖን ሆይ፥ ብፁዕ ነህ፡ ሥጋና ደም ይህን አልገለጠልህምና፡” አለው። (ተከታተሉኝ!) “በደብዳቤ አይደለም፡ በትምህርት ቤትም አይደለም፥ በሴሚናር ውስጥ አልተማርከውም፡ ማንም አልነገረህም። ሥጋና ደም ይህን

አልገለጹልህም፡ ነገር ግን በሰማያት ያለው አባቴ ገልጦልሃል። በዚችም ዓለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ፡ የገሃነም ደጆችም አይችሏትም።" ይኸው። ይህች የሕያው እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ናት። ያ ነው። በዚህች ቤተ ክርስቲያን ላይ... ይህች ቤተ ክርስቲያን የተሠራችው፡ በዚህ **መገለጥ** ላይ ነው። ይህ መለኮታዊ መገለጥ ነው፡ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ገልጦታል፡ እናንተም እንደ ግል አዳኛችሁ ተቀበላችሁት፡ ከሞት ወደ ሕይወት ተሻገራችሁ።

655 መንፈስ ቅዱስም ይሰራል በዚህ አካል ብልቶች ውስጥ እየሰራ ነው። ቤተክርስቲያን ይህች ናት! ድሃ ብትሆን፡ ተልእኮ ላይ ብትሆንም፡ የሆነ ቦታ ጥድ ስር ብትቆሙ፡ ወይም የትም ቦታ ምንም ለውጥ አያመጣም፡ በግል ስብሰባ ላይ በአንድ ሰው ቤት ውስጥም ይሁን፡ ምንም ለውጥ የለውም። እግዚአብሔርን ውበት እና እነዚህ ነገሮች አይሰቡትም። ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ግል አዳኛችን የእግዚአብሔር ልጅ ሆኖ የቀረበበት፡ የልብ ቅንነት መገለጥ ነው። አሜን!

656 አቤት፡ እ... እንዲህ ከቀጠልን፡ ወደ መጨረሻው አንደርስም፡ አይደል?

657 ወደዚያ የሄደላቸው... እነዚህ ናቸው፥ መላእክቱ፥ መልእክተኞቹ፡ እነዚህ ሰባኪዎች፡ እነዚህ ምሁራን፡ እነዚህ መልእክተኞች ኖኅ ሄዶ ሲሰብክላቸው ያላመኑት መልእክተኞች፡ "ሂዱ፡ ወደዚህ መርከብ ግቡ" አላቸው።

658 እንዲህም አሉ፡ "ይህን ሆሊ-ሮለርን ሰሙት። ይህን አክራሪ ሰሙት። ለምን፡ ዝናም አይዘንብም። እንደዚህ ያለ ነገር ማን ሰምቶ ያውቃል? ለምን፡ አቤት፡ እኛ ቤተ ክርስቲያን የለንምን? ሃይማኖተኛ አይደለንምን?" አዎን፡ ሃይማኖተኛ ነበሩ!

659 ኢየሱስ በዚያን ጊዜ ያለፈው ትውልድ፡ ያ ትውልድ ገና ከመምጣቱ በፊት እንደሚነሳ ተናግሯል፡ "በኖኅ ዘመን እንደ ነበረ፡ በሰው ልጅ መምጣት እንዲሁ ይሆናል። ይበሉም፡ ይጠጡም፡ ያገቡም፡ ይጋቡም ነበር።" በዚያን ጊዜ፡ አካባቢ የሆነ ቦታ ሬኖ፡ ኔቫዳ ነበራቸው። ዛሬ እንዳለን አይነት ከንቱ ነገር ሁሉ ነበራቸው፥ ፌዝ፡ ሳቅ፡ መሳቂያ፡ መሳለቂያ እና ሁሉም ነገር፥ የአምልኮት መልክ አላቸው፡ ነገር ግን እውነተኛውን እውነት ክደዋል፥ የጸጋውን መልእክት፡ ቃል ኪዳን ነው። እግዚአብሔር መንገዱን ራሱ አዘጋጅቶ፡ ህዝቡ የሚያመልጡበትን መንገድ የእርሱን—ቃል ኪዳን ሰጥቷቸዋል፥ በእርሷ መዳን ነበረ፥ መዳን ሰው የሚያመልጥበት ቦታ ነበር።

660 "ከመዳን በቀር ምን ያስፈልገናል?" ዛሬ ሰዎች እንዲህ ይላሉ፡ "የምንኖረው በመልካም ዲሞክራሲያዊ የመንግስት መዋቅር ስር አይደለምን? ምን ያስፈልገናል?"

661 በጣም ዲሞክራሲያዊ በሆነ ሰርአት ብንኖር ግድ የለኝም፡ የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ያስፈልገናል። እውነት ነው! ክርስቶስ እንፈልጋለን። ዴሞክራሲያዊ ሰርዓቱን አደንቃለሁ፥ ያ ከነፍስ መዳን ጋር ምንም ግንኙነት የለውም። በፍፁም! እነዚህ መንግስታት ያልፋሉ፡ እና ሁሉም ህዝብ ያልፋል። እኔ ራሴ በቅርብ ጊዜ... ፈርዖኖች የቆሙበት ሰፍራ ቆሜአለሁ፡ እና የተቀመጡባቸውን ዙፋኖች ለማግኘት ሃያ ጫማ ጥልቀት መቆፈር አለባችሁ። ፈርዖኖች እና የዚህ ምድር መንግስታት ሁሉ፡ እና ከእነሱ ጋር የተያያዙት የሚያልፉ ነገሮች ሁሉ ይወድቃሉ፡ ያሕዌ ግን ለዘላለም ይነግሣል፡ እርሱ

የማይሞት አምላክ ነውና። በዓለቱ በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ጸንተናል፡ ሌላው መሬት ሁሉ እንደሚሰምጥ አሸዋ ነው።

662 ግድ አይሰጠኝም... መንግስታት ይነሳሉ፡ ይወድቃሉም፡ ምንም ቢሆን ግን፡ ኦህ፡ አያስጨንቀኝም ምንም ቢሆን፡ ያለም ቢሆን፡ የሚመጣም ቢሆን፡ ምንም (ረሃብ ወይም ስጋት ወይም ምንም ነገር) በክርስቶስ ካለው ከዚህ ከእግዚአብሔር ፍቅር ሊለየን አይችልም። ሰው በእግዚአብሔር መንፈስ ሲወለድ፡ የጊዜ ፍጡር ሳይሆን፡ የዘላለም ፍጥረት ነው። ኣሜን። ከሞት ወደ ሕይወት ተሻገረ። ከዚህ ወጥቶ... ከዘመን ቆጠራ ወጥቶ፡ ወደ ዘላለማዊነት ተሻገረ። ፈጽሞ ሊጠፋ አይችልም! እግዚአብሔርም በመጨረሻው ቀን እንደሚያስነሣው ማለ።

663 ስለዚህ ትልልቅ ኣብያተ ክርስትያኖቻችሁ ሁሉ፡ እና ታላላቅ ጊዜአቶቻችሁ ሁሉ ይኑራቸው፡ የፈለጋችሁትን ሁሉ፡ እና ክፉ ቀልዶቻችሁን ንገሩ እና የሎቶ ጨዋታዎችን፡ እና የሾርባ እራትን እና የፈለጋችሁትን አርጉ፥ እናም የተማረ ሰባኪም ይኑራችሁ። ምናልባት እሱም ከእነዚህ ሀሁን እምብዛም ከማያውቁት ከእነዚህ ወጣቶች የተሻለ ሥራ ሊሰራ ይችላል። ነገር ግን እውነት እላችኋለሁ፡ ሀሁን የማያውቅ (ክርስቶስን የሚያውቅ) ወጣት ቢሰብከኝ ይሻለኛል አለ የተባለ ትምህርት ካላቸው ታላላቅ የሥነ መለኮት ሊቃውንት ሁሉ ይልቅ እሱ ይሻለኛል። በትክክል!

664 ከቅርብ ጊዜ በፊት፡ እዚህ ኬንታኪ ውስጥ፡ የራሱን ስም እንኳን ማንበብ የማይችል አንድ ወጣት፡ ጌታ እንዲሰብክ ጠርቶኛል ብሎ ትምህርት ቤት አዳራሽ ጠየቀ። ለምን፡ ባለሥልጣኖቹ ይህ እንዲያደርግ አልፈቅዱለትም። ከዚያ ሰሙ **እንዲህ** የተጻፈበት ከዘራ የያዘ አንድ ታላቅ ሰባኪ መጣ፡ ታላቅ የሰነመለኮት ዶክተር፡ እንዴታ፡ ትምህርት ቤቱን ለእርሱ ፈቀዱለት። አዎን። የሁለት ሳምንት ተከታታይ የመነቃቃት ሰብሰባዎችን አደረገ፡ አንድም ነፍስ አልተገኘም። ከዚያ አባቱ ወደዚያ ሄደና፡ እርሱም፡ “አሁን ፍቀዱለት፡ እኔ ግብር ከፋይ ነኝ፡ ስለዚህ ልጄ እንዲፈቀድለት የመጠየቅ መብት አለኝ። ልጄም ሊፈቀድለት ይገባል” አላቸው።

665 በድጋሚ ሄዶ፡ ጠየቃቸው፡ እነርሱም “እሺ፡ ቢያንስ ለሁለት ሌሊት እንዲሰጠው እንፈቅድለታለን፡” አሉ። በመቀጠል ለሁለት ምሽቶች ፈቀዱለት።

666 እና በዚያ ምሽት ይህ ወጣት ወደዚያ ወጣ መጽሐፍ ቅዱስ ማንበብ እንኳ አልቻለም፡ ሌላ ሰው ጽሑፉን እንዲያነብለት ጠየቀ። ወደ መድረክ ሲወጣ ግን፡ በመንፈስ ቅዱስ ተቀባ። ሲሰብክም ሀያ የሚያህሉ ሰዎች፡ ወደ መሠዊያው መጡ፥ በዚያም በመሠዊያው አጠገብ፡ ይህች አስመሳይ-ሰባኪ ሴት እያለቀሰች ወደ ቀራንዮ ሄደች።

667 እውነት ነው፡ ወንድሜ፡ ምን ታውቃለህ ሳ—ሳይሆን፡ ማንን ታውቃለህ ነው። ያ ነው ሃሳቡ፡ ያ ነው የሚያስፈልገው፡ ክርስቶስን ማወቅ ያስፈልጋል። እርሱን ማወቅ፡ ሕይወት ነው፥ እሱን አለመቀበል፡ ሞት ነው።

668 በፍጥነት ወደ ሌሎች ጥያቄዎቻችን፡ በመቀጠል ወደ ጆርጂያ የሚወርዱ ጥያቄዎች ናቸው፥

**67. በራእይ 21፡19 እና 20 ውስጥ ያሉት... ድንጋዮች ምንን ያመለክታሉ?**

669 ጊዜ ወሰዳችሁ መጽሐፍ ቅዱስህን ለመክፈት ከፈለጋችሁ፡ ለአሁን ብዙ ጊዜ የለንም፡ ነገር ግን ቶሎ መልስ ለመስጠት እሞክራለሁ። ራዕይ ሀያ-... 21፡ 19 እና 20 ይመስለኛል። አዎን።

670 በጣም ጥሩ፡ በህንጻው ላይ ስለነበሩት ድንጋዮች ሲናገር ታያላችሁ። ድንጋዮቹም መሠረት ነበሩ። ካስተዋልክ... ወንድም ኔቪል፡ አንተ ጋር እንደከፈትክ አምናለሁ። እያንዳንዱ ድንጋይም ሁሉ መሠረት ነበር። መሠረቱ አንድ ድንጋይ ብቻ አልነበረም፡ ሌሎቹም... እያንዳንዱ ድንጋይ ግን መሠረት ነበር። እያንዳንዱ ድንጋይ ቋሚ መሠረት ነበር። በዚያም አሥራ ሁለት ድንጋዮች ነበሩ። እነዚህን አሥራ ሁለቱን ድንጋዮች ካስተዋላችሁ፡ እያንዳንዳቸው... መጀመሪያ በኢያስጲድ ይጀምራል፡ እና ሰርዶኒክስ፡ ወዘተ ነበር፡ የእያንዳንዱ ድንጋይ ተመሣሌት።

671 በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እነዚህ ድንጋዮች የተወሰኑ ሰሞች እንደነበራቸው ታያላችሁ። ጥቂቶቹ ትንሽ ይለያሉ፡ ስለነሱ ሰምታችሁ አታውቁም። መዝገበ ቃላቱን ብትመረምሩት፡ ሰሙ ብቻ ነው የተቀየረው እንጂ፥ ያው ድንጋይ ነው።

672 ግን የሚጀምረው—በኢያስጲድ ነው። ኢያስጲድ የ—የብንያም ድንጋይ፡ ወይም፡ የሮቤል፡ ኦህ፡ የበኩሩ ልጅ ድ... ድንጋይ ነበር። የመጀመሪያው ድንጋይ ሮቤል ነበር፡ እርሱም ኢያስጲድ ነበር። የመጨረሻው ድንጋይ፡ የመጨረሻው የላይኛው ድንጋይ ብንያም ነበር።

673 አሁን፡ ለመሠረት የተቀመጡት እነዚህ ዐሥራ ሁለቱ ድንጋዮች፡ እ— እነዚህ አሥራ ሁለቱ ድንጋዮች በአሮን በደረት ኪስ ላይ ተሰቅለው ነበር። እነርሱም—እርሱ የነዚሁ ነገዶች፡ ሊቀ ካህናት እንደነበረ—ተምሣሌት ናቸው። እያንዳንዱ የትውልድ ድንጋያቸው በዚህ—በዚህ የደረት ኪስ ውስጥ፡ ተቀምጠዋል። ሕዝቡም ይህን የደረት ኪስ ባዩ ጊዜ፡ በአሮን ደረት ኪስ ያሉትን የልደት ድንጋዮችን ሲመለከቱ፡ የዚህ ነገድ ሁሉ ሊቀ ካህናት መሆኑን ያውቃሉ።

674 አሁን ዛሬ ማለዳ በወንድም ኔቪል መልእክት፡ እንደሰማነው ነው። ብዙ ጊዜ ኡሪም ቱሚምን ያመጣሉ። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀሰውን መልእክታቸው ትክክል እንደሆነ ወይም እንዳልሆነ የሚያውቁበት መንገድ እንደሆነ ተጠቅሶ ታያላችሁ። እነዚህ ድንጋዮች፡ ይህ ሰው የተናገረው በፈጸመ ጊዜ፡ ነቢዩ ትንቢት ይናገራል፡ እነዚህ ድንጋዮች በአንድነት ያበራሉ። እንዲያንጸባርቁ የሚያደርጋቸው ህብረ ቀለማት ይፈጠራል ከሳፋየር፡ እና ከኢያስጲድ፡ ከካርቡንክል፡ እና ሌሎች ድንጋዮች ብርሃናቸውን ያንጸባርቃሉ፡ ትልቅና ድንቅ የሆነ የቀስተ ደመና ህብረ ቀለም ይሰራሉ ነገሩን ሁሉ በአንድነት ይዋሃዳል።

675 አሁን፡ አሁን፡ ዛሬ፡ ይህ ኡሪም ቱሚም ከዚያ ክህነት ጋር በተመሳሳይ ጊዜ ስለተወገደ፡ አሁን ዛሬ የእግዚአብሔር ኡሪም ቱሚም የሆነው ይህ መጽሐፍ ቅዱስ ነው። እናም አንድ ሰባኪ ሲሰብክ፡ ተሰፋውን ሁሉ የሚያደርግበት፡ ትንሽ ክፍል ብቻ መሆን የለበትም፥ መላው መጽሐፍ ቅዱስ ይህ ሰው እየሰበከ ያለውን መልእክት የሚያንጸባርቅ መሆን አለበት። የሚያስፈልገው ይህ ነው። አንድ ክፍል ብቻ ሳይሆን፡ "እሺ፡ መጽሐፍ ቅዱስ **እንዲህ** ይላል" ይላሉ። አረ፡ አዎን፡ ብዙ ነገርም ይናገራል። ነገር ግን ሁሉም ህብረ ቀለም እንዲፈጠሩ በሚያስችል መንገድ ማቅረብ አለባችሁ። የእግዚአብሔርም መንፈስ መጥቶ

ወደ—ቃሉ ሲገባ፡ እነዚህን ሁሉ አንድ ላይ አድርጎ አንድ ትልቅ ብርሃን ያንጸባርቃል፡ ያ ብርሃን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ኣሜን።

676 አሁን፡ እነዚህም አሥራ ሁለቱ ድንጋዮች ከሮቤል የተጀመሩ አሥራ ሁለት መሠረቶች ነበሩ፡ እነ ጋድ፡ እስከ ብንያም ድረስ፥ አሥራ ሁለት ነገዶች፡ አሥራ ሁለት ድንጋዮች። እነዚያም በቤተ መቅደሱ ውስጥ፡ በአዲሲቷ ሰማያዊት ኢየሩሳሌም ውስጥ ያሉት ድንጋዮችም፡ እያንዳንዱ መሠረት በእያንዳንዳቸው አባቶች ስም ይጣላል።

677 እንግዲህ ተመልከቱ፡ እነዚህን ድንጋዮች አስተውሉ፡ አሁን በሚቀጥለው ጥያቄ ውስጥ፡ እነዚህ አባቶች በሌላ ነገር ሲንጸባረቁ ታዩአቸዋላችሁ።

## 68. ይብራራልን—አራተኛውን... የራዕይ 5 አራቱን አራዊት አስረዳን።

678 ወንድም ኔቪል፡ አንተ ቀድመህ ከሆነ እስኪ፡ ወይም አንዳችሁ፡ የዮሐንስ ራዕይ 5 ላይ፡ ይህንን ለአንድ ደቂቃ ያህል እናነባለን። የ—የሚያምር ተምሣሌት ነው... እንዲህ ይላል፡ እኔ ራሴ ከፍቼአለሁ፡ የዮሐንስ ራዕይ ምዕራፍ 5፥

> በ—በ**ዙፋኑ ላይ በተቀመጠው በቀኝ እጁ ላይ** በውጭ **በውስጥና እ—እ—እና በኋላ የተጻፈበት፡ በሰባትም ማኅተም የተዘጋ መጽሐፍን አየሁ።**
>
> **እናም...**

679 እንግዲህ፡ ቦታው ይህ አይደለም። ትንሽ ወደ ፊት፡ አራቱን እንስሳት ማየት እፈልጋለሁ። እስቲ እንያቸው፡ ቁጥር 14። እሺ፡ ወዳጄ። አሁን እንቀጥል፡ ያ ነው። አሁን እዚህ በ—በቁጥር 12 እንጀምር፡ አይደለም፡ ይመስለኛል... "አራቱም አራዊት 'አሜን፡' አሉ፡" አይደለም፡ ከዚያ በፊት ትንሽ ወደ ኋላ፡ ወንድም ኔቪል። "እነሆ፡ ድምጽ ሰማሁ... "

680 እስቲ እንየው፡ አንድ ደቂቃ ብቻ፡ ከትንሽ ጊዜ በፊት እያነበብኩት ነበር። ኦህ፡ አገኘሁት፡ በ 6ኛው ቁጥር እንጀምር። 5ኛው ቁጥር፦

> **ከሽማግሌዎቹም** አንዱ፡ **አታልቅስ፥ እነሆ፡ ከይሁዳ ነገድ የሆነ አንበሳ፡ እርሱም የዳዊት ሥር፡ መጽሐፉን ይዘረጋ ዘንድ፡ ሰባቱንም ማኅተም... ይፈታ ዘንድ ድል ነሥቶአል አለኝ።**
>
> **አየሁም፡ እና፡... በዙፋኑና፡ በአራቱ እንስሶች መካከልም፡ በሽማግሌዎችም... መካከል፡ እንደ ታረደ በግ፡ ቆሞ አየሁ፡ ሰባትም** ራሶች **እና ሰባት ዓይኖች ነበሩት፡ እነርሱም** ወደ... **ምድር ሁሉ የተላኩ የእግዚአብሔር... ሰባቱ መናፍስት ናቸው።**

681 ይህንን ጥያቄ እንድታስታውሱት እወዳለሁ፡ እና ወደ እሱ ካልተመለስኩኝ፡ እንድታስታውሱኝ እፈልጋለሁ፡ በዚህ ጉዳይ ላይ ልናገር፡ "በበጉ ዘንድ ስለነበሩ ሰባቱ መናፍስት ሰባቱ አይኖች።" ኦህ፡ ያ በጣም ቆንጆ ነገር ነው። (እሺ፡ ወደዚህ ወንድም ጥያቄ አሁን መግባት እንፈልጋለን።) በጣም ጥሩ፡ አሁን ያንን እንዳትረሱ።

> **መጥቶም በዙፋን ላይ** ከተቀመጠ **ከዚያ ከቀኝ እጁ መጽሐፉን ወሰደው።**

**መጽሐፉንም በወሰደ ጊዜ፡ አራቱ እንስሶችና ሀያ አራቱ ሽማግሌዎች በበጉ ፊት ወደቁ፡... እያንዳንዳቸውም በገናንና፡...**

682 አሁን፡ ካስተዋላችሁ፡ አ—አራቱ—አራቱ እንስሳት እነዚህ ናቸው። አሁን እንቀጥልና ትንሽ ወደፊት እናንብብ፦

... **የቅዱሳን ጸሎት** የሆነ፡... **ዕጣን የሞላበትን፡...** የወርቅ ዕቃ **ያዙ።**

**የተገባህ ነህ እያሉ፡... አዲስ መዝሙርም** ዘመሩ... (እነርሱም አምልኳቸውን ሁሉ... ለጌታ ማቅረባቸውን ቀጠሉ)

683 አሁን፡ እነዚህ አራት የራእይ እንስሳት፡ ከተመለከቷቸው፡ በእያንዳንዱ ምንባብ ላይ... (እናንተ መጽሐፍ ቅዱስን የምታነቡ፡ እንዲሁም ይህንን ቀረጻ የምታዳምጡ ሰዎች)። እነዚህ አራት እንስሶች፡ አራት ፊት ነበሯቸው፥ አንዱ የሰው ፊት ነበረው፡ ሁለተኛው የበሬ ፊት ነበረው፡ ሌላኛውም የንስር ፊት ነበረው፡ ሌላኛውም የአንበሳ ፊት ነበረው። እና ወደ ኋላ ፈጽመው አይሄዱም ነበር፡ ወደ ኋላ መሄድ አይችሉም።

684 ጥንታዊውን የራዕይ መጽሐፍ ከአመታት በፊት ስንማረው፡ የራዕይ መጽሐፍ ሁለት ዓመት ያህል ሲፈጅብኝ ሰንቶች ታስታውሳላችሁ? ከንጋፋዎቹ-መካከል ብዙዎች አሉ።

685 ተመልከቱ፡ ወደ ኋላ አይሄዱም፡ ምክንያቱም የትም ቢሄዱ ወደ ፊት ይሄዱ ነበር። **በዚህ** መንገድ ከሄዱ፡ እንደ ሰው ይሄዱ ነበር፡ **በዚህ** መንገድ ከሄዱ፡ እንደ አንበሳ ይሄዱ ነበር፥ **በዚህ** መንገድ ከሄዱ፡ እንደ ንስር ይሄዱ ነበር፥ **በዚህ** መንገድ ከሄዱ፡ እንደ በሬ ይሄዱ ነበር። አያችሁ፡ ወደ ኋላ መሄድ አይችሉም፡ ሁል ጊዜ ወደፊት ይራመዳሉ።

686 እንግዲህ እነዚህ አራት እንስሳት። አሁን ይህን በፍጥነት ለመረዳት፡ ምክንያቱም ብዙ ላቆየው አልፈልግም። አራቱ እንስሳት ግን... በመጽሐፍ ቅዱስ፡ **እንስሳ**፡ የ "ኃይል" ተምሣሌት ነው። እና አስተውሉ እነዚህ እንስሳት እዚያ በኩሬ ውስጥ ወይም በአንድ ቦታ ውስጥ በባህር ውስጥ አልነበሩም፡ ነገር ግን በእግዚአብሔር ዙፋን ፊት ነበሩ፡ እግዚአብሔርንም ያመልኩ ነበር። እነዚህ አራት እንስሳት ከምድር የሚነሱትን አራት ኃይላት ያመለክታሉ፡ እና እነዚህ አራቱ ኃይላት አራቱ ወንጌሎች ነበሩ፥ ማቴዎስ፡ ማርቆስ፡ ሉቃስ፡ እና ዮሐንስ፥ እርስ በርሳቸው አይቃረኑም።

687 ከመካከላቸው አንዱ፡ ይህ... ወንጌል እንደ አንበሳ ሲወጣ፡ ጠንከር ያለ፡ ደፋር መሆኑ ነው፥ ወንጌል እንደ አንበሳ ደፋር ነው፡ እንደ አንበሳም ንጉሥ ነው። እንደ ሰው ፊት ሲሄድ፡ እንደ ሰው ብልጥ እና ብልሃተኛ ነው። እንደ ንስር ሲሄድ፡ ፈጣን እና እና ከፍተኛ ደረጃ የሚበርር መሆኑ ነው። ም... ምን ለማለት እንደፈለግኩ አያችሁ? እንደ በሬው ሲሄድ፡ ይህ መጎተት የሚችል ፈረስ፡ ማለቴ የ—የ—የወንጌልን ሸክም መጎተት፡ የበሬ ስራ ነው። አራቱ እንስሳት አራቱ ኃይላት ናቸው፡ እነርሱም፦ ማቴዎስ፡ ማርቆስ፡ ሉቃስ፡ እና ዮሐንስ፥ በእግዚአብሔር ፊት የሚሰሙት አራቱ ወንጌላት ናቸው። ያም...

688 ካስተዋላችሁ፡ ከፊትና ከኋላ ዓይኖች ነበሯቸው። እነሱ—እነሱ... በሄደበት ሁሉ፡ ያንጸባርቃል። የሚሄዱበትን ቦታ ሁሉ ያያል። እና በወጣ ቁጥር

ይህ የወንጌል ኃይል ነው፡ ይህም... የሰው ብልሃት አለው፥ የንስር ፍጥነት አለው፥ ኃይል አለው፡ የ—የ—የመጎተት ኃይል አለው፡ እንደ በሬ፡ ሸክም-ተሸካሚ ነው፥ እንደ አንበሳም—ጽናት እና ድፍረት አለው። እያችሁ፡ አራት ወንጌል ናቸው፡ እነሱም የራእይ፡ የአራተኛው ምዕራፍ ኃይላት ናቸው።

በጣም ጥሩ፡ በመቀጠል፦

**69. ሃያ አራቱ ሽማግሌዎች እነማን ናቸው?** እሺ፡ እንዲህ ይሆናል ብዬ አምናለሁ ሃ—ሃ... **ሃያ-አራቱ ሽማግሌዎች እነማን ናቸው?**

689 አሁን በጣም ቀላል ነው፡ ያንን መግባት እንችላለን። ሃያ-አራቱ ሽማግሌዎች በዙፋኑ ፊት ተቀምጠዋል። ያም... በቁጥር 4 ላይ የሚገኝ፡ ይመስለኛል። “እና ሌላ ወጣ... ” እስኪ... እንየው፡ እ... 4:10 ላይ።

690 እሺ፡ ራዕይ፡ ምዕራፍ 4 ላይ፡ ከቁጥር 10 ይህ ነው። ትክክል። እንቀጥላለን።

> **ሀያ አራቱ ሽማግሌዎች በዙፋኑ ላይ** በተቀመጠው **ፊት** ወድቀው፡ **ከዘላለም እስከ ዘላለም በሕይወት ለሚኖረው** እየሰገዱ፡ **ጌታችንና አምላካችን ሆይ፡**
>
> **አንተ፡ ሁሉን ፈጥረሃልና፡ ስለ ፈቃድህም ሆነዋልና ተፈጥረውማልና፥ ክብር ውዳሴ ኃይልም ልትቀበል ይገባሃል እያሉ፡ በዙፋኑ ፊት አክሊላቸውን ያኖራሉ።**

691 አሁን ሃያ አራቱ ሽማግሌዎች። ሽማግሌ የበላይ ተመልካች ነው። እንግዲህ እናስተውል፡ አሥራ ሁለት አባቶች እና አሥራ ሁለት ሐዋርያት ነበሩ። በአንድ ወገን አሥራ ሁለት፡ በዚያም አሥራ ሁለት ሆነው ተቀምጠው ነበር። ሃያ አራቱ ሽማግሌዎች ነበሩ፡ በአንድ በኩል ብሉይ ኪዳን፡ አሥራ ሁለቱ አባቶች የነበሩ፡ አሥራ ሁለቱ ሐዋርያት በሌላ በኩል፡ የአዲስ ኪዳን ነበሩ። ኢየሱስ፡ “በአሥራ ሁለቱ የእስራኤል ነገድ ላይ ስትፈርዱ በአሥራ ሁለት ዙፋኖች ላይ ትቀመጣላችሁ፡” አላለምን?

692 አሁን፡ መሠረቶች ናቸው። ተመልከቱ፡ በዚያ ውስጥ አንድ ዛፍ አለ። በሁለቱም ጎን በኩል ዛፉ አሥራ ሁለት ፍሬ ያፈራል። ፍሬያቸውንም በወር አንድ ጊዜ ይሰጣሉ፡ ይህም በዓመት አሥራ ሁለት ወር ነው። በየአመቱ አስራ ሁለት አይነት ፍራፍሬዎችን ሲያቀርቡ ይሰጣሉ። **አስራ ሁለት** የ “አምልኮ” ቁጥር ነው፡ እያችሁ። እና ሀያ አራት ነበሩ፡ ሀያ-አራት ናቸው፡ አስራ ሁለት ሐዋርያት እና አስራ ሁለት አባቶች ይሆናሉ። በዙፋኑ ላይ ተቀምጠዋል።

693 እሺ፡ አሁን 4ኛው ቁጥር፡ ወይም፡ አራተኛው ጥያቄ፦

**70. በዘፍጥረት 38 ላይ ያለው ቀይ ክር ምንን ያመለክታል?**

694 ቀዩ ክር፡ ልብ በሉ፡ ይሁዳ ነበር። ለእርሱም ወንዶች ልጆች ነበሩት፡ ከልጆቹም አንዱ ከነዓናዊቷን ሴት አገባ። ይህች ከነዓናዊት ሴት ልጅ አልነበራትም፡ ይህ ልጅ ሞተ። ስለዚህ፡ በዚያን ጊዜ ህጉ... ቀጣዩ ልጅ የወንድሙን ሚስት ወሰዶ፡ ለሞተው ሰው ዘር ያስገኛል ይላል። እና ቀጣዩ ልጅ አልተባበረም ማድረግ የሚገባውን አላደረገም፡ ስለዚህ ጌታም ቀሰፈው። ከዚያም አንድ ታዳጊ ልጅ ነበረው፥ ስለዚህ ይሁዳም “ይህ ልጅ እስኪያድግ ድረስ... እስኪያድግ ድረስ፥ እስክታገቢው ድረስ ጠብቂ፡” አላት።

695 የሁለቱን ወንድሞቹን የቀድሞ ባለቤት ሊያገባ ወደሚችልበት አቅም ባደገ ጊዜ፡ ስለዚህ፡ ለወንድሞቹ ዘር ለማስነሣት፡ በዚያን ጊዜ ሊወስዳት ይገባ ነበር… ከእርሱ በፊት ሞተው ነበርና። ይሁዳ ለሴቲቱ (ከነዓናዊቷ ሴት) ወንድ ልጁን፡ ብላቴናውን አልሰጣትምና፡ ዝም ብሎ እንዲሄድ ፈቀደለት። እሷም መታለልዋን አይታ፡ ወጥታ በፊቷ ላይ መሸፈኛ ሸፈነች፡ እና እንደ ጋለሞታ በአደባባይ ተቀመጠች።

696 ይሁዳም መጥቶ ሴቲቱን አገባ፡ ጋለሞታም ነበረች፡ ወደ እርሰዋም ጋር ገባ። እርሰዋም፡ እንዲህ አለችው፡ "እሺ፡ ሰንት ትከፍለኛለህ? " አለችው… እርሱም…

697 እርሱም፡ "ጠቦት—እሰጥሻለሁ።" አላት፡ "እሺ፡ ይህን እንደምትከፍለኝ ምልክት ስጠኝ።" በትሩንና፡ ቀለበቱን ሌላውንም ወሰዳ አሰቀመጠች።

698 የፍየል ጠቦትን ይዘው በመጡ ጊዜ፡ ጋለሞታይቱን ሊያገኟት አልቻሉም፡ ምክንያቱ ጋለሞታ አይደለችምና።

699 ከተወሰነ ጊዜ በኋላ፡ የመውለጃዋ ወራት መድረሱ ታየች። ልትወልድ መሆኗን ምልክት ባሳየች ጊዜ፡ ወደ ይሁዳም መጥተው "ምራትህ-አመንዝራ-ሆናለች፡" ብለው አወሩለት። "ምክንያቱም ሁለቱ ልጆችህ ሞተዋል፡ እ—እሷ ግን ልትወልድ ነው፡" አሉት።

700 እንዲህም "እሺ፡ ትጠራ፡ እና በእሳት ትቃጠል፡" አላቸው።

701 ስለዚህ ወደ ይሁዳ መልእክት ላከች፡ "ይህን ያደረገው ሰው፡ የዚህ በትርና የዚህ ቀለበት ባለቤት ነው፡" አለችው። እንግዲህ፡ እሱም-የ-አማቿ ነበረ።

702 እርሱም "እሷ ከእኔ የበለጠ ጻድቅ ነች፡" አላቸው።

703 አሁን፡ ልጆቿን የምትወልድበት ጊዜ እንደደረሰ ባወቀች ጊዜ፡ መንታ ነበሩ። መንትያዎቹም… እንደ ቀድሞው የአይሁድ ሥርዓት፡ ቀድሞ የሚወለደው ሕፃን፡ ቀድሞ የሚገለጠውም የመጀመሪያው ልጅ፡ የበኩርነት መብት አለው። ያም፡ አስታውሱ፡ የመጀመሪያ ልጇ ነበር። አንዳቸውም ልጆች ከእርሷ ልጅ አልወለዱም። ከዚህ በፊት ልጅ አልወለደችም።

704 የመጀመሪያ ልጇም በወጣ ጊዜ፡ አንድ እጁን ብቻ አሳየ። አዋላጇ ቀይ ፈትል አደረገችለት፡ ምክንያቱ ቀይ ፈትል የሚናገረው ቤዛነትን ነው ይህም የድንግል ማርያም የበኩር ልጅ የሚሆነው… የቤዛው ቀይ ክር አደረገችለት።

705 እጁንም ወደኋላ በመለሰ ጊዜ፡ ሌላኛው አሰቀድሞ ወጣ። ይህንንም ሲያደርግ፡ "ለምን እንዲህ አደረግክ? የብኩርና መብት ያለው ሌላኛው ነው፡" አሉ።

706 እንግዲህ ዘፍጥረት 38 ማለት ይህ ነው፡ አያችሁ፡ የበኩር ልጅ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እስኪመጣ ድረስ እንደጸና ይቀራል፡ የመጀመሪያው በመዋጀት ህግ ስር ነበረ።

707 ታውቃላችሁ እንዲህ ብዬ ነበር… ስለ ትንሹ አህያ፡ ታውቃላችሁ፡ ነግሬአችኋለሁ፡ አይኖቹ… ከዚህም በላይ፡ ጆሮዎቹ ይሰበራሉ፡ ግን፡ የበኩር ልጅ ሆኖ ከተወለደ ግን፡ በእርሱ ፋንታ ነውር የሌለበት፡ ንጹሕ በግ ይሞታል። ይኸው ነው።

708 ስለዚህ ያ ለብኩርና ነው። ያንን እጁ አይተውት የነገረው፡ ከእናቱ የወጣው የመጀመሪያው ሕፃን (እና እንደገና ወደ ኋላ ሊመለስ እንደሚችል ያውቃሉ)። ከእርሱ ጋር እንደሆነች ለማሳየት እጁን በዘረጋት ጊዜ፡ በኩር ሆነ፡ አዋላጅዋም ቀይ ክር በዙሪያው አሰረችለት እጁንም ወደ ኋላ መለሰ። አያችሁ? ይህን እንጂ፡ ሙሉ በሙሉ፡ ቀዳሚ ነበር። ቀይ ክር ማለት ያ ነው፡ ቀይ ክር... በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሁሉ፡ ቤዛነት ማለት ነው፥ ይህም ወደፊት ስለሚመጣው የበኩር ልጅ የሚያስረዳ ነበር።

709 መጀመሪያ የሚወለደው ፈረስ፡ መጀመሪያ የሚወለደው ከብት፡ ምንም ቢሆን፡ አስቀድሞ የሚወለደው ሁሉ (የሚወለድ) ሁሉ በቤዛነት ሥር ነበር፡ መቤዠት ነበረበት፥ ሁሉም ነገር መቤዠት ነበረበት! ሃሌ ሉያ! ኦህ፡ ይህ ያስደስተኛል። ገባችሁ? **የመጀመሪያው** መቤዠት ነበረበት። ህግ ነበር። የጌታ ስም የተባረከ ይሁን!

710 ኢየሱስ ክርስቶስም በተወለደ ጊዜ፡ ዓለምን ሁሉ ተቤዠ። በትክክል፡ ዋጅቷል። በምድር ላይ ለተፈጠሩት ፍጥረታት ሁሉ ቤዛ ነው። እርሱ ቤዛ ነበር። በዚያም... ቤዛነት ሁሉ በእርሱ ዘንድ ሆነ፡ እናንተም በሌላ መንገድ ልትመጡ አትችሉም በበጎ ሥራም ቢሆን፡ በቤተ ክርስቲያንም አባልነት፡ ወይም በምንም ነገር አይደለም፡ በዚህ በቀይ ክር፡ በዚህ ቤዛ፡ በዚህ የዋርሣ ቤዛ ትመጣላችሁ።

እሺ፡ አሁንም በመቀጠል፦

**71. የራዕይ 11 ሁለቱ ምስክሮች ሞት ጋር በተያያዘ የሚላኩት ስጦታዎች ምን ይሆናሉ... ስጦታዎቹ ምንድን ናቸው?**

ኦህ፡ ወንድም ፓልመር ሆይ፡ ምን ጥያቄዎችን መጠየቅ ትችላለህ!

711 ስለዚህ፡ ቤዛነት፡ እነዚህ ክሮች፡ ይህ የቀይ ክር፡ ቤዛ ማለት እንደሆነ እናያለን።

712 አሁን ቀጣይ ጥያቄ፦

**በራእይ 11 ላይ ያሉት ስጦታዎች ምንድን ናቸው?**

713 ጊዜ ይመጣል... አሁን ይህ በቀደም ሌሊት መልስ ለተሰጠው ጥያቄ ለመመለስ ነው፡ እንዴት እንደሚሆን አንድ ሰባኪ ወዳጄ ስለ አይሁድ፡ ጽፏል።

714 አሁን ለእነዚህ ለአይሁዶች ለ-ሦስት-ዓመት-ተኩል ቃል ተገብቶላቸዋል። ሰንቶች ታውቃላችሁ? ሰባ ሳምንታት ቃል ተገብቶላቸዋል። "መሲሕ ይመጣል በእኩሌታው ይቆረጣል" ይላል። ክርስቶስ ሦስት-ዓመት-ተኩል ሰበከ፡ በትክክል ከሦስት-ዓመት-ተኩል በኋላ ተገደለ፡ ሦስት ዓመት ከስድስት ወር ሰበከ።

715 እና ከዚያም ጥፋትን የሚያመጣው እርኩሰት፡ የ—የሙስሊም ኦማር መስጊድ በቅድስት ሀገር ተተከለ፥ እግዚአብሔር እንደ ተናገረ፡ ሁለት ሺህ-አምስት መቶ ዓመት በፊት፡ ከመሆኑ አስቀድሞ በዚያ ይሆናል ብሎ ተናግሯል። ነቢዩም አየና፡ አይቶም፡ እንዲህ አለ የአሕዛብ ዘመን እስኪፈጸም ድረስ፡ አሕዛብ፡ በዚያ ይረግጧታል አለ።

716 አሁን ገና ለ-ሦስት-ዓመት-ተኩል ቃል ገብቷል። ካስተዋላችሁ፡ እነዚህ የዮሐንስ ራዕይ 11 ምስክሮች አንድ ሺህ፡ ሁለት መቶ ስድሳ ቀን ትንቢት

ይናገራሉ፥ በትክክል ሦስት ዓመት ተኩል ነው። ስለዚህ... ማቅም ይለብሳሉ። አሁን አገልግሎታቸውን፡ ምን እንደሆኑ ተመልከቱ። ሆኖም፡ እነዚህ ሁለት ምስክሮች ይገደላሉ።

717 ስለዚህ፡ የ... የአህዛብ ቤተክርስቲያን ከተነጠቀች በኋላ ወደ አይሁዶች ይመጣሉ። የአሕዛብ ቤተክርስቲያን ለሠርግ እራት ወደ ቤት እንደሄደች፡ ርብቃም ወደ አብርሃም መኖሪያ ከይስሐቅ ጋር ተወሰደች በዚያም እንደተጋቡ ነው። ከዚያም በኋላ ርብቃና ይስሐቅ የአብርሃምን የሆነውን ርስት ሁሉ ይዘው ወጡ፡ ሁሉም ነገር ለይስሐቅ ተሰጠው። በትክክል! ይስሐቅም እስካላገባ ድረስ ወደ ይስሐቅ መምጣት አይችልም። ኦህ ሃሌሉያ! ያ ነው።

718 ክርስቶስም እንዲህ ይሆናል... እግዚአብሔር በዚያ ሙሉ በሙሉ፡ ለዘለአለም እና ለዘለአለም በዚያ በተነቀፈ አካል ይኖራል። በጉ እና ሙሽራይቱ በገነት ከተጋቡ በኋላ፡ እሷ ሙሉ በሙሉ ርስት ይዛ ትመጣለች። በትክክል! ይስሐቅና ርብቃም ይዘው እንደመጡ።

719 እናም ይህ ሥነ ሥርዓት በገነት ሲከናወን፡ ሙሽራይቱ፡ ልዑሉ (የእግዚአብሔርን ልጅ)፡ የአሕዛብ ሙሽራን በክብር በሚያገባበት ጊዜ፥ በመጋባት ላይ ሳሉ፡ ሦስት-እና-ተኩል-ዓመታት የሚከናወኑት ያኔ ይሆናል... ሙሴና ኤልያስም...

720 እንደውም፡ ሙሴ ከቶ አልተገኘም... አይ፡ አስከሬኑ ተወስዷል። መላእክት ወሰዱት፡ አልበሰበሰም፡ አልተበላሸም። እርሱ ፍጹም የክርስቶስ ምሳሌ ነበር። ሞቶ መላእክቱ ወሰዱት፡ ዲያቢሎስም የት እንደተቀበረ አላወቀም፡ ስለ መቀበሩም ከመላእክት አለቃ ሚካኤል ጋር ሊከራከር ሞከረ። መጽሐፍ ቅዱስ የሚለው ይህ ነው። እግዚአብሔር በንጥቀት ወሰደው።

721 የእግዚአብሔር ነቢይ፡ ኤልያስም፡ በጉዞ ላይ ሳለ፡ ወደ ዮርዳኖስ ወረደ፡ መጎናጸፊያውንም አውልቆ ውኃውን መታው፥ ወደ ቀኝም ወደ ግራም ተከፈሉ። ወደ ተራራው ወጣ። ኤልሳዕን... እንዲህ አለው፡ "ስለ ምን ትከተለኛለህ? "

722 እርሱም "የመንፈስህን ዕጥፍ እፈልጋለሁ፡" አለው።

723 አለውም፡ "ከባድ ነገር ጠይቀሃል፡ ነገር ግን እኔ ስሄድ ካየኸኝ ይሆንልሃል።" ዓይኑንም በእሱ ላይ አደረገ።

724 ከዚህም በኋላ፡ የእሳት ሰረገላ የእሳት መላእክት፡ እና የእሳት ፈረሶች ከሰማይ ወረዱ፡ ኤልያስም ወጥቶ ወደ ክብር ተወሰደ። ሞትን ቀምሶ አያውቅም፡ ተነጥቋልና፡ መሞት አለበት!

725 እነዚህንም የዮሐንስ ራእይ 11 ሁለቱን ነቢያት ብትመለከቱ፡ ሙሴና ኤልያስ እንዳደረጉት እንዲሁ ያደርጋሉ። እናንተም "ወንድም ብራንሃም ሆይ፡ ኤልያስና ሙሴ በሕይወት እንዳሉ እየነገርከን ነው ማለት ነው? " በትክክል!

726 ምክንያቱም፡ ከተአምራዊው ተራራ በፊት... በተአምራዊ ተራራ ላይ፡ ኢየሱስ ወደ ቀራንዮ ከመሄዱ በፊት፡ ሙሴ እና ኤልያስ ሁለቱም በዚያ ቆመው ከእርሱ ጋር ተነጋገሩ። በእርግጠኛነት፡ ተነጋግረዋል፡ አልሞቱም።. በፍጹም አልሞቱም፥ ሟቾች ናቸው፡ መሞት አለባቸው። ስለዚህ እነሱ በተከበረ ሁኔታ ውስጥ ናቸው, ያንን ጊዜ እየጠበቁ ናቸው

727 እናም ተመልሰው መጥተው በትክክል ለ-ሦስት-ዓመት-ተኩል በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ሲሰብኩ፡ ያን ጊዜ በረከቱ ከአሕዛብ ሲወሰድ፡ (ቤተ ክርስቲያንም ስትወሰድ)፥ ያን ጊዜ የቀዝቃዛና፡ የመደበኛ ቤተ ክርስቲያን ሰዎች፡ በኮሚኒስቶች እና በሮማውያን ፓርቲዎች እንደ ውሻ እየታደኑ፡ ያኔ እየታደኑ ይገደላሉ። እነዚህ ነቢያት ለ-ሦስት-ዓመት-ተኩል ይሰብካሉ፥ ያኔ—ይገደላሉ፡ መጽሐፍ ቅዱስም በታላቅ ጎዳና... እንደሚገደሉ ይናገራል፡ ይህም በመንፈሳዊ ሁኔታ፡ ሰዶምና ግብጽ፡ ጌታችን የተሰቀለበት ነው። ያ በኢየሩሳሌም ነው፥ አያችሁ፡ በመንፈሳዊ አጠራር፡ በዚያ በኢየሩሳሌም ውስጥ ነው።

728 በአደባባይም ለሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት ይወድቃሉ። ከዚያም በ-ሦስቱ-ቀን-ተኩል መጨረሻ ላይ፡ የሕይወት መንፈስ ይገባባቸውና ይነሣሉ። እንደሌሎች ሟቾች መሞት ነበረባቸው፡ መሞት አለባቸው። እና እነዚህን ሁለት ሰባኪዎችን በገደሉ ጊዜ...

729 ሰለ በደል ሰብከዋልና፡ እሳትንም ከሰማይ አወረዱ። ይህን ያደረገው ማን ነበር? አያችሁ? መቅሰፍቶችን ከሰማይ አወረዱ፡ እንደፈለጉም... ፈጥነውም ምድርን መቱ። እሳትንም ከሰማይ አወረዱ። ዝናብም እንዳይዘንብ እስከፈለጉ ድረስ፡ ሰማያትን ዘጉ። ማን ነበር? በትክክል ሙሴ እና ኤልያስ። እነዚህ ሁለት ምስክሮች ናቸው።

730 በሰብከታቸውም፡ ቤተ ክርስቲያንን፡ ወይም ዓለምን ባሰቃዩአት ጊዜ፡ አይሁድን ተቀብለው፡ ወደ ንሰሐ መለሷቸው፡ ወደ እምነትም መለሷቸው... ኢየሱስን ለሙሽሪት ሲመጣ ሲያዩት፡ እንዲህ ይሉታል፡ "እነሆ፡ የጠበቅነው አምላካችን ይህ ነው። እሱ ነው!" ለእነርሱ ግን አይመጣም፡ ለሙሽራይቱ ይመጣል። ሙሽራይቱም...

731 ዮሴፍ ወደ ግብፅ በሄደ ጊዜ፡ ወንድሞቹን ከእርሱ ጋር አልወሰደም፡ ነገር ግን ሚስቱን ከዚያ አገኘ። በትክክል! ራሱን ለወንድሞቹ ሲገልጽላቸው ግን፡ ከሱ ጋር ማንም አልነበረም። ይህ ፍፁም እውነት ነው። ለእነዚህ አይሁዶች ራሱን ሲገልጽላቸውም፡ ከአይሁድ በቀር ከሱ ጋር ማንም አይኖርም። የዮሴፍን ገዳዮች ሁሉም፡ በዚያ ቆመው፥ እርሱም፡ "እኔ፡ ወንድማችሁ ዮሴፍ ነኝ፡" አላቸው። አለቀሰም።

732 እነርሱም አሉ፡ "እንግዲህ ዋጋ እንደምንከፍል አሁን አወቅን፡ ምክንያቱም እኛ ሰለገደልነው።"

733 ተመሳሳይ ነገር ነው፡ እነዚህ አይሁዶች አሁን ከመምጣቱ በፊት ይህን ታላቅ የችግር ጊዜ ይጠብቃቸዋል፡ ይህም ወደ ትውልድ አገራቸው የሚመለሳቸው ሰደት ነው። ወደዚያኛው የቀርሜሎስ ተራራ ማዶ እንደ መንጋ ያባርሯቸዋል።

734 ጌታ ኢየሱስ ለሙሽሪት ሲመጣ፡ እና ሲያዩት፡ እንዲህ ይላሉ፡ "እኛ ስንጠብቀው የነበረው፡ እሱ ይህ ነው!" ከክንፎቹ በታች ፈውስ ይዞ ይነሳል። እውነት ነው።

735 የአይሁድ ቅሪትም፡ ማለት ቤተ ክርስቲያንም፡ እነዚህን ሁለቱን ነቢያት ገድለው፡ በመንፈሳዊ አባባል ሰዶምና ግብጽ በተባለው ሰፍራ፡ ይህም ጌታችን በተሰቀለበት ሰፍራ በጣሏቸው ጊዜ፡ እርስ በርሳቸው ሰጦታ ይላላካሉ (ይህ ዓለም የሚያደርገው ነው)።

736 አሁን፣ ወንድም ፓልመር፡ ይኸውልህ፡ መለስ ብለህ የሮማን ታሪክ ተመልከት እና በኦኣለም ታሪክ ውስጥ ከጦርነት በኋላ ስጦታ የላከች ብቸኛ አገር እንዳለች ታገኛለህ፡ ያም የሮማ ስርወ መንግስት ናት።

737 በዚህ ምክንያት ነው የክርስቶስ ተቃዋሚ ከሮም ይነሣል ያልኩት። አውሬው ከሮም እንጂ፡ ከሞስኮ አይመጣም። ልጅዋን እንደ ወለደች፡ ሊበላው በሴቲቱ ፊት የቆመው ቀይ ዘንዶ ከሮም የመጣ ነው። ይህ ዲያብሎስ፡ ያ ዲያብሎስ የት ነበር? ማን ነበር? ከሁለት አመት በታች የሆናቸው ህጻናትን ሁሉ ለመግደል የላከው አውግስጦስ ቄሳር ነው። ቀዩ ዘንዶ፡ ዘንዶው **አውሬ** ማለት "ስልጣን፡" ይወክላል። የሮማ ስልጣን መንግሥት ይህንን ክርስቶስ ሕፃን ለማግኘት ሰደት አስነሣ።

738 ተመሳሳይ ነገር! ሮማውያን የጥንት ጣዖት አምላኪ፡ ሮማውያን ታላቅ ድል ባደረጉ ቁጥር፡ ነጭ ድንጋዮችን እና ነገሮችን እንደ ስጦታ አድርገው፡ እንደ ማስታወሻዎች፡ እርስ በርሳቸው ይላላኩ ነበር፡ እንግዲህ... እነዚህ ድንጋዮች፡ በሮማ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተላላኳቸው ትንሽ ስጦታዎች ናቸው። በትክክል! ትክክል ነው። መሆንም አለበት።

739 በቫቲካን ከተማ ቆሜ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አስተያየሁት። ጳጳሱ ባለ ሶስት ድርብ አክሊል ነበረው፡ Vicarivs Filii Dei፡ እነዚህ ሁሉ የሰማሁት እና ሁሉም ነገሮች፡ ትክክለኛና እውነት ናቸው፥ ከሰማይ በታች ያለውን ሕዝብ ሁሉ የሚገዛ የሃይማኖት ቡድን ነው፡ እንዲሁም ነው። ይኸው፡ ያ ነው።

740 ከካቶሊክ ሰዎች ጋር ችግር የለብኝ (የለብኝም፡ ወዳጄ)፡ እንደሌላው ጥሩዎች ናቸው፡ በዚህ መጽሐፍ ቅዱስ መሰረት ግን ሃይማኖታቸው የተሳሳተ ነው። ይህ መጽሐፍ ቅዱስ እውነት ከሆነ፡ የእነሱ ስህተት ነው። እንዲህ ይላሉና... "ቤተ ክርስቲያን በምትለውን እንጂ፡ መጽሐፍ ቅዱስ በሚለውን አይደለም" ይላሉ። እኛ መጽሐፍ ቅዱስ በሉአላዊ ሥልጣን እንደሚናገር እናምናለን! ፍፁም፡ የእግዚአብሔር ቃል ነው።

741 እንግዲህ ታያላችሁ፡ በዚያን ጊዜ የተላኩት፡ እነዚህ ድንጋዮች፡ በራዕይ ላይ እርስ በርሳቸው የተላኩ ስጦታዎች እነዚህ—ድንጋዮች ናቸው። ይህም የሚያሳየው፡ መፅሃፍ ቅዱስ... እዚህ ራእይ ላይ፡ እንዲህ ይላል፡ "ጥበብ ያለው የአውሬውን ቁጥር ይቁጠረው። ጥበብ ያለው **እንዲህ-እና-እንዲያ** ያድርግ። አንዳንድ የጸጋ ስጦታዎች መንፈስ ያለው **እንዲህ-እና-እንዲያ** ያድርግ።" ቤተ ክርስቲያን ከምልክቱ ምን ያህል እንደራቀች አይታችኋል?

742 ዛሬ ጠዋት አንድ ወጣት ስለ መንፈሳዊ ስጦታዎች፡ በልሳን ስለመናገር ጠየቀኝ። በጣም ቅን፡ ወጣት ነው፡ በቅርቡ ወደ አገልግሎት እንደሚገባ አምናለሁ። ስለ ቤተ ክርስቲያንም፡ እንዲህ አልኩ፡ "ብዙው ሥጋዊ ነገር ነው። ያንን አንፈልግም ግን የምንፈልገው ትክክለኛው ነገር ነው። እንዲኖረን የምንፈልገው ይህ ነው።"

743 ይኸውላችሁ በመጀመሪያ ነገር፥ እነዚህን ነገሮች በቤተክርስቲያን ማስተማር አትችሉም፡ አንደኛው፡ ልሳን ይኖረዋል፡ ሌላው ዝማሬ፡ ከዚያ ነገሩን ለማሳደግ ትዋጋላችሁ። ስጦታን የሰጠው እግዚአብሔር ሲሆን ግን፡ በራሱ ጊዜ ይገለጣል። እውነት ነው። አየህ፣ እነዚህ የእግዚአብሔር ስጦታዎች ናቸው፣ ይህ ለድል ወደ ቤተክርስቲያን የላከው ነው።

744 አሁን፡ የክርስቶስ ተቃዋሚው ሁሌ አንበስ እና ጎፈር አለው፡ ያም ዋ—ዋ—ዋናው ነገር በማጣመም ነው። ይህም የሮማ ስርወ መንግስት ስጋዊ ስጦታዎችን፡ እርስ በርስ መላላኩ ይህ ነው። እግዚአብሔር ለድል ነሺዎች መንፈሳዊ ስጦታዎችን ይልካል፥ ሮማውያንም እርስ በርሳቸው ስጋዊ ስጦታዎችን ይላላካሉ።

745 እኛ መንፈስ ቅዱስ መንፈስ እንደሆነ እናምናለን፡ እርሱን የተቀበልነውም ከላይ በሚመጣው ጥምቀት ነው።

746 የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ስታስተምር፡ "ቅዱስ ቁርባን የክርስቶስ አካል ነው፥ ይህም የድርቆሽ ቂጣውን ስትቀበሉ፡ መንፈስ ቅዱስ፡ መንፈስ ቅዱስ፡ ቅዱስ ቁርባን **ነው** ይሉታል።" አያችሁ?

747 እኛ ቁራሽ ቂጣ ነው ብለን እናምናለን እንጂ፡ የክርስቶስ አካል ነው ብለን አናምንም፡ (እኛም ከደቂቃዎች በኋላ ልንወስደው እየተዘጋጀን ነው)። ይህም የክርስቶስን አካል እንደሚወክል እናምናለን። ያ አይደለም...

748 በካቶሊክ አስተምህሮ እና በፕሮቴስታንት አስተምህሮ መካከል ያለው ልዩነት ይህ ነው። አያችሁ? የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን እንዲህ ትላለች፡ "አካሉ... ማለት ቂጣው ራሱ እውነተኛው አካሉ **ነው**። ቤተ ክርስቲያኒቱ ይህንን የመለወጥ ኃይል አላት።" አንድ የካቶሊክ እምነት ተከታይ በቤተ ክርስቲያን አጠገብ አልፎ ሲራመድ፡ አንገታቸውን አጎንብሰው የመስቀሉን ምልክቶች ሲሰሩ፡ አይታችሁ ታውቃላችሁ? ይህ በትንሽዬዋ ተብርናክል ውስጥ ባለው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ይህ ትንሽ ጧፍ እየበራ ስለሆነ ነው። እዚያ ውስጥ ትንሽ ጧፍ አለች፡ እና ይህ የድርቆሽ ቂጣ እዚያ ውስጥ ይቀመጣል። "ይህም የክርስቶስ አካል ነው። እናም ያንን ስትወስድ፡ የክርስቶስን ትክክለኛው ስጋ ወሰደሃል በመጀመሪያው ቁርባንህ እና በኑዛዜህ እና በመሳሰሉት ላይ። ይህ ማለት፡ በጥሬው፡ የክርስቶስን ስጋ እንደወሰድክ ነው።"

749 እኛ ግን የክርስቶስን ስጋ **ተምሣሌት** ነው እንላለን፡ አያችሁ፡ ፍፁም ከቁራሽ ቂጣነት የዘለለ ነገር የለውም። እና ቂጣ ባይሆንም እንኳን፡ ሌላ ነገር ቢሆን፡ አሁንም ለተምሣሌት ብቻ ነው። በ—በትክክል። ምንም ቢሆን...

750 ልክ እንደነዚያ "በገንዳ መጠመቅ አልፈልግም፡ በወንዙ ውስጥ መጠመቅ እፈልጋለሁ፡" እንደሚሉት ሰዎች ነው።

751 እስከተጠመቅክ ድረስ፡ ምን ለውጥ ያመጣል? ገንዳ ውኃ ውስጥም፡ ይሁን... እንግዲህ ፊልጶስም... ጃንደረባው በተጠመቀ ጊዜ፡ በውኃ ገንዳ ውስጥ ተጠመቀ። ፊልጶስ ጃንደረባውን በውኃ ገንዳ ባጠመቀው ጊዜ፡ መንፈስ ቅዱስ ወሰደው ፊልጶስንም ወሰደው፡ ከዚያ በኋላ እስከ ሁለት መቶ ማይል ርቀት ድረስ አልታየም። በመንፈስም ነጠቀው፡ ወደ ሁለት መቶ ማይሎች ርቀት ይወሰደው ዘንድ—ሰረገላን ከሰማይ ላከለት። ኣሜን። ድንቅ ነው!

አሁን፦

**ከ-ሺህ-ዓመት መንግስት በኋላ ቅዱሳን የት ይሆናሉ? እና ምን ዓይነት አካል ይኖራቸዋል**? ይህን ከአፍታ በኋላ እመለሰበታለሁ። [ወንድም ብራንሃም ይህን ጥያቄ በአንቀጽ 820 ላይ፡ እንደ ጥያቄ 74 መለሰ—እርታዒ።] ከኢየሱስ ጋር ይሆናሉ።

752 እሺ፡ ስ—ሰባተኛው ጥያቄ፦

**72. በመላእክት እንዴት እንፈርዳለን?**

753 ይህ የሚገኘው… በመላእክት እንዴት እንፈርዳለን? ምክንያቱም እኛ የእግዚአብሔር ወንዶች እና ሴቶች ልጆች ነን። መላእክት አገልጋዮች ናቸው፡ እኛ የእግዚአብሔር ወንዶች እና ሴቶች ልጆች ነን። መጽሐፍ ቅዱስም በመላእክት ላይ እንፈርዳለን ይላል። እውነት ነው። አሁን፡ እንግዲህ…

8ኛው ጥያቄ፦

**73. በአንደኛ ቆሮንቶስ ከመላእክት የተነሣ ፀጉር የሚለው ለምንድነው?**

754 አሁን አንድ ሰው አንደኛ ቆሮንቶስ፡ ም—ምዕራፍ 11 ክፈትልኝ፡ እና እናየዋለን፡ እናንተም ይ—ይህ ምን እንደሆነ ይገባችኋል… በአንደኛ ቆሮንቶስ፡ 11ኛው ም—ምዕራፍ፡ ጳውሎስ ሲናገር እናገኘዋለን። ይህንን እስክከፍት ድረስ ትንሽ ጊዜ ስጡኝ፡ በፍጥነት እናነበዋለን ከዚያ በኋላ እ—እንመልሰዋለን።

755 በዚህ ሌላ ጥቅስ ላይ የምለው ነገር አለኝ፡ ጌታ እንደ እኛ እንደሚሰጠን ተስፋ አደርጋለሁ። ያገኘው ሰው አለ… ምእራፍ 11 ላይ ይመስለኛል፡አዎን፡ በጣም ጥሩ። አሁን እንድትረዱት፡ በጣም በጥንቃቄ አሁን፡ በትኩረት አዳምጡ። አሁን አንብቤ እስክጨርስ ድረስ፡ ሁሉም ንቃተ ህሊናችሁ ሁሉ፡ በሼሰት ኪሳችሁ ውስጥ አድርጉት እያችሁ፡ አስተያየት እስክትሰጡበት ድረስ። በጥሞና አድምጡ፡ የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦

> **እኔ ክርስቶስን እንደ… እንደምመስል፡ እኔን ምሰሉ።** (ጳውሎስ ያለው፡ "ክርስቶስን እንደምከተል፡ እኔን ተከተሉኝ።")
>
> **ወንድሞች ሆይ፥ በሁሉ ስለምታስቡኝና፡ አሳልፌ እንደ ሰጠኋችሁ፡ … ወግን ፈጽማችሁ ስለ** ያዛችሁ፡ **አመሰግናችኋለሁ።**
>
> **ነገር ግን፥ የወንድ ሁሉ ራስ ክርስቶስ፥ የሴትም ራስ ወንድ፥ የክርስቶስም ራስ እግዚአብሔር እንደ ሆነ ልታውቁ እወዳለሁ።**

756 እንዴት እንደሆነ ተመልከቱ? እግዚአብሔር፣ ክርስቶስ፣ ወንድ፣ ሴት። አሁን፦

> **ራሱን ተከናንቦ የሚጸልይ፡ ወይም ትንቢት የሚናገር ወንድ ሁሉ፡** ክርስቶስን ያዋርዳል።
>
> **ራስዋን ሳትሸፍን ግን** የምትጸልይ **ወይም** ትንቢት **የምትናገር ሴት ሁሉ ራስዋን** ታዋርዳለች፥…

757 አሁን የተወሰነ ጊዜ እንውሰድና፡ የሴቲቱ ፀጉር መሸፈኛዋ እንደሆነ እንመልከት፥

> **…** እንደ**… ተላጨች ያህል አንድ ነውና።** (ይህ ማለት—ፀጉሯን የምትቆርጥ ከሆነ፡ ትላጨው።)
>
> **ሴትም ራስዋን ባትሸፍን፡ ጠጉርዋን ደግሞ ትቆረጥ፥** (ትቆረጥ ማለት ትላጭ ማለት ነው፡ እያችሁ)… **ለሴት ግን ጠጉርዋን መቆረጥ ወይም መላጨት የሚያሳፍር ከሆነ፡ ራስዋን ትሸፍን።**

758 አሁን ወደ ጥያቄአችሁ ደርሰናል። እያችሁ? በጣም ጥሩ፡ ስለዚህ በመጽሐፍ ቅዱስ መሠረት፡ ሴት—ፀጉሯን መቁረጧ ስህተት ነው። አሁን እዚህ ላይ አዳምጡና መጽሐፍ ቅዱስ ወንድ ሚስቱን ፀጉሯን ብትቆርጥ ሚስቱን ሊፈታት ሕጋዊ መብት የማይሰጠው ከሆነ፡ ይህ ትክክል እንደሆነ ወይም እንዳልሆነ ተመልከቱ።

> **ወንድ... ወንድ ራሱን መከናነብ አይገባውም** (ይህ ማለት፡ ረጅም ፀጉር ማለት ነው)፡ ይህም **ወንድ የእግዚአብሔር ምሳሌና ክብር ስለ ሆነ ነው፥ ሴት ግን የወንድ ክብር ናት።** (እንዲህ አሰባችሁ ታውቃላችሁ? )

759 አሁን እዚህ ጋር ማቆም እፈልጋለሁ፡ ምክንያቱም ይህ በጥልቀት እንድትረዱት ስለምፈልግ፡ እያችሁ። እና አሁን ልብ በሉ፡ በአስር ሺዎች የሚቆጠሩ ቆንጆ ሴቶች አይቻለሁ (አሁን የማውቃቸው፡ እና ብዙዎቹ በዚህ ቤተክርስቲያን ውስጥ ቁጭ ብለዋል) ክርስቲያኖች ናቸው፡ ጸጉራቸው አጫጭር ነው። እና እናንተን እየወቀስኩ አይደለም፡ የተማራችሁት ትምህርት እንጂ። እያችሁ? ያ ነው። ሰባኪያችሁ ይህ ነግሯችሁ አያውቅምና። በዚህ ተበርናክል የሚካፈሉ ሴቶች እንደዚያ ከሆኑ፡ ራሳቸው ጥፋተኞች ናቸው። እያችሁ፡ ምክንያቱ እኛ በርግጠኝነት ነግረናቸዋል።

760 አሁን፡ አሁን ይህንን ተመልከቱ፦

> ... **ለ... ወንድ...** (ቁጥር 7 ላይ)... **ለወንድ...**

761 አሁን፡ እዚህ ጋር የሚናገረው ለማን ነው? አንዴ፡ አንዲት ሴት እንዲህ ብላኛለች፡ "ኦህ፡ ጳውሎስ 'ኮ የሴት-ጥላቻ የነበረበት ሰው ነው።"

762 እሺ፡ እዚህ ላይ እያለን፡ ወደ ገላትያ 1፡8 እንሂድና፡ ጳውሎስ ስለዚህ ጉዳይ ምን እንደሚል፡ እያችሁ፡ በገላትያ 1፡8 ተመልከቱ። ጳውሎስ እዚህ ገላትያ 1፡8 ላይ እንዲህ እንዳለ ታገኛላችሁ፥

> ... **እኛ ብንሆን፡ ወይም ከሰማይ መልአክ፡** ከዚህ ከሰማችሁት ወንጌል **የሚለይ ወንጌልን ቢሰብክ፡ የተረገመ ይሁን።**

763 እንግዲህ እኔን አትውቀሱ፡ እሱን ውቀሱት፡ እሺ።

> **ወንድ የእግዚአብሔር** ምሳሌና ክብር ስለ ሆነ፡ **ራሱን መከናነብ አይገባውም፤ ሴት ግን የወንድ ክብር** እና ምስል **ናት።**

764 አሁን ቀጣዩን ጥቅስ ተመልከቱ፦

> **ሴት ከወንድ ናት እንጂ፥ ወንድ ከሴት አይደለም**ና።
>
> **ሴት** ስለ **ወንድ** ተፈጠረች **እንጂ፥ ወንድ** ስለ **ሴት አልተፈጠረም**ና።

765 አሁን፡ የምለው ነገር በእውነት በፍቅር እና በየዋህነት ነው፡ እናም እኔ በተናገርኩት መንገድ እንድትረዱት ተስፋ አደርጋለሁ። እኔ ወደ ሌሎች አገሮች ተጓዥ ከመሆኔ ጋር ተያይዞ... አሜሪካ፡ አሜሪካ በዓለም ላይ ካሉት የትኛውም ሀገር ለሴቶቻቸው ካላቸው ህጎች ይልቅ በጣም ዝቅተኛ የሆነ፡ የወረደ-ህጎች አሏት። ፓሪስ፡ ፈረንሳይ፡ አሜሪካ ሴቶቿ እንዲሰሩ ከፈቀደችበት መንገድ ጋር ሲነጻጸር የሰማይ-ጠቀስ ፎቆች ርቀት አለው። አሳፋሪ ነው!

766 የአሜሪካ አምላክ ሴት መሆኗን አስተውላችኋልን? በዚህ መጽሐፍ ቅዱስ ላረጋግጥላችሁ እችላለሁ። እውነት ነው። የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን የድንግል ማርያም አስተምህሮዋን ለማስተዋወቅ ይህ መሆን እንደነበረበት አስተውላችኋል?

767 እንግዲህ፡ ሴት ለወንድ ካልተፈጠረች፡ ማለቴ... ወንድ ለሴት ካልተፈጠረች፡ ሴት ግን ለወንድ ከተፈጠረች፡ ታዲያ እንዴት ሴትን ታመልካላችሁ? አያችሁ? አሁን፡ ይህ ምን ጀመረ፡ ይህ ነገር በፓሪስ ተጀምሮ በሆሊውድ አረፈ። በዚህ ጊዜ ፓሪስ ሞዴሎቿን እና ፋሽኖቿን እና ሁሉንም ነገር ለመፈለግ ወደ ሆሊውድ መምጣት ያለባት ሆናለች፡ ይህ የአሜሪካ ሴቶቻችን ውድቀት ነው።

768 ይህ ምንድን ነው? አገራችን እንዲህ አይነት መሰረት ላይ በመድረስ ሴቶችን ወደ እነዚህ የስራ ድርሻዎች ለመተካት፡ ስራውን ከወንዶች እስከምንወስድ ድረስ፡ ዘጠና በመቶው፡ ሴተኛ አዳሪ የሆኑበት ደረጃ ላይ፡ ደርሰናል። እና ስለ ወንዶች እነርሱም መሸነፋቸውን ስንናገር፡ እውነት ነው፡ ምክንያቱም ሥራቸውን የሚሰሩት ሴቶች ናቸው። እና ሴቶችን የመንገድ ሰላም መኮንኖች እስኪያደርጓቸው ድረስ በጣም ዝቅተኛ-ደረጃ ላይ ደረሱ። ይህ ለማንኛውም ህዝብ ውርደት ነው! አዎን፡ ወዳጄ። ምንስ ታደርጉታላችሁ?

769 "ወንድም ብራንሃም ሆይ፡ ስለዚህ ሁኔታ ምን ታደርጋለህ?" እኔ አሜሪካዊ ዜጋ ነኝ፡ ትልቁ አለቃ የሚለውን አደርጋለሁ፡ ማክበር አለብኝ። መቼም ቢሆን... አ—አንድ ቤተሰብ ለቤተሰቡ ያለውን ክብር ካጣ (ልጆቹ ለወላጆች ያላቸውን ክብር ያጣሉ)፡ ያ ቤተሰብ ይበታተናል። አ—አንዲት ቤተ ክርስቲያን ለፓስተሯን ክብር ካጣች፡ ለምን፡ ያ ቤተ ክርስቲያን ጠፍቷል። እናም አንድ ህዝብ ለጠቅላይ ፍርድ ቤት እና ለውሳኔው የሚሰጠውን ክብር ከሌለው፡ ያ ህዝብ ፈርሷል። በትክክል ትክክል ነው። እነዚያን ነገሮች ማክበር አለብን ምክንያቱም እነሱ አለቆች ናቸው፡ አያችሁ። ከመጀመሪያው ግን ልክ አይደለም። በፍጹም!

770 ታውቃላችሁ ሰው በመጽሐፍ ቅዱስ... በዘፍጥረት፡ ምዕራፍ 1 ላይ፡ እግዚአብሔር ሴትንና—ወንድን ሲፈጥር፡ ወንድና ሴትን ሲፈጥር፡ ያን ጊዜ እግዚአብሔር ሔዋንን "ባልሽ ይገዛሻል፡ እርሱም ገዢሽ ይሆናል" እንዳላት ታውቃላችሁ? ያንን በአሜሪካ ውስጥ ተናገሩ እና የት እንደምትደርሱ እናያለን! ወዳጄ፡ እንዲህ አይደለም፡ ሴቲቱ በወንድ ላይ ትገዛለች፥ ያን ማድረግ አለባቸው፡ ማሕበራዊ ሰፍራዎች ሁሉ ተቀናጅቷል...

771 አስፈላጊ ከሆነ፡ ከዚያ ከቢሮዬ፡ እዚያም በደርዘን የሚቆጠሩ፡ በጣም ጥሩ ሴቶችን፡ ማምጣት እችላለሁ... ሁሉም ሴቶች አንዳንድ ጊዜ መሥራት የለባቸውም ማለቴ አይደለም፥ ምናልባት የታመመ ባል፡ ወይም የሆነ ነገር ያላቸው ከሆኑ ይስሩ። ግዴታ ካልሆነባቸው ግን፡ መስራት የለባቸውም። ሰፍራቸው በቤታቸው ነው፡ ትንሿ ቤተ መንግስታቸው፡ መሆን ያለባቸው በትክክል በዚያ ነው።

772 አሜሪካዊያን ሴቶቻችን መሞት እንኳ ቢሆን ነፃ የመውጣት መብት ተሰጥቷቸዋል። በሁሉም እንስሳት እና በሌሎች ነገሮች ዘንድ፡ ይህ ሁኔታ ሲያሸንፍ፡ ሰፍራውን በመውሰድ ከዚያም የሁሉም ዘር ውድቀት ያስከትላል።

773 በአፍሪካ ውስጥ ትንሽ ወፍ አለች፡ እና ባለ ትንሽ አፍ ናት።

774 ይኸውላችሁ፡ በአብዛኛው፡ ሁልጊዜ ከሁለቱ መካከል እንስቷ በጣም አስቀያሚ ነች። የአጋዘን ተባት፡ የኤልክ ተባት፡ የዳክዬ ተባት፡ አ—አውራው ዶሮ፡ ተባቶቹ ሁል ጊዜ እጅግ ያምራሉ፡ ሁል ጊዜም እንዲሁ ነው... ምክንያቱም፡ እንስቷ ሁልጊዜ የጎጆ ወፍ ነች። ጎጆው ላይ ተቀምጣ፡ ልጆቿን ታሳድጋለች። ከጭልፊት፡ ከእባቡ፡ ከቀበሮ፡ እና ከሌሎች ትደበቃለች፡ አያችሁ፡ ጫጩቶቿን ታሳድጋለች።

775 በዚህ ዝርያ ውስጥ ግን... ወይም በጾታ—ሴ—ሴቷ፡ ወይም እንስቷ፡ በውበት የበላይ ናት፡ ሁሌም እያሽቆለቆለ ነው። አፍሪካ ውስጥ፡ አንድ ወፍ አለች... ትንሽ ወፍ ናት፡ ይህች ወፍ በተለያዩ አህጉራት የምትገኝ ብቸኛዋ ወፍ፡ ከወንዱ የበለጠ ቆንጆ ነች። ይህ ሲሆን... ይህች—ወፍ ሁልጊዜ በተደጋጋሚ ታመነዝራለች። ወንድ ፈልጋ ትዞራለች፡ ከእሱ ጋር ከተጣመረች በኋላ እንቁላሎችን ትጥላለች፡ እናም ወንዱ እንቁላሎቹን ለመፈልፈል ትታው ሌላ ወንድ ለመፈለግ ትሄዳለች። ይህ ፍፁም እውነት ነው። አያችሁ? ምን ማለቴ እንደሆነ አያችሁ?

776 አሁን፡ ዛሬ፡ አሜሪካ ውስጥ፡ ወደ ሴቶቻችንን እንመለስ። ከኬንታኪ የሚኖር ወጣት፡ ከጥቂት ቀናት በፊት፡ ሰምንት መቶ ሴቶች እዚህ ኬንታኪ ውስጥ በአንድ ፋብሪካ ውስጥ እንደሚሰሩ ነገረኝ። እርሱም፡ “ከነርሱ መካከል አራት መቶዎቹ የለመዱ ዝሙት አዳሪዎች፡ እና ልጆች ያሏቸው ባለትዳር ሴቶች እንደሆኑ እምላለሁ አለኝ።” አንድ ወንድ ሚስቱን ወደዚያ አስገባትና፡ በቦርድ ደብድቦ ሊገላት ትንሽ ቀርቶት ነበር። ሌላኛው ደግሞ ተኩሶ ሰው ሊገድል ሄደ። ሌላው በስለት ለመውጋት እና ለመማታት። መሆን የለበትም። ይህ ጥሩ አይደለም።

777 ሴቲቱን ወደ ኩሽና ውስጥ መልሷት ቦታዋ ያ ነው፡ ያን ጊዜ ሁሉም ነገር ደህና ይሆናል። በሕዝብ ተቋማት ውስጥ እንድትሠራ ብታደርጓት ግን፡ አልቆላታል። በትክክል-... ይህን የምናገረው...

778 አሜሪካውያን ሴቶች በትዕቢት፡ “ይህ ምንም እውነት የለውም።” እና፡ “አሳየኝ” እያሉ ተሳለቁበት። በትክክል፡ ይህን ማድረጋችሁ ግድ ነው፡ ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ እንደምትሆኑ ተንብዮአል። ማድረጋችሁ አይቀርም።

779 እነሆ... በጥንት ጊዜ፡ እንዲህ ነበረ፡ በሜቶዲስት ቤተክርስቲያን ውስጥ፡ አንዲት ሴት ፀጉሯን ብትቆርጥ፡ ከቤተክርስቲያን ትባረራለች፡ በትክክል፡ ያባርሩ ነበር። አዎን፡ ያለጥርጥር። ናዝሪኖች፡ ፒልግሪም ሆሊነሶች፡ ጴንጤዎች፡ ሁሉም ያባርሩ ነበር። ምን ተፈጠረ?

780 ለምን እንደሆነ ታውቃላችሁ? ከመድረክ ጀርባ አንዳንድ ሴታሴቶች ስላሏችሁ ነው። ይህ ፍፁም እውነት ነው። ስለ ደመወዙ የሚፈራ... እንዳይገለሉ የሚፈሩ፡ ከቤተክርስቲያን እንዳይባረሩ የሚፈሩ ሰዎች አሉ። ቢጎዳም ባይጎዳም አቋም ለመያዝ፡ የእግዚአብሔርን ቃል የሙጥኝ ለማለት ድፍረቱ አልነበራቸውም። ይህ ፍፁም እውነት ነው።

781 በጥሞና አዳምጡ፡ ወንዱ አለቃ ነው። ቤቱን የምታስተዳድሪው እንዳይመስልሽ። የቤቱ አለቃ አንቺ አይደለሽም። አንቺ... ፍጹም ባሪያ ነሽ

ማለት አይደለም፡ ግን ረዳት ነሽ። አዳምም… ወንዱ በሚስቱ ላይ ይገዛል፡ እርሱም በሚስቱ ላይ ኃላፊነት ይሸከማል። እግዚአብሔር ወንዱን ስለሚስቱ ተጠያቂነትን እንዲኖረው አደረገው። አሁን፡ አንብቡና እግዚአብሔር የሚናገረው እንደ ሆነ ተመልከቱ።

> **ወንድ የእግዚአብሔር ምሳሌና ክብር** ስለ ሆነ፡ **ራሱን መከናነብ አይገባውም፥…**

782 እግዚአብሔር ሴት አይደለም፡ እግዚአብሔር ወንድ ነው። በድንግል ማርያምና በሌሎች ያንን ሁሉ፡ ምልጃ-… ወይም አማላጅነት እና የመሳሰሉ ነገሮች ሲያደርጉ፡ ወደ ድንግል ማርያም ሲጸልዩ፡ ምን እንደሚያስታውሰኝ ታውቃላችሁ? ጳውሎስ ያወገዛት እና ያባረራት፡ ታላቋ ጣኦት ዲያና። እውነት ነው። እርሱም "እንግዲህ፡ እግዚአብሔር ሴት አይደለም፡" አላቸው!

783 በአንድ ሜዳ ላይ ድንጋይ ወድቆ ስለተገኘ፡ ጣኦቷ የራሷን ምስል ከሰማይ ወረወረች አሉ፡ በቆሮንቶስ፡ እና በዚያ አካባቢ የነበሩ ሴቶች፡ ዲያናን… ያመለኳት፡ እና ሴቶች ሰባኪ ለመሆን የፈለጉት ለዚያ ነው።

784 "ይኸው፡ መሰበክ እንደምንችል መንፈስ ነግሮናል፡" አሉ።

785 እርሱም፡ "ምነው? የእግዚአብሔር ቃል ከእናንተ ዘንድ መጣን፡ ወይስ ከእናንተ ዘንድ ወጥቷልን? ማንም መንፈሳዊ ወይም ነቢይ የሆነ ቢመስለው፡ ይህች የምላችሁ ትእዛዝ የጌታ ትእዛዝ እንደሆነች ይወቅ፥ ሴት ግን ዝም ትበል በቤተ ክርስቲያንም እንድትገዛ፡ በምንም ነገር ልታስተምር ወይም ልትገዛ አይገባትም።" ልክ ነው! የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል እንዲህ ይላልና። አያችሁ? በፍርድ ቀን እግዚአብሔር ብዙ ቁጥር ያላቸውን ሰባኪዎችን ይጠይቃቸዋል መልሰም ይሰጡበታል።

786 እሺ፡ ሰሙት! እናንተም "እንግዲህ፡ ልንገርህ፡ እኛ የተማርነው እንዲህ ነው፡" ትላላችሁ። አሁን የተሻለውን አውቃችኋል! እውነት ነው። እናንተ ወይም ሌላ ሰው የመድኃኒት መጠን እየወሰዳችሁ ከነበራችሁ፡ እና አንድ ሰው መጥቶ ይህ'ኮ አርሴኒክ ነው ብሎ ከነገራችሁ፡ እና—እናንተም ነገሩን ችላ ብላችሁ መውሰዳችሁን ከቀጠላችሁ፡ በኋላ ለሚመጣው ጥፋት የራሳችሁ ችግር ይሆናል። አያችሁ?

787 አሁን ይህን አዳምጡ፦

> **ወንድ ከሴት አይደለምና፥ ሴቲቱ ግን ከወንድ ናት።**
>
> **ስለዚህ** ሴት **ከመላእክት የተነሣ በራሷ ላይ ሥልጣን ሊኖራት ይገባታል።**

788 ከእናንተ የሚያነብልን አለ? አንደኛ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች፡ ምዕራፍ 11፡ ከቁጥር 10 ላይ። ልብ ብላችሁ ከሆነ፡ "ሥልጣን" ይላል፡ (ለምን?) "ከመላእክት የተነሣ፡" አንደኛ ቆሮንቶስ፡ ምክንያቱም መላእክት ሲል ሰው ነው፡ መልእክተኞች ናቸው። ይኸውላችሁ፡ ትንሹ "a" ነው። መላእክትን በተመለከተ፡ የሰማይ መላእክትን ከሆነ፡ ትልቁ "A" ነው፡ ካፒታል "A።" ትንሹ "a" ከሆነ፡ ሰዎችን ነው።

> **ነገር ግን በጌታ** ዘንድ **ወንድ…** ወይም **ሴት፡… ሴት ያለ ወንድ—ወንድም፡ ያለ ሴት አይሆንም።**

**ሴት ከወንድ እንደ ሆነች፡ እንዲሁ ወንድ ደግሞ በሴት ነውና፡... ሁሉም ከእግዚአብሔር** ነው።

በእናንተ በራሳችሁ መካከል... **ፍረዱ፥ ሴት** ራስዋን ሳትሸፍን (ጸጉሯን ቆርጣ) **ወደ እግዚአብሔር ልትጸልይ** ይገባታልን? (አሁን አስቡት)

789 አሁን ተከታተሉ፦

**ወንድ ጠጉሩን ቢያስረዝም፡ ነውር እንዲሆንበት፡ ተፈጥሮ እንኳ እያስተምራ**ችሁምን፡...

790 "ስለ ምን ነበር፡" ብላችኋልን? ስለ ፀጉር። ጳውሎስ የሚናገረውን አትመለከቱምን? ፀጉር፡ ረጅም ፀጉር! ሴ... ሴቷ ረጅም ፀጉር ሊኖራት ይገባል። ቁጥር 14 አሁን፦

**ወንድ ጠጉሩን** ቢ**ያስረዝም፡ ነውር** እን**ዲሆን**በት፡ **ተፈጥሮ እንኳ፡ እያስተምራ**ችሁምን?

791 ተረድታችኋል? ለወንድ ፀጉር ቢያስረዝም ነውር ነው፡ ሴት ግን-... የሴት ድርሻ ነው። እግዚአብሔር ወንዱን ከሴት የተለየ አድርጎ፡ በጾታ እና በመልክ፡ እንዲሁም በሁሉ ነገር አደረገው። ልብሱን መልበስ የለባትም... መጽሐፍ ቅዱስ "ሴት ሱሪ ወይም የትኛውም የወንድ ልብስ ብትለብስ፡ በእግዚአብሔር ፊት ጸያፍና ርኩሰ የሆነ ጸያፍ ነገር ነው" ይላል። እግዚአብሔርም ዋጋ ያስከፍላታል። ማንን ትሰማላችሁ? ይህ ግን መጽሐፍ ቅዱስ ነው!

792 እናንተም እየዞራችሁ፡ "እንዴ፡ ሴቶችን ሱሪ ለብሶ ማየት... በጣም ቆንጆ ይመስለኛል።" እግዚአብሔር ግን የተለየ ስላደረጋቸው፡ የተለየ ልብስ እንዲለብሱ ይፈልጋል።

793 መፅሃፍ ቅዱስም፡ "ለሴት የወንድ ልብሰ መልበስ፡ አስጸያፊ ነው።" **አስጸያፊ** ምን እንደሆነ ታውቃላችሁ? "በእግዚአብሔር ፊት የቆሸሸ ነገር" ነው። ታላቁ ያሕዌም ሲመለከታችሁ እናንተን እንደቆሸሸ ነገር ያያችኋል... .መጽሐፍም እንዲህ ይላል...

794 እና እናንተ እንዲህ የምትሉ... አንዳንድ እመቤቶች ሆይ፡ በጉርምስና ዕድሜአቸው፡ አሥራ ሰምንት፡ ሃያ ዓመት የሆናቸው ሴት ልጆቻችሁን፡ አሁን እንደሚለብሱት አይነት ሆነው እንዲወጡ ትፈቅዳላችሁን!

795 አንቺም፡ ደግሞ፡ እናት ሆይ! አየሽ? ወጥተሽ እነዚህን ሱሪዎችና እና አሸንክታቦች እና እነዚህን ለብሰሽ... ጎዳና ላይ ትወጪአለሽ፡ እ—እና አሁን በዚህ ዘመን የሚሰሯቸው አይነቶች፡ የተበላሹ ልብሶችን ለብሰሽ ያልሆንሺውን እንድትመሰዪ ያድርጉሻል። አየሽ? ሴሰኛ መሰለሽ ጎዳና ላይ ትወጭአለሽ፡ ምናልባት ለባልሽ እና ለሁሉም ነገር ንፁህ እና ንጽህት ልትሆኚ ትችያለሽ፡ ነገር ግን መንገድ ላይ ከወጣሽ እና አንድ ሰው ቢያይሽ እራስሽን በዚያ መልክ ስላቀረብሽ፡ ጥፋተኛ ነሽ፡ በፍርድ ቀን እንዲህ ካዩሽ ሰዎች ሁሉ ጋር ዝሙትን ስለፈፀምሽ መልስ ትሰጫለሽ። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላልና።

796 መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፦ "ወደ ሴት ያየ ሁሉ የተመኛትም፡ ያን ጊዜ በልቡ ከእርሰዋ ጋር አመንዝሯል፡" ስለዚህ አንቺም በዚህ በደለኛ ነሽ ቢሆንም...

797 በፍርዱ ፊት ቀርበሽ እንዲህ ትያለሽ፡ "ጌታ ሆይ፡ አንተ ልቤን ታውቃለህ፥ አመንዝሬ አላውቅም፡ ለባለቤቴ ታማኝ ነበርኩ።"

798 ነገር ግን አንድ ሰው እዚህ ቆሟል፡ ሌላ ሰውም እዚህ ጋር፡ እዚህ ሌላ፡ ሌላ፡ ሌላ፡ አሰራ አምስት፡ ሀያ፡ ሠላሳ፡ አርባ ጥፋተኞች ተብለው ቆመዋል፡ "የዝሙት ጥፋተኞች ተባሉ!" ለምን? አንቺን በመመልከታቸው።

799 "እንዴ፡ እኔ ከሱ ጋር ምንም ግንኙነት አላደረግኩም።" ታዲያ፡ ለምን እራስሽን እንዲህ አድርገሽ አቀረብሽ? እግዚአብሔር ያንን እንዳትለብሺ አዞሽ ሳለ፡ ይህን ማድረግ አስጸያፊ ሆኖ ሳለ፡ አንቺ ግን **ሁ ላብሰ ሱዚ**፡ ወይም ሌላ ለማዳመጥ ሄድሽ...

800 **የሱዚን ባል ማን** ይወደዋል የሚለውን አይታችሁ ምን እንደሆነ አስተውላችኋል? ሁላችሁም ይህን በቅርብ ጊዜ በጋዜጣ አይታችሁታል። በዋዮሚንግ፡ ካስፐር ውስጥ በነበርን ጊዜ፡ የወጣ ነው። ሰሙ ማን ነበር? ያ ሰውዬ... **ዊ ላቭ ሱዚ** ላይ፡ ወይም ምን ነበር—ምን እንደሚባል እንጃ? ኦ... ኦህ፡ እሮብ ምሽት ላይ ወደ ጸሎት ሰብሰባ ከመምጣት ይልቅ እቤት ውስጥ የምትመለከቱት ያ ትርኢት። ምንድን ነው? **ዊ ላቭ**... ርእሱ ማን ይባላል? [አንዲት እህት እንዲህ "**አይ ላቭ ሉሲ**፡" አለች።—አርታዒ።] **አይ ላቭ ሉሲ**፡ ባለቤቷ፡ የሚሆነው አካል፡ እዚያ ሬኖ፡ ኔቫዳ ውስጥ፡ ያውደለድላል፡ ከአንዲት ጥቁር ሴት ልጅ ጋር፡ ከእሷ ጋር ለዓመታት ግንኙነት ነበረው። እናንተም ይህንንም ለማየት ነው ወንጌልን ከመስማት ይልቅ፡ በቤታችሁ የምትቀመጡት። ሴትየዋ ተናዝዛለችና። አቤቱ፡ ማረን! ከኢየሱስ ክርስቶስ ሌላ ንፁህ የሆነ ነገር የለም!

801 ልብህን ይባርካት፡ ወንድሜ፡ አ—አንድ ነገር—እነግራችኋለሁ ወዳጆቼ፡ አንዳንዶች... እንዲህ ትላላችሁ፡ "ኦህ፡ ማይ፡ ዝርያዎችን ታያላችሁ።" በጣም መጥፎ ከተባሉት ጥንብ አንሳዎች—ስጋ ተመጋቢዎቹ፡ ጥቂቶቹ፡ ቆንጆ ወፎች ናቸው። ወፍን በላባው ልትፈርዱት አይገባችሁም፡ አያችሁ። ሰለዚህ ይሄን አትርሱት። ኦህ፡ ማይ!

802 አሁን ተከታተሉኝ፦

> **ተፈጥሮ እንኳን...** (ያ 14ኛው ቁጥር ነው)... ለወንድ ፀጉር ማሳደጉ እንደሚያሳፍር፡ **ይህ፡ አያስተምራችሁምን**? (ያ ለሴት የተሰጠ ነው።)

**ሴት ግን ጠጉርዋን ብታስረዝም፡ ክብር እንዲሆንላት፥...**

803 አሁን ሰለምን እያወራ ነው? እናንተ ካቶሊኮች ለቤተክርስቲያን የምትለብሱት ጨርቅ ማለቱ ነውን? በፍፁም! በራሳችሁ ላይ ጣል ሰለምታደርጉት መሸፈኛ፡ መሃረብ ነውን? የሚያወራው ሰለ ፀጉርሽ ነው!

804 እንግዲህ! ሴት ፀጉሯን ብትቆርጥ፡ ክብሯን ትቆርጣለች፡ እናም ወደ መሠዊያው ሄዳ እንድትጸልይ አልተፈቀደላትም። አያችሁ፡ በትክክል እዚህ ላይ እንዲህ ይላልና፡ "ሴት ራሷን ሳትሸፍን ብትጸልይ ተገቢ ነውን?" እንደሚለውም፡ እዚህ ጋር እንዲህ ይላል፡ "እንግዲያውስ፡ ፀጉሯን ደግሞ ትላጭ" ይላል። እንግዲያውስ መላጣ ደግሞ ትሁን። "እስክትመለጥ ድረስ ከተላጨችም፡" "ይህ ውርደት ነው፡ ለሴት እንዲህ ማድረጉ አሳፋሪ ነውና፡"

ይላል። ስለዚህ “መሸፈን አለባት፡” አለ። አሁን፡ የጳውሎስ ደብዳቤ እ— እያነበብኩ ነው። ሁላችሁም፡ የራሳችሁ ውሳኔ ነው፡ አያችሁ።

ሴት **ግን ጠጉርዋን ብታስረዝም፡ ክብሯ ነው፥ ጠጉርዋ መጎናጸፊያ** ሊሆን **ተሰጥቶአታልና።**

805 ኮፍያ ተሰጥቷታል ይላልን? እናንተ ካቶሊኮች ወይም ፕሮቴስታንቶች፡ ማናችሁም፡ ወደ ቤተ ክርስቲያን የምትሄዱና ኮፍያ ለመልበስ የምትፈልጉ፡ “አሁን፡ ቤተ ክርስቲያን ልሄድ ነው፣ ኮፍያ ማድረግ አለብኝ፡” የምትሉ። አይደለም፡ ጸጉራችሁ ማሳደግ አለባችሁ። ልዩነቱ ይህ ነው። አያችሁ?

**... ፀጉሩ እንደ መጎናጸፊያ ተሰጥቶታልና።** (ሳትሸፈን ወደ ቤተ ክርስቲያን መግባት፡ ወደ መሠዊያው ሄዳ መጸለይ ለእርሰዋ ነውር ነው።)

**ሰው ግን እ—እንዲህ የሚመስለው ከሆነ...** (ይህን ቃል መጥራት እንደምችል አላምንም፡ c-o-n-t-e-... )... **አከራካሪ— አጨቃጫቂ** (አከራካሪው ምን እንደሆነ ታውቃለህ)፡ **እኛ ብንሆን የእግዚአብሔር** ቤተክርስቲያንም **ቢሆን፡ እንደዚህ አይነት ልማድ የለንም።**

806 አሁን ስለሱ መከራከር ከፈለጋችሁ፡ ተከራከሩት። እሺ፡ ስለዚህ ጉዳይ መጨቃጨቅ ከፈለጋችሁ፡ “ኡህ፡ ለእኔ ምንም ለውጥ አያመጣም። ተውአቸው ያደርጉት። እሰቲ፡ ለኔ ትርጉም የለውም። እ... ዋናው ነገር፡ ስለ ፀጉር ሳይሆን፡ ስለ ልብ ነው።” እውነት ነው፡ ልብ ከተስተካከለ፡ ፀጉሩም ይስተካከላል (ኧሃ-ሃህ)።

807 ቀጥሉ፡ መጨቃጨቅ ከፈለጋችሁ፡ ጳውሎስ እንዲህ አለ፦ “እኛም የእግዚአብሔር ቤተክርስቲያንም፡ እንደዚህ አይነት ልማድ የለንም የላትም።” “የቃየን ወገን መሆን ካማራችሁ፡ እንግዲያውስ፡ ቀጥሉ፡” አለ። ጳውሎስ ግን የተናገረው ይህ ነው።

808 ኡህ፡ ለመሳቅ አይደለም፡ ምክንያቱም ምንም የሚሳቅበት ነገር የለም። እኔ ግን እላችኋለሁ ወዳጆቼ፡ ይህን ሁሉ እንድናደርግ መፈቀዱን ማየት ያሳፍራል። እ...

809 አዳምጡ! እናንተ ግን፡ ውድ እህቶቼ፡ አቀራረባችሁን እንድትጠነቀቁ፡ እና የራሳችሁን ምርጥ ነገር እንድታደርጉ እፈልጋለሁ። እንደዚህ መሆን አለባችሁ። እና ባል ሲመጣ የቻላችሁትን ያህል ጣፋጭ እና ፍሬሽ እና ሁሉንም ነገር መሆን አለባችሁ፡ ልክ እጮኛሽ በነበረ ጊዜ እንደነበረው ይሁንላችሁ። በመሳም— በበር ላይ ልትቀበይው ይገባል ባልሽ እንዲሆን በመሠዊያው ላይ የሳምሽው ቀን እንደነበረ ያህል ለእርሱ ጣፋጭ ሁኚ። ልክ ነው። በተቻላችሁ ቆንጆ ለመሆን የተሻለ ለመሆን መጣራችሁ አልወቅሳችሁም። እና እግዚአብሔር ያውቃል፡ እንደዚያ እንድትሆኑ እፈልጋለሁ።

810 ከጥቂት ጊዜ በፊት፡ ከጃክ ሹለር ጋር እየተነጋገርኩ ነበር። ስለ ጃክ ሹለር ሲባል የሰማ ሰው አለ? ሜቶዲስቶች ያላቸው በጣም ታዋቂው ሰባኪ ነው። እንዲህ አለ፡ “አንዲት ሴት መጣችና እንዲህ አለች... ፀጉሯ ቆሽሸዋል፡ ማስቲካ-

እያኘከች፡ ግማሽ እርቃኗን ሆና፡ እንዲህ አለች፡ 'ታውቃለህ፡ ባለቤቴ ከእንግዲህ ሊታገሰኝ አልቻለም።'"

811 እርሱም "እኔ አልወቅሰውም፡" አላት።

812 እውነት ነው። እሺ፡ ማድረግ ያለባችሁ ነገሮች ግን፡ በትክክለኛው መንገድ ማድረግ አለባችሁ። ፍሬሽነታችሁ እና ውበታችሁ፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በእግዚአብሔር ፊት ፈልጓቸው እንጂ፡ ወጥታችሁ ከሆሊውድ አትፈልጓቸው። እመቤት ሁኚ፡ እንደ እመቤት ተመላለሺ፡ እንደ እመቤት ልበሺ፡ ንጹህ ሁኚ። እንደ እመቤት ሁኚ፡ አሸንክታቦች አይሁኑልሽ...

813 ሚስቱን ወደ ውጭ እንድትወጣ እና እነዚህን ርካሽ አሸንክታቦች ለብሳ በወንዶች ፊት እንድትወጣ የሚፈቅድ ሰው ሁሉ፡ በእነዚህም አጫጭር አሸንክታቦች... ውጭ ወጥታ የግቢውን ሣር እንድትከረክም፡ እና ሌላ ነገሮች እንድታደርግ የምትፈቅድላት ሰው ሆይ፡ አንድ ነገር እነግርሃለሁ፡ ወንድሜ! እ—እኔ ክፉ ለመሆን ፈልጌ አይደለም፡ ከልቤ እንደሆነ እ... እግዚአብሔር ያውቃል። ግን ማድረግ አለብኝ... የእኔን ያንን ለማድረግ ከመፍቀዴ በፊት ብዙ መለወጥ አለብኝ። እኔ የቻልኩትን ያህል በከፍታው ላይ መሪ እሆናለሁ፡ አየህ፡ እኔም ማድረግ ባልችል ጊዜ፡ እተወዋለሁ። እውነት ነው።

814 ኧረ፡ ወንድሜ ሆይ፡ ያን ማድረግ ለሴቶች አሳፋሪም ነውርም ነው። እና እ—እህቴ ሆይ፡ እንዲህ ማለቴ አይደለም... እ—እናንተን ለማዋረድ አይደለም፡ ማለት የፈለግኩት... ሰዎች እንዲሁ ይመጣሉ እንጂ፡ የቤተክርስቲያን አባላት የሉንም። ይህ ግን የእግዚአብሔር ቤት ነው፡ እና ለሰዎች እነዚህን ነገሮች እንዳይለብሱ በግልፅ እንናገራለን። ስለዚህ... ለዚህም በፍርድ ቀን መልስ ትሰጡበታላችሁ። አሁን እዚህ ጋር በደንብ ተከታተሉኝ። እና ፀጉርሽ ይደግ፡ እሺ፡ እመቤት ሁኚ።

815 አሁን፡

> **ነገር ግን በምትሰበሰቡበት ጊዜ... ለሚከፋ እንጂ ለሚሻል ስላልሆነ፡ ይህን ትእዛዝ ስሰጥ**... **የማመሰግናችሁ፡ አይደለም።**
>
> **በመጀመሪያ፡ ወደ ማኅበር ስትሰበሰቡ፡ በመካከላችሁ መለያየት** እንዳለ **እሰማለሁና፥** በአንድ በኩልም አምናለሁ፡... (አሁን ወደ ጌታ እራት ማዕድ አልፏል)

816 አሁን ይህንን አዳምጡ። ለዛም ነው መላእክቱ...

817 አሁን፡ ወንድም ፓልመር ሆይ፡ በዚህ ካሴት ለአንተ አልናገርም እኔ እዚህ እንደማደርገው ያንኑ ነገር እዚያ ሰበክ አልልህም። አንተ እራስህ ግን ሰባኪ በመሆንህ፡ መልካም እና በጎ ታውቃለህ፡ ወንድሜ ሆይ፡ እውነት እንደሆነ አንተ ታውቃለህ። በጣም ጥሩ።

818 ስለዚህ እነዚህ **መላእክት** "ሰዎች" ናቸው። ካስተዋልክ፡ ወንድም ፓልመር፡ በትንሿ ሆሄያት፡ "መላእክት" ነው። መጽሐፍ ቅዱስም በመቀጠል... ስለ ወንድና ስለ ሚስቱ እያወራ ነው፡ አየህ፡ ጉዳዩ ያ ነው።

819 ሰዎች ከመጽሃፍ ቅዱስ ጋር ግራ እንዲጋቡ የሚያደርጋቸው ይህ ነው፡ እንዲህ ይላሉና፡ "እንዴ፡ እግዚአብሔር እዚህ ጋር አንድ ነገር አለ፡ **እዚህ** ጋር

ደግሞ... ” አይ፡ ከርዕስ የወጣኸው እ—እንተ ነህ። በርዕስ ላይ ብቻ ቆይ፡ በቃ። ስለ ወንድና ስለ ሚስቱ እያወራ ነው።

820 አሁን ከመጨረሳችን በፊት ልነካው የምፈልገው አንድ ተጨማሪ ነገር ልናገር፡ ሁለት ደቂቃ ያህል ይወስድብኛል፦

## 74. ከ-ሺህ-ዓመት መንግሰት በኋላ ቅዱሳን የት ይሆናሉ? እና ምን ዓይነት አካል ይኖራቸዋል?

821 ይህ ጥያቄ በጣም ደስ የሚል ሆኖ አግኝቼዋለሁ፣ በጣም ወድጄዋለሁ። አሁን ጠለቅ ብለን እንመርምር።

822 በመጀመሪያ፡ እግዚአብሔር... ለጥቂት ደቂቃዎች ትምህርታችንን በዕብራውያን እንቀጥላለን። እግዚአብሔር ባለ ሰባት ቀለማት ታላቁ የምንጭ ፏፏቴ ነበር። ሰንቶች ታውቃላችሁ? እያችሁ? እግዚአብሔር ሰባት መናፍስት እንዳሉት ሰንቶች ታውቃላችሁ? ፍፁም፡ ሰባት መናፍስት። በጉም ሰባት ዓይኖች ነበሩት፡ ወዘተ፡ አሁን ሁሉም ወደ አንድነት እየመጡ ናቸው። እያችሁ? አሁን፡ እግዚአብሔር ያ ነበር።

823 አሁን እርሱ ማለት (ሎጎስ) ከእግዚአብሔር በወጣ ጊዜ፡ እርሱም እግዚአብሔር ከዚያ ታላቅ ምንጭ መጥቶ በ—በሰው አምሳል ወደ አካል መጣ፥ እና ቴዎፋኒ ብለን የምንጠራውን ሎጎስ፡ እንዲሆን ያደረገው ይህ ነው።

824 አሁን፡ ቲዮፋኒውን ከተመለከታችሁት፡ ሲታይ ሰው ነው። አሁን እኛ... አሁን፡ መጀመሪያ ላይ የነበርነው በዚያ መልክ ነበር። አሁን፡ አሁን አይገባችሁም፡ ድሮ በመጀመሪያ ግን በዚያ መልክ ነበራችሁ። ሰው ሲፈጠር... እግዚአብሔር ሰውን በመልኩ ሲፈጥር፡ ቲዮፋኒ ሠራ። እርሱንም በሥጋ ውስጥ አኖረው... እግዚአብሔር ሰውን በመልኩ፡ በአምሳሉ ሲፈጥር፡ እንዲህ ነበሩ... በዘፍጥረት 2 ላይ፡ አለ... ወይም በዘፍጥረት 1፡28 ላይ፡ ያለ ይመስለኛል፡ “የሚያርስ የሚያርስ ሰው አልነበረም፡” እግዚአብሔርም ወንድና ሴት አድርጎ ፈጥሮ ነበር። ልክ ነው፡ “ምድርን የሚያርስ ሰው አልነበረም።”

825 ከዚያም እግዚአብሔር ሰውን በትንሹ ዝቅ አድርጎ በእንስሳት ሕይወት ውስጥ አስቀመጠው፡ ይህም ይህ አካል ነው፡ መሬትን ያርሳት ዘንድ፡ ይነካትም ዘንድ እንደ እንስሳ አደረገው። ይህ ቲዮፋኒ እኛ እንዳሉን የስሜት ህዋሳት፡ አይነካም፡ አያይም፡ አይቀምስም፡ አይሰማም፡ አይሰማም። ስለዚህ እግዚአብሔር ሰውየውን—ስሜት እንዲኖረው እና እንዲዳሰስ አድርጎ አኖረው።

826 እ—እና በኤደን ገነት ውስጥ ሲመላለስ፡ መጀመሪያ ቲዮፋኒ ነበር (አሁን እዚህ እየተመላለሰ እንዳለ እንደ መንፈስ ቅዱስ)፡ እንስሳትን ህይወት ይመራ ነበር። በሁሉ ላይ ተቆጣጣሪ ነበር፡ ምድሩን ግን ማረስ አልቻለችም፡ እያችሁ። እግዚአብሔርም ምድሩን እንዲያርስ በሥጋ አኖረው። አምስቱን የስሜት ህዋሳቱን ሰጠው፡ መሬቱን እንዲያለማ እና ወይን—እና ሁሉንም ነገር—እንዲንከባከብ፡ ነገር ግን ሰውየው አሁንም በብቸኝነት የሚሰቃይ ይመስላል። ኦህ፡ እንዴት የሚያምር ምሳሌ ነው።

827 እነሆ፡ በመጀመሪያ ሲፈጠር፡ ሁለት ሰዎች አንድ ላይ ተፈጥረዋል። ሰው የተፈጠረው፡ ወንድና ሴት ሆኖ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል።

እግዚአብሔር ሰውን ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠረው፡ "ፈጠረው።" ልብ በሉ፡ እንግዲህ የሰው ልጅ ከቲዮፋኒው ተለይቶ ወደ ስጋ ሲገባ፡ ሙሉ በሙሉ—ያለቀለት አልነበረም፡ የፍጥረቱ ክፍል አሁንም ቲዮፋኒ ነበር፡ ስለዚህ ልክ ያልሆነ ነገር ነበረው።

828 ከከብቶች ወንድና ሴት ሆነው ይሄዳሉ፡ ፈረሱም እንዲሁ፡ በሬውም እንዲሁ፡ ሌላውም ሁሉ ጥንድ ሆኖው፡ ይሄዳሉ። አዳም ግን፡ የ... የሆነ... ነገር፡ የጎደለው ነገር ነበረ። ይህ ፍላጎቱ የትዳር አጋር እየጠበቀው እንዳለ ያሳያል። ገባችሁ? እዚህ እንሞታለን የሚለው አሳባችን ራሱ፡ በመጨናነቅ እና በድንጋጤ ውስጥ መሆናችን፡ ሞት የሌለበትን ህይወት ስንናፍቅ፡ ይህ እንደሚጠብቀን ያሳያል። አያችሁ?

829 አዳምም ብቸኛ ነበር። እግዚአብሔርም፡ ሊለያዩ እንዳልቻሉ ለማሳየት... አሁን ወደዚያው ነገር፡ ከእፍታ በኋላ እመለሰበታለሁ።

830 ይኸውላችሁ፡ ሄዋንን ሲያበጃት አፈር አላነሳም፡ ነገር ግን ከቀደመው ከዋናው አፈር፡ ከአዳም አበጃት። ከጎኑ የጎድን አጥንት ወስዶ ረዳት አደረገላት፡ ሔዋንም ሆነች። ለወንዱ ተሰራች፡ የወንዱ አካል ናትና። እሷ በመጀመሪያ፡ በፍጥረት፡ በቲዎፋኒ ውስጥ የእሱ አካል ነበረች። በዚህ ፍጥረት ውስጥ የሱ አካል ነበረች። በሌላ ፍጥረት፡ ልትነጣጠል አልቻለችም፡ ከአንድ ፍጥረት መምጣት ነበረባት።

831 ክርስቶስ እና እግዚአብሔር በትክክል አንድ አካል መሆናቸው ለዚህ ነው፡ ካልሆነ ግን ሌላ ሊሆን አይችልም። እርሱ መልካም ሰው ወይም ተራ ነቢይ ቢሆን ኖሮ፡ ቤዛ ባልሆነም ነበር፥ እሱ ራሱ ፈጣሪ መሆን ነበረበት። እሱ ግን ልክ ያኔ እንደነበረ፡ አያችሁ፡ አሁንም ቲዮፋኒ ነው።

832 ስለዚህ ሰው ወደዚህ ወረደ እነሆም—ድንቅ ነበር፥ እግዚአብሔርም በዚህ ደስ ተሰኘ፡ እንዲህም አለ፡ "እነሆ ይህ መልካም ነውና፡ በምድር ላይ ይኑሩ ሁሌም በዚያ ይቀመጡ። ይኼው ነው፡ ለ—ለዘለአለም፡ ቀጣይ እና የማይቋረጥ። እንዲሁም እያንዳንዱ ተክል፡ እና ሃመልማል ሁሉ ይብቀል፡ ይደግም። ሰውም ህያው ይሁን፡ እንሰሶችም፡ ሌላውም ሁሉ ይኑሩ፡ ለዘለአለም እና ዘለአለም። ይኸው ነው።" አያችሁ?

833 ከዚያም ኃጢአት ገባ። ይህን አሳብ ማስቀመጥ እፈልጋለሁ። ብ... ብዙ ሰዎች በዚህች አንዲት ቃል ላይ ታላቅ ስህተት ያደርጋሉ፡ ቃሉም በመዝሙሩ 23 ይገኛል። እንዲህ ያነቡታል፡ "እነሆ፡ በሞት ጥላ **በጨለማው** ሸለቆ ውስጥ ብሄድም።" ይኸውላችሁ፡ እንደዚህ ያለ ነገር የለም። መጽሐፍ ቅዱስ፡ እንዲህ አይልም፡ "በጨለማው ጥላ ሸለቆ... በሞት ጥላ በጨለማው ሸለቆ።"

834 የሚለው፡ "በሞት ጥላ ሸለቆ ውስጥ ብሄድም እንኳ።" አሁን፡ ጥላ ከመውጣቱ በፊት፡ ጥላ ለማድረግ ብርሃን መኖር አለበት። አያችሁ፡ ዳዊት ነቢይ ሆኖ በቅብዓቱ ሥር ሆኖ፡ ስህተት አልሰራም፡ ዝም ብሎ እውነቱን ተናገረ፥ "አዎን፡ ብሄድም እንኳ... " **በጨለማ** ሸለቆ ውስጥ፡ ሳይሆን፡ "በሞት **ጥላ** ሸለቆ ውስጥ፡" ነው።

835 አሁን ጥላ ለማውጣት የተወሰነ የብርሃን መጠን መኖር አለበት። እዚህም እንደዛ ነው። እኛ ፍጥረታዊ እና መንፈሳዊ ነን። ይህ አካል ሞት ሟች ነው፡ እና ወደ ዓለም በሴት መጣ፥ በምንም ሳይሆን በ... በእግዚአብሔር አይደለም፡

በመዋለድ የአዳምና የሔዋን ውጤት ናችሁ። ጥቁር፡ ነጭ፡ ወይም ምንም ይሁን ምን፡ የአዳምና የሔዋን፡ ፍሬ ናችሁ። ስለዚህም ሰውነታችሁ "በኃጢአት የተወለደ፡ በዓመፅም ተወለደ፡ ሐሰትን እየተናገረ ወደ ዓለም የገባ ነው።" ገና ከጅምሩ ያለ አንዳች፡ ባለመታደል፡ ህይወታችሁ ከጅምሩ የተወገዘ ነው።

836 እንግዲያስ፡ በእናንተ ዘንድ የመጣው መንፈስ በተፈጥሮ ስለሆነ፡ በተፈጥሮም በጾታ ግንኙነት የተላለፈ በመሆኑ፡ በወንድና በሴት መካከል ያለው ምኞት ምድራዊ ልጅን ይወልዳል። እና ህጻኑን ከተዋችሁት፡ ምንም ጥሩ ነገር ካልተማረ፡ መጥፎ ይሆናል። ትክክልም ሆነ ስህተትን አታስተምሩት፡ ስህተት ይወስዳል። ምክንያቱም ይህን ማድረግ ተፈጥሮው ነው።

837 ህጻን ልጅን ተመልከቱት፡ **ከዚህ** እንኳ የማይበልጥ ሲሆን፡ ቁጡ ይሆናል፥ እንደው በቃ... እ—እጆቹን እያወናጨፈ፡ ፊቱ ቀልቶ፡ ሲቃ ይይዘዋል። በእውነት። ምንድነው ይሄ? ተፈጥሮው ነው። ከአባቱ ወይም ከእናቱ፡ ከአንዳቸው ወርሷል፥ ክብ መጋዝ ጋር ለመጣላት ቁጡ ትሆናለች፡ ከአባቷም ሊሆን ይችላል። ከእነሱ ካልሆነ፡ ከወንድ አያት ወይም ከሴት አያታቸው ይሆናል። አያችሁ፡ ዘር ነው።

838 ስለዚህ... የተወለዳችሁት ወደ አለም ነው። ወደዚያም በተፈጥሮ መጣችሁ፡ ሁለንተናችሁ ጨለማ እና ረግረግ ነው፡ የተወገዘ፡ የተረገመ ወደ ገሃነም የሚሄድ ነው። በትክክል!

839 ዳግመኛ ስንወለድ ግን የእግዚአብሔር ብርሃን በዛች ነፍስ (ሃሌ ሉያ) ውስጥ ይበራል፡ ያኔ ግን ጥላ ያለው ሽለቆ እንጂ፡ ጨለማ ያለው ሽለቆ አይደለም። እዚህ በሥጋ እና በተለያዩ ነገሮች፡ ፊታችንን በሚሸፍኑ ነገሮች ትሸፈኑ ይሆናል፡ ነገር ግን በዚያ በቂ ብርሃን አለ። እናም አንድ ቀን ይህ ብርሃን እና ጨለማ መለያየቱ አይቀርም! ብርሃንም ሲበራ፡ ጨለማው ይጠፋል። ከክርስቶስ ጋር ለመሆን ስንሄድ፡ በዚያ አካል ውስጥ ጨለማ እና ሞት ይጠፋሉ፡ እናም ወደ ፍጹም ብርሃን እንነሳለን። ክብር ለእግዚአብሔር! ይኸው ነው፥ ከእንግዲህ በሽታ አይኖርም፡ ጨለማም ከእርሱ ጋር አይደባለቅም።

840 አሁን ህመም እና ደስታ አለን፡ ጤናም ጥንካሬም አለ፡ **ከፍታ** እና **ዝቅታም** አለ፡ **ውጣ ውረድም** አለ፡ ደስታና ሀዘን፡ ሁሉም አይነት ነገር አለን። እነዚህም፡ ጥላ ብቻ ናቸው። ማዶ ላይ ብርሃን እንዳለ የምናውቅበት በቂ ብርሃን አለበት፥ አሁንም በዚህ አካል፡ በሥጋ ነን። አንድ ቀን ግን ጎህ ይቀዳል። የሞት መልአክ በአልጋው እግር ስር የሚወድቀው ያኔ ነው፡ ዶክተሩም አለቀ የሚለው ያኔ ነው፥ እና ፍጥረታዊው ከመንፈሳዊው ውጭ ይሆናል፡ ብርሃኑም ወደ ብርሃን ይመለሳል፡ ጨለማውም ወደ ጨለማው ይመለሳል። ከዚያም ይህ ሟች አካል የማይሞተውን ይለብሳል። ይህ በሰባሽ አካል የማይበሰብሰውን የሚለብሰው ያኔ ነው። ያኔ ይህ ሟች የማይሞተውን በለበሰ ጊዜ፡ ከጊዜ ፍጥረት ወደ ዘለአለማዊ ፍጥረት እንለወጣለን። በድቅድቅ ጨለማ ወደዚያ መውጣት አይቻላችሁም፡ በጨለማው ውስጥ ብርሃን መኖሩ የማይቀር ነው። ይኸው ነው። የምትቀበሉት አካል ያ ነው።

841 841 ምን እየሰራን ነው? እንግዲህ፡ ውድ የተቀደሰክ ወንድሜ፡ ውድ የተቀደሰሽ እህቴ ሆይ፡ አለም ሳይፈጠር በፊት፡ እንቺን በመልኩ ሲፈጥርሽ፡ ወይም ወ—ወንዱን በመልኩ ሲፈጥረው፡ ሴትን በወንድ አምሳል ለወንድ

ክብር በፈጠራት ጊዜ፡ ቲዮፋኒ አደረጋችሁ። ልክ እንደራሱ፡ ለፈጠራቸው ፍጥረታት “እንፍጠር” ሲል፡ “ሰውን በአርአያችን፡ በአምሳላችን፡ ቴዎፋኒ እንፍጠር።” እግዚአብሔር ገና ሥጋ አልሆነም፡ በቲዮፋኒ ውስጥ ነበር።

842 ሙሴም አይቶታል። ሙሴም፡ “ጌታ ሆይ፡ እንዳይህ ፍቀድልኝ” አለው።

843 “ወደዚያ ሂድና፡ በዓለት ንቃቃት ውስጥ ተሸሸግ፡” አለው። ሙሴም ወደ ንቃቃት ገባ፥ እግዚአብሔርም ባለፈ ጊዜ፡ መብረቅና ነጐድጓድ... እግዚአብሔርም ሲያልፍ፡ ጀርባው **እንዲህ** አዞረ፡

ሙሴም “የሰው ጀርባ ነው፡” አለ። ሃሌሉያ!

844 ማን ነበር? የወረደው መልከ ጼዴቅ፡ የሳሌም ንጉሥ፡ አባትና እናት የሉትም፡ የቀኖች መጀመሪያ ወይም የህይወት ፍጻሜ የሌለው። እርሱ ነው! እርሱም ወረደ። ከአብርሃም ጋር የተነጋገረው እርሱ ነው፥ እርሱም እንደዚያ አይነት ትንሽ ሥጋ አደረገ፡ እና “እፍፍ!” እፍ ብሎ ገባበት፡ ወርዶም፡ የጥጃ ሥጋ በላ፡ የላም ወተት ጠጣ፡ ቅቤና የበቆሎ እንጀራ በላ። ከሁለቱ መላእክት ጋር።

845 ወደዚያ ሲሄዱ፡ ሁሉም ነገር “እፍፍ!” ብሎ ጠፋ፡ እልም ብሎ ጠፋ።

846 ስለዚህ ጉዳይ አሰቤ አላውቅም። ከተወሰነ ጊዜ በፊት፡ የጠመንጃ ካርትሪጅ እየጫንኩ ነበር፡ ባለ 22 ረጅም ጠመንጃ ነበረኝ፡ 220 ስዊፍት ነው። እናንተ እዚህ የምትተኩሱ ወንድሞች ታውቁታላችሁ። ይህች ትንሽ ጥይት፡ ባለ አርባ-ስምንት ፍሬ ጥይት ናት፡ **ይሄን** ያክል ትረዝማለች፡ ተራ ባለ 22 ጥይት። የመቀባበል ኃይሉ ከ 30-06 ያህል ነው። አሁን እኔ... የፋብሪካው አቀባበል በሰከንድ ወደ አራት-ሺህ አራት መቶ ጫማ ይደርሳል። እና፡ በበቂ ሁኔታ ካስተካከላችሁ ግን... እራሳችሁ ስታቀባብሉት፡ በሴኮንድ እስከ አምስት ሺ ጫማ ድረስ ይደርሳል። እ—እና በሌላ አነጋገር፡ ብትተኩሱ... በቀደም፡ ሁለት መቶ ሜትሮች ላይ፡ ተኩስንበት ነበር፡ እና ሽጉጡ ከማስተጋባቱ በፊት፡ ጥይቱ አቧራውን መታ። ይሄን ያህል ፈጣን ነው።

847 ስለዚህ ስቴኪኒ ይዛችሁ (የስቴኪኒውን ጠፍጣፋውን ክፍል ታውቁታላችሁ) እና ባሩድን አፍሳችሁ ይህንን ነገር በባሩድ ሙሉት፡ ምናልባት አራት ወይም አምስት ትናንሽ ጥይቶች፡ እና እዚያ ላይ አሰቀምጣችሁ፡ ጥይታችሁን በዚያ ላይ አድርጉ። ባላችሁበት፡ በሴኮንድ ውስጥ ጥይቱን በእጃችሁ ትይዛላችሁ። ያኔ በሁለት መቶ ጫማ ርቀት የተቀመጠውን የሜዳ አሳማ ላት ተኩሱት፡ እና የሚዳ አሳማው አይንቀሳቀሰም። ጥይቱ ወደ መጀመሪያው ሁኔታ፡ ወደ ጋዞች ይመለሳል። ከመዳብ እና ከሊድ ድብልቅ የተሰራ ጥይት፡ እና በሰከንድ ውስጥ፡ መልሳችሁ ማግኘት ወደማትችሉበት ደረጃ ይለወጣል። ከመቶ ቢሊዮን ዓመታት በፊት ወደነበረው፡ ወደ ጋዞች ይመለሳል። እነዚህ ጋዞች መጠናከር እና መዳብ እና ሊድ ወደ መሆን እንደገና ማምራት እና እንደዛ መሆናቸው፡ አይቀሬ ነው። ጋዞቹ ማረፋቸው አይቀሬ ነው።

848 ስለዚህ፡ ይኸው። እኛም እዚህ ያለነው እንደዚህ ነው፡ የመጣነው ከፍ ካለ አካል ነው። በመጀመሪያ በእግዚአብሔር መልክ ነበርን። መጋረጃው እና ጨለማው አሁን እንዳንገነዘበው አድርገውናል። ኢየሱስ ግን “ዓለም ሳይፈጠር ከእነርሱ ጋር እንደነበረ” ለደቀ መዛሙርቱ ነግሯቸዋል። አያችሁ? አዎን ነበርን! አሁን ላታውቁት ትችላላችሁ፡ ግን መጀመሪያ ላይ ነበራችሁ። “እናም ይህች በምድር የምንኖርበት ድንኳን ቢፈርስ፡ እነሆ ሌላ ይጠብቀናል!” ሃሌሉያ! እናም

ወደዚህ ቲዮፋኒ ውስጥ፡ ያኔ ድሮ ወደ ኖርንበት፡ ለመብላት እና ለመጨባበጥ እንገባለን። ከመሠዊያው በታች ያሉት ነፍሳት፡ “አቤቱ ጌታ ሆይ፡ እስከ መቼ ነው” እያሉ ይጠይቃሉ?

849 ወደ እግዚአብሔር የሚመሩ ሰባት ደረጃዎች አሉ፡ ለሰባት መናፍስት—እንደ ደረጃ መልክ። እሺ፡ በእግዚአብሔር በመሰውያው ስር ስትቀርቡ፡ እንዲህ እያሉ ይጮኺሉ፡ “ጌታ ሆይ፡ እስከ መቼ? ከዚህ በኋላ፡ ወደ ኋላ መመለስ እንችላለንን? ”

850 እግዚአብሔርም አላቸው፡- “ገና ጥቂት ጊዜ፡ እንደ እናንተ ያሉ ሰዎች መከራን እስኪቀበሉ ድረስ ጠብቁ።” አያችሁ?

851 እናም ነፍሶች ተመልሰው ይመለሳሉ፡ እና እንደገና ወንዶች እና ሴቶች ይሆናሉ፡ እና ጨለማው እና ሞት እና ህመም እና የጥቁር ሀዘን ሁሉ ሲያልፉ ለዘላለም ይኖራሉ፥ ያኔ ፍጹም ከሆነው ብርሃን ውጪ፡ ሌላ ጥላ አይኖርም!

852 አዳምጡ። እዚህ ላይ ነው። የቱንም ያህል ቢጨልም፡ ጸሀይ ያን ሁሉ ጨለማ ለማድቀቅ ከባድ አይሆንባትም። ጨለማ እና ብርሃን ለረጅም ጊዜ አብረው ሊኖሩ አይችሉም። ምክንያቱም... የበለጠ ኃይለኛ የሆነው የትኛው ነው? ብርሃኑ ነው። ብርሃንም ሲበራ፡ ጨለማው ይጠፋል። ኣሜን። ደስ አይላችሁምን? ይህን በማወቃችሁ ደስ አይላችሁምን? ምንም ጥርጥር የለውም፡ አንዳች ጥላ እንኳን የትም አይቀርም። ነገር ግን ይህ አሁን በልባችን ውስጥ የበራው የተባረከ ብርሃን፡ የሚመሰክረው ነገር አለው፡ እርሱም የእግዚአብሔር ልጅ፡ የእግዚአብሔር ኃይል ነው።

853 ከዚያ ወደዚህ ገብተን፡ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ወደ ሰብሰባው ሲወርድ እናያለን፡ እና፡ “አንቺ ወይዘሮ **እከሊት-እና-እከሊት** ትባያለሽ፡ **እንዲህ** በሚባል ሰፍራ፡ **እንዲህ** አድርገሻል። በዚህ ምክንያት **ለረጅም** ጊዜ በደዌ ስትሰቃይ ኖረሻል፡ አሁን ግን የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡ ‘ተፈውሰሻልና፡ ተነስተሽ በእግሮችሽ ቁሚ።’” አንካሳ እና ዓይነ ሰውር በእግሩ ይነሣል። እና በካንሰር የተበላ ሰው፡ ከራሱ ጥላ ያለፈ ምንም ነገር የሌለው ሰው፡ ወደ ህይወት ይመለሳል ጤናን ያገኛል።

854 ምንም ጥርጥር የለውም፡ ኢየሱስም፡ “እኔ የማደርጋቸውን ሁሉ፡ እናንተም ደግሞ ታደርጋላችሁ።” “አብ አስቀድሞ ካላሳየኝ ምንም አላደርግም አለ፡” አለ።

855 ያ ምንድን ነው? አያችሁ፡ ከጨለማ ጋር ሊዋሐድ የመጣው፡ እኛን ሊቤዥን የመጣ ብርሃን ነው። ምን ማለቴ እንደሆነ ገባችሁ?

856 እነሆ፡ አንድ ቀን በቀጥታ ወደዚህ የሚመለስ ይሆናል፡ እናም ቲዎፋኒው የማይሞት ሥጋ ሆኖ እንደ ገና እንደ መጀመሪያው ሲሆን፡ ያን ጊዜ ኢየሱስ ይመጣል፡ እናም እግዚአብሔር... ይህም ክርስቶስ አንድ ይሆናል። ክርስቶስ በዙፋኑ ላይ ይቀመጣል፡ እና ህዝብ ሁሉ ሰዎች ይሆናሉ። ክርስቶስ በዳዊት ዙፋን ላይ ይሆናል፡ ጌታ ኢየሱስ፡ ሰው ይሆናል፡ መቼም አይሞትም። እኛም መቼም አንሞትም፡ መቼም አንታመምም፡ ከእንግዲህ አናዝንም፡ እናም የሺህ አመታት ዘመን እንኖራለን።

857 እናም በዚህች ምድር ላይ የሺህ አመታት ዘመን ሲያልቅ፡ ዲያብሎስ እንደገና ይነሣል፥ ያን ጊዜ ሁለተኛው ትንሣኤ ይመጣል፡ እርሱም የበደለኛዎች ትንሣኤ ነው። እንደ ባህር አሸዋ ያለ ብዙ ሰራዊት ሆነው ይሰበሰባሉ፡ መጥተውም የቅዱሳኑን ሰፈር ይከባሉ፡ ያን ጊዜም፡ እግዚአብሔር ከሰማይ እሳትና ዲን ያዘንባል ያጠፋቸውማል።

858 ዮሐንስም፡ "አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር አየሁ፡ ፊተኛይቱ ሰማይና ፊተኛይቱ ምድር አልፈዋልና፡ እናም ከዚያ ወዲያ ባህር አልነበረም። እኔም፡ ዮሐንስ፡ ቅድስቲቱ ከተማ፡ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም፡ ለባልዋ እንደ ተሸለመች ሙሽራ ተዘጋጅታ፡ ከእግዚአብሔር ዘንድ ከሰማይ ስትወርድ አየሁ።" ይኸው።

859 በዚያም ይላል፡ "ሚስቱ... በጉ እና ሙሽራይቱ ለዘላለም በዚያ ይኖራሉ።" አዲስ ምድር ይሆናል፡ ሚሊዮኖች እና ሚሊዮኖች ካሬ ሰፋት ያለው ይሆናል። ኦህ፡ ማይ። ከተማይቱም በመጽሐፍ ቅዱስ ልክ አንድ ሺ አምስት መቶ ስኩር ማይልስ ሰፋት ይኖራታል። ርዝመቷ አስራ አምስት ሺህ ማይል፡ ወርዷ አስራ አምስት ሺህ ማይል፡ ቁመቷም አስራ አምስት ሺህ ማይል ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ከተማዋ የሚሰጠው መግለጫ ይህ ነው። ባህር አለመኖሩ አይደንቅም፡ ለሱ የሚሆን በቂ ሰፍራ አይኖርምና።

860 እነሆ፡ እጅግ ውብ ይሆናል! በዚያም፡ ከእግዚአብሔር ዙፋን ላይ፡ በዙፋኑ ፊት የሚፈስ ምንጭ አላት። በህይወት ወንዝ በዛፉ... በሁለቱም በኩል አንድ ዛፍ አላት። በዚህ ዛፍ ውስጥ አሥራ ሁለት ዓይነት ፍራፍሬዎች ይኖራሉ፡ ፍሬውን በየወሩ ይሰጣሉ።

861 በዚያም ሃያ አራቱ ሽማግሌዎች አሉ። ሙሽሪት አለች። በዚያም አርባ አራት ሺህ፡ የቤተ መቅደሱ ጃንደረቦች አሉ። ወንድሜ ሆይ፡ ወደ አንድ ቦታ እንወሰዳለን! የሚጠብቁን ነገሮች አሉ። አራቱ... ሃያ አራቱ ሽማግሌዎች። መቶ አርባ-አራት ሺህ ጃንደረቦች። ሙሽራይቱ ከክርሰቶስ ጋር ትቀመጣለች። ኦህ፡ እንዲህ ትላላችሁ... ይኸው ቤቴ፡ ውቧ ቤቴ! ኣሜን።

862 ወደዚያ የመሄድ እድል እንዳለኝ፡ እና ወደዚያ የመሄድ እድል እንዳላችሁ አሰቡት እስኪ። ለምንስ በዚህ ጨለማ ውስጥ መሄድን እና ብርሃንን አለማየት፡ እና ሞትን እና ትርምሰ ውስጥ ገብታችሁ ይህን ትመርጣላችሁ? ብርሃን የበላይ የሆነውን ሥልጣኑን ሲይዝ፡ ለጨለማ ቦታ የለውም። ስለዚህ ሂዱና ብርሃን ሲመጣ ጨለማ ወዴት እንደሚሄድ መርምሩ። ሁሉ ነገር ወደ እግዚአብሔር የሚመለሰበት በዚያን ጊዜ፡ እንደዚያ ይሆናል። ይህም፡ ጨለማ መጀመሪያ ስላለው፡ ጨለማው መጨረሻ ይኖረዋል። ብርሃን ጅማሬ አልነበረውም ፍጻሜም የለውም። እግዚአብሔር መጀመሪያ ወይም ፍጻሜ የለውም። ስለዚህ፡ አንድ ቀን፡ ይህ ሁሉ ብልሹ ዓለም ከኃጢአቱና ከውበቱ ሁሉ፡ የሚወራለት-ነገሩ፡ ከነሙሉ ብርቅዬው እና ሰሜቱ ሁሉ፡ ማራኪነቱ ሁሉ እና ነገሩ ሁሉ ወደ ከንቱነት ይጠፋል፡ ሰፍራም አይገኝለትም። ከእንግዲህ አይገኝም፡ ከእንግዲህ አይታሰቡም! እንዲህም፡ ተብሏልና፡ "ከእንግዲህ መታሰቢያ የላቸውም።"

863 የጌታ ብሩካን ግን ሁሌም ከእርሱ ጋር ይሆናሉ። የከበረ ሥጋውን የሚመሰል አካል ይኖረናል፥ ከእርሱም ጋር እንኖራለን፥ ከእርሱም ጋር እንበላለን፥ ከእርሱም ጋር እንቀመጣለን፡ ከእርሱም ጋር ለዘላለምና ለዘላለም ከእርሱ ጋር

እንኖራለን፥ ለዘመናትም የማይቆጠር እና የዘላለም ዘመናት ፍጻሜ በሌለው ዓለም ውስጥ እንሆናለን።

864 ዛሬ ማታም ምርጫ አላችሁ። ወደዚያ ቦታ ለመሄድ ዝግጁ ካልሆናችሁ፣ የቱንም ያህል ቤተክርስቲያን ብትሄዱ፡ የቤተክርስቲያን አባል ብትሆኑም፡ ክርስቶስ በምትመላለሱበት ጨለማ ውስጥ አዲስ ሕይወት እስኪሰጣችሁ ድረስ ጠፍታችኋል። ሃይማኖተኛ ልትሆኑ ትችላላችሁ። ስሙኝ፡ ወዳጆች ሆይ፡ ሃይማኖታዊነት፡ ምሁራዊነት ነው። አያችሁ? የቃየን ልጆች ሁሉ ሁል ጊዜ ሃይማኖት ነበራቸው። ኢየሱስ በመጣ ጊዜ አይሁዶች ሃይማኖት ነበራቸው፡ መዳንን ግን ንቀውታል።

865 ዛሬ ማታም እጅግ ሃይማኖተኞች ልትሆኑ ትችላላችሁ። ፕሪስባይቴሪያን፡ ሜቶዲስት፡ ጴንጤቆስጤ፡ ናዝሪን፡ ፒልግሪም ሆሊነስ ትሆኑ ይሆናል። ምናልባት እንደ ሃይማኖተኛ፡ ወደ ቤተ ክርስቲያንህ ሄደህ ትመሰክር ይሆናል፡ ምናልባትም ትዘምራለህ ትጮኻለህ እንዲሁም ጌታን ታመሰግናለህ፡ ምናልባት አስራትህን ወደ ቤተ ክርስቲያን ታመጣለህ፡ ምናልባትም ባልንጀራህን በትክክል ታያለህ፡ ይህ ሁሉ ግን ከዘለአለማዊው መዳረሻህ ጋር በምንም አይገናኝም። ቃየንም ይህን ሁሉ አድርጓል። በትክክል።

866 መጽሐፍ ቅዱስም "ስንዴውና እንክርዳዱ አብረው ይበቅላሉ" ይላል። የስንዴ ቅንጣት ወድቃ፡ ዝናቡን ትጠማለች፡ እንክርዳዱም—እንዲሁ ነው። ዝናቡ በመጣ ጊዜ፡ ቁጥቋጦዎቹ ሁሉ ዝናቡን በማግኘታቸው ልክ እንደ ስንዴው ይደሰታሉ። "ነገር ግን፡ ከፍሬያቸው፡ ታውቋቸዋላችሁ።"

እንግዲያውስ ፍሬአችሁን እየመረመራችሁ ሳለ እንጸልይ።

867 አሁን፡ እግዚአብሔር አባት ሆይ፡ እዚህ ምሽት አንዳንድ አስቸጋሪ ጥያቄዎች ነበሩ። ምናልባት ትክክለኛውን ነገር አላደረግኩም፡ ነገር ግን የቻልኩትን ሁሉ አድርጌያለሁ፥ ልቤን ታውቃለህ። አምላኬ ሆይ፡ እንድትቀበለው፡ እጸልያለሁ። አሁንም፡ በእነዚህ ጉዳዮች፡ ምናልባት፡ አንዳንድ ነገሮችን በትክክል ካላቀረብኩኝ፡ አንተ የህዝቡን ልብ ተናገር እና በትክክል አቅርብላቸው፡ መሆን ባለባቸው ስፍራ አኑራቸው። አንተ እንደመከርከኝ አስባለሁና። መቼም ተሳስቼ ከሆነ፡ ይቅርታ አድርግልኝ።

868 እግዚአብሔር ሆይ፡ እያንዳንዱ ሰው እነዚህን ነገሮች ወደ ልባቸው እንዲወስድ፡ እንዲያሰላስሏቸው፡ እና አስፍተው እንዲህ እንዲያስቡ እጸልያለሁ፡ "አዎን፡ ቤተ ክርስቲያን አለ፡ እነዚህ ነገሮች አሉ። መጽሐፍ ቅዱስ የተናገረው ይህ ነው።"

869 ምናልባት እመቤቶች፡ ጌታ ሆይ፡ እነዚህን ነገሮች ስነግራቸው ማንንም ላይ እንዳላነጣጥር ታውቃለህ። ነገር ግን፡ እግዚአብሔር ሆይ፡ እኔ—እህቶቼን እወዳቸዋለሁ፡ ይህን ታውቃለህ፡ አባት ሆይ። ስለ እነርሱ ምን እንደማስብ አንተ ታውቃለህ። ነገር ግን እዚያ ቆሜ የውሸት ነገር ብነግራቸው፡ አስመሳይ እ—እሆናለሁ። ለእህቶቼ አስመሳይ መሆን አልፈልግም፡ እውነቱን ልነግራቸው እፈልጋለሁ። እናም፡ አባት ሆይ፡ ከቃልህ በትክክል እወስደዋለሁ።

870 አሁንም ወንድሞቼን አልፈርድባቸውም፡ ነገር ግን፡ ጌታ ሆይ፡ እነዚህን ነገሮች በመፍቀዳቸው ተሳስተዋል እላለሁ። ሴቲቱ ስለ ጉዳዩ ካወቀች በኋላ እንዲሁ ካደረገችው፡ ያ ስራዋ ነው፡ ፓስተሩ ጥፋተኛ አይደለም።

871 አባ አባት ሆይ፡ እነዚህ ነገሮች የአንተ ቃላት ናቸው፡ እነርሱም ለአንተ ናቸው። አሁን በህዝቡ ልብ ውስጥ ተናገር። ሁሉንም ለአንተ አደራ እሰጣለሁ። አንተ ያደረግከውን አያለሁ፡ አባት ሆይ፡ አንተ ታውቃለህ። ለእያንዳንዱ ልብ ተናገር። በክርስቶስ ስም እንጠይቃለን።

እና አንገታችንን ደፍተን ሳለን፦

872 አንድ ሰው እጁን አንሥቶ፡ እንዲህ የሚል ካለ እጠይቃለሁ፡ "ወንድም ብራንሃም ሆይ፡ ሙሉ በሙሉ አሸናፊ መሆን እንድችል አስበኝ፡ እና በመጨረሻው ቀን የሰርግ ልብስ ለብሼ ከክርስቶስ ጋር እሆን ዘንድ።" እጃችሁን አንሥታችሁ፡ "ጸልይልን፡" ትላላችሁን?

873 ሁላችሁም ጭንቅላታችሁን ዝቅ አድርጉ፡ እና ዝቅ በሉ። እግዚአብሔር ይባርካችሁ፡ ጥሩ ነው። እዚያ ጋር፡ እግዚአብሔር ይባርካችሁ፡ እህቶቼ፥ ወንድሞቼም፡ እናንተም ደግሞ፡ እጆቻችሁን አንሡ። በጣም ጥሩ።

874 አሁን፡ አባት ሆይ፡ እጃቸውን አይተሃል። (አውቃለሁ፡ ታስብልናለህ፡ "እንግዲያውስ፡ እንደዚህ ያለ ትንሽ ጸሎት? ") እግዚአብሔር ሆይ፡ ስለዚያች፡ ስለ ትላንትናዋ እናት እያሰብኩ ነው፡ "ያ ልጅ ለመሞት ሶስት ሳምንት ብቻ ቀርቶት፡ በዚያ ቀን በቤቷ አነስተኛ ጸሎት አደረግን፡ በአንጎል ውስጥ እብጠት ነበረው፡ አሁን ነገሮች ተቀየሩ።"

875 ሕዝቅያስን፡ ፊቱንም ወደ ግድግዳው ጠግኖ ሲያለቅስ፡ ትዝ ይለኛል፡ "ጌታ ሆይ፡ እባክህ፡ ማረኝ። በፍጹም ልብ በፊትህ ሄጄአለሁና፡ አስበኝ" አለ። ከሞት ወደ ሕይወት ተለወጠለት።

876 በአንዲት የእግዚአብሔር ልጅ አዋጅ፡ "አልዓዛር ሆይ፡ ና!" የሞተውም ሰው ወጣ።

877 አቤቱ አምላክ ሆይ፡ አንተ እንዲህ አልከን፡ "ተናገሩ፡ ጠይቁ፡ እና ይሰጣችኋል። ማንኛውንም ነገር ስትጠይቁ፡ የጠየቃችሁት ነገር እንደተሰጣችሁ እመኑ፡ የምትለምኑት ነገር ታገኛላችሁና።"

878 አሁን፡ አባት ሆይ፡ እጃቸውን ያነሱት ሁሉ እጃቸውን በማንሳት የጠየቁትን እንዲቀበሉ እጸልያለሁ። የተባረኩ ይሁን። እግዚአብሔር ሆይ፡ እህቶቻችንን እንድትረዳቸው እጸልያለሁ፡ እራሳቸውን መግዛት... እንዲኖራቸው እርዳቸው፡ ከሰይጣን ደግሞም በቴሌቭዥን እና **ከእውነተኛ ታሪክ** በስሜታዊ መጽሔቶች፡ እና ልቅ ከሆኑ ነገሮች ሁሉ፡ ሳንሱር ካልተደረጉ ሰርጭቶች፡ ከቆሸሹ ድርጊቶች እና ከቴሌቭዥን ጸያፍ ድርጊቶች እና ሁሉም ነገር፡ ይህም... በሚሊዮን የሚቆጠሩ ነፍሳትን ወደ አንተ ለመማረክ መሳሪያ ሊሆን ይችል ነበር፡ ነገር ግን እነዚህ ነገሮች ሳንሱር ስለማይደረጉ፡ እና እነዚህን ሁሉ ቆሻሻ ነገሮች ይለቃሉ... ኦህ፡ እንዴት ያሳዝናል! የዲያብሎስ መንፈስ በእህቶቻችን ላይ እንደሚሽከረከር እና በመካከላቸው እንደገባ ለማወቅ፡ ፋሽን እንዲከተሉ እና እንዲለብሱ እየገፋፋቸው ነው።

879 እንዲሁም ደግሞ፡ እንደምናየው... በወንድሞቻችንም መካከልም፡ ጌታ ሆይ፡ ማጨስ እና መጠጣት፡ እንዲህ እና እንዲህ እያደረጉ፡ "እምናለሁ" ስላሉ ብቻ ይህ ማድረግ እንደሚችሉ አድርገው ያስባሉ። አቤቱ "ዲያብሎስም እንደሚያምን፡" ይወቁ። "እምናም ይንቀጠቀጣልና፡" ቢሆንም አልዳነም።

880 አሁንም፡ አባት ሆይ፣ ሁላችንን እንድትምረን፡ እና ኃጢአታችንን ይቅር እንድትለን እንጸልያለን፡ ምናልባት አንዳንዶች እጃቸውን አላነሱም፡ አምላክ ሆይ፡ ማራቸው። የሚቀጥለው እድል ሲያገኙ፡ እጆቻቸውን ወደ ላይ ያንሡ።

881 ጌታ ሆይ፡ የጌታን እራት ለመውሰድ ዝግጅት ላይ ነን። ያለፈውን በደላችንን እና ስህተቶቻችንን ይቅር በለን። በክርስቶስ ስም እንለምናለንና፡ በረከትህን እንቀበል። ኣሜን።

882 ጌታ ይባርካችሁ። እንደዚህ ስላቆየኋችሁ ይቅርታ አድርጉልኝ። እንዲህ አሰባለሁ፡ ከጌታ እራት በፊት፡ ሊጸልይለት የመጣ ሰው ካለ፡ ሊጸልይለት የሚፈልግ ካለ፡ እንግዲያውስ፡ ጸሎት የሚፈልግ ካለ፡ አሁን በደስታ እናደርገዋለን።

883 እሺ፡ ወንድሜ፡ ፈጥነህ አምጣት፡ ጥሩ ነው። ለአፍታ ብቻ፡ እና ከዚያ በኋላ—አገልግሎቱን እናስናብታለን። ካስናበትን በኋላ፡ ለጌታ እራት መቆየት የምትፈልጉ ሰዎች፡ መቆየት ትችላላችሁ። አሁን ግን ለታመሙ እንጸልያለን። መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል?

884 ያ ወንድም መነሣት የማይችል ከሆነ... ምንም ችግር የለውም፡ ባለበት ቁጭ አርጉት፡ ወደሱ እንመጣለን። ችግር የለውም፡ ባለበት ይቀመጥ። ወደ እርሱ ወርደን እንጸልይለታለን። ምንም አይደለም። እሺ፡ ጌታዬ፡ እዚያው—ቁጭ አርገው። እዚህ መቆም ከባድ ከሆነበት፡ ታዲያስ፡ እሱ ወዳለበት በደስታ እንወርዳለን።

885 አሁን ይህን ትንሽ ነገር ልጠቅስ እፈልጋለሁ፡ ውድ ወዳጄ። አየህ፡ ጌ—ጌታ ይህን ብዙ ብዙ ጊዜ እንዳረጋገጠው አውቃለሁ። አየህ? እኔ ታላቅ ሰባኪ አይደለሁም፡ ትምህርትም የለኝም ወዘተ። ጌታ ኢየሱስን እወደዋለሁ፡ እንደምወደውም እግዚአብሔር ያውቃል። ነገር ግን የተጠራሁት ለአንድ ነገር ነው፡ እርሱም ለታመሙ ለመጸለይ ነው። ታምናለህ? ስለ ስጦታው ገና ሳላውቅ እንኳን፡ ወደ ሆስፒታል እሄድ ነበር፥ ነርሶቹም "አሁን ትድናለህ፡" ሲሏቸው አስታውሳለሁ። አየህ? እግዚአብሔር በጸጋው ለሰዎች ጸሎቴን ለማክበር ፈቃደኛ የሆነው፡ ይህ አንድ ነገር ነው።

886 እንደውም፡ ዛሬ ማታ፡ በመላው-ዓለም ለሚኖሩ ሁሉ ጥሪ ቢደረግላቸው፡ ብዬ አሰባለሁ። እናም፡ ወንድም ብራንሃም የጸለየላችሁ ሰዎች በሙሉ፡ ወደዚህ ቅረቡና፡ ለዩናይትድ ስቴትስ መንግስት፡ ደብዳቤ ጽፋችሁ መልስ እንድታቀርቡ እፈልጋለሁ ቢባል። ይህ ዓለም-አቀፍ ሰርጭት በሆነ ነበር። ምናልባት አራት ወይም አምስት ሚሊዮን ሰዎች ጥሪው ሰምተው መልስ ይሰጡ ይሆናል፡ ብዬ አሰባለሁ። አያችሁ?

887 እና ከሰዎቹም፡ አንዳንዶቹ ሞተዋል፡ ዶክተሩ፡ እ—እና ቀብር አስፈጻሚው የገነዛቸው ነበሩ። አንዳንዶቹ በአደጋ የሞቱ፥ አንዳንዶቹ በተፈጥሮ ምክንያት የሞቱ ናቸው። አንዳንዶቹ ዓይነ ሰውሮች፡ አንካሶች፡ ሽባዎች፡ ጠማማዎች፡ ታማሚዎች፡ የአእምሮ ሕመምተኞች... በሆስፒታል ውስጥ ሆነው፡ ሆስፒታል ገብተን እንደምንጸልይላቸው እንኳ ያላወቁ ናቸው። ስናስገባቸው፡ ልንወስዳቸው ይገባል። የት እንዳሉ እንኳን ሳያውቁ፡ ሲታገሉ እራሳቸውን ይጎዳሉ፡ ከአምስት ደቂቃዎች በኋላ፡ ቀሪው ሕይወታቸው፡ ዝምተኞች፡ ጣፋጭ፡ አፍቃሪ እና ጤናማ ይሆናሉ። አያችሁ?

888 ይህ... ከማን ነው? ከወንድም ብራንሃም አይደለም። ለታመሙ ሰዎች እንድጸልይ፡ የላከኝ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። እንግዲህ ይሄው ነው። በጄፈርስንቪል ውስጥ ብዙ ስኬት አልነበረኝም፡ ምክንያቱም፡ ይህ ነው። አሁን፣ በዚህ ከተማ ውስጥ አንዳንድ የቅርብ እና የቅርብ ጓደኞቼ እንዳሉኝ እንድታውቁ እፈልጋለሁ። ምንም እንኳን ከተማው ራሱ፡ የከተማው ሁኔታ፡ ባልወደውም። እኔ ይህን ሁኔታ አልወደውም፡ በፍጹም፡ ትንሽ ልጅ ሳለሁ፣ እና የታሪክ መጽሃፎቼን፡ ተቀምጬ እያነበብኩ፡ "አንድ ቀን ከዚህ እሄዳለሁ፡" አልኩኝ። እያችሁ?

889 ጄፈርስንቪልን አልወደውም፡ ረግረጋማ ነው፡ ዝቅተኛ ነው። ከባድ ረግረጋማ ነው፡ እ—እና ጤናማ አይደለም። ወደዚህ ወደ ስፓይከርት ኖብስ አናት ላይ ወይም ሌላ ወጥታችሁ፡ እና ማየት ከፈለጋችሁ፡ ወደ ኒው አልባኒ እና ጀፈርስንቪል ማየት ትችላላችሁ። ተመልከቱ፡ ዶክተሮች እንኳን እንዲህ እያሉ ነው፡ ማለት፡ "በዚህ ሸለቆ ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች በዚህ ሁኔታ የደም ማነስ እየገጠማቸው ነው" ብለዋል።

890 የዚህ አካባቢ ኗሪ፡ ወይዘሮ ሞርጋን፡ ከካንሰር የተፈወሰችው፡ ውሻዋ ማንጃይት እንዳለበት በማሰብ፡ ወደ ክሊኒኩ ወሰደችው። ከምን እንደነበረ ታውቃላችሁ? ከኮልጌት ፋብሪካ በደረሰው ሰፈራ ምክንያት በአረሞቹ በገቡ ነገሮች። እጅግ ንጽህና የጎደለው ቦታ ነው።

891 በሠራዊቱ የነበረ አንድ ሰው፡ ወደዚያ አካባቢ ገብቶ... አስም ይዞታል። እና ዓይኖቹ ጥቁር ሆኑ፡ ወደ ፍሎሪዳ ሄደ እናም ወደ ሐኪም ሄደ፡ ዶክተር ሆይ፡ "አለው... "

892 ዶክተሩ አለው፡ "እሺ፡ ስትጣላ ቆይተሃል፡ አይደል? "

893 "አይ፡ በፍጹም፡ ጌታዬ፡" አለው።

894 ማን እንደሆነ ማወቅ ከፈለጋችሁ፡ ስሙ ሄርቢ ይባላል። አሁን፡ ምናልባት ትዝ ካለኝ... በኒው አልባኒ ውስጥ፡ የ—የዩኒየን ብሔራዊ ባንክ ሰራተኛ ነው፡ ቴለር ነው። ወደዚያ ሄዳችሁ "ሄርቢ" የሚለውን አይታችሁ፡ ጠይቁት።

895 እርሱም... ሄዶ፡ እንዲህ አለ፡ "ዶክተር፡" "የሳይነስ በሽታ አለብኝ፡" አለው።

896 እሱም መርምሮ፡ "እውነት ነው፡" አለው። እሱም "የተጣላህ መስሎኝ ነበር፡" አለው። እሱም "የት ነው የምትኖረው፡ ልጄ፡" አለው?

897 እርሱም "ቦታውን ላታውቀው ትችላለህ፡" አለው፡ "የምኖረው ከሉዊስቪል፡ ኬንታኪ ማዶ በምትገኝ ትንሽ ከተማ ውስጥ ነው፡ ኒው አልባኒ፡ ኢንዲያና፡" ትባላለች።

898 እርሱም፦ "በዚህ በማያሚ ጉዞህ ውስጥ፡ ከዚህ የጨው ውሃ የሳይነስ በሽታ አመመኝ እያለከኝ ነውን? " አክሎም፡ "በጄፈርስንቪል፡ ኢንዲያና፡ ወይም ኒው አልባኒ፡ ኢንዲያና ውስጥ መኖር ከቻልክ፡ የዩናይትድ ስቴትስ ጦር በላከልህ በየትኛውም የዓለም ክፍል መኖር ትችላለህ።" ይኼው ነው። እያችሁ?

899 ይህ ቦታ እኔ እስከማውቀው ድረስ፡ በወባ ከተጠቁ ረግረጋማ አካባቢዎች ውጪ፡ በአለም ላይ ካሉት እጅግ በጣም ንጽህና የጎደለው ቦታ ነው። አያችሁ? እና እ—እ—እ—እዚህ ጋር ጓደኞች አሉኝ።

900 ይኸውላችሁ፡ በደንብ ልጠቅሳቸው እችላለሁ። ጓደኛዬ፡ ዶክተር ሳም አዲር። እና፡ እዚያ የተቀመጠው፡ ማይክ ኢጋን። ኦህ፡ ማይ፡ ስንት ብዬ ልጥራ! በመቶዎች የሚቆጠሩ እውነተኛ ጥሩ ጓደኞች፡ የድሮ ጓደኞቼ፡ አብረን ተጫውተናል... ምንም ያህል አዲስ ጓደኞች ባገኝ፡ የድሮ ጓደኛን የሚተካ ምንም ነገር የለም። ታውቃላችሁ።

901 አሮጊትዋ እናቴም ከኋላ ተቀምጣለች፡ አሁን በሰልሳዎቹ ውስጥ ነች፡ በምድር ላይ ብዙም ጊዜ የላትም። የባለቤቴ እናትም፡ ሰባ፡ አሁን ወደ ሰባ-አንድ እየሄደች ነው፥ ይመስለኛል፡ ዛሬ ማታ፡ እዚህ ከኋላ አካባቢ ተቀምጣለች። እናም፡ እዚሁ የተውኳት። አባቴ እዚህ ተቀበረ፥ ሚስቴም ዋልኑት ሪጅ ላይ እዚህ ተቀበረች፡ ልጄም እዚያ ተኝታለች። ምን ለማለት እንደፈለግኩ አያችሁ?

902 እ—እ—አልወደውም... እዚህ መኖር እ—እ—እ—አልፈልግም፡ በቅርቡም ወዲያውኑ፡ ለቅቄ መሄድ እንዳለብኝ፡ አምናለሁ። አያችሁ፡ ደጋግሞ ይመጣብኛልና፡ እኔም በዚህ ፑልቢት እና በመጽሀፍ ቅዱሴ፡ በተደጋጋሚ ተናግሬአለሁ።

903 ለሚስቴ ስነግራት፡ ያኔ ለዚህች ቤተ ክርስቲያን የሰጠሁትን ይህንን የአገልጋይ መኖሪያ እንድንሠራ ገንዘቡን በተሰጠን ጊዜ... መኖሪያው ባለቤትነቱ የቤተክርቲያን ነውና፡ ካልሆነ፡ ሂዱና መርምሩ። አያችሁ፡ ለራሴ እንዲሆን አላደረግኩትምና።

904 አሁን፡ እኔ እዛ ልገነባ ስሄድ፡ ሜዳ "በእናቴ ምክንያት እዚህ መቆየት እፈልጋለሁ፡" አለችኝ።

905 እኔም፡ "የኔ ማር፡ በጣም እዝናለሁ፡ ቢሆንም የማይሆን ነገር ነው። እየሽ፡ በጭራሽ አይሰራም። እግዚአብሔር 'ተለዩ፡' ብሎናል፡ መለየት አለብኝ።"

906 እንደገናም አለች፡ "ግን'ኮ፡ እናቴ!"

907 እኔም፡ "እናቴም፡ እንዲሁ። 'ይሁን እንጂ የራሱ የሆነውን ነገር የማይተው፡ ከኋላየም የማይከተለኝ፡ የእኔ ሊሆን አይገባውም።' ይህም እውነት ነው።"

908 አንድ ቀን፡ ብዙም ሳይቆይ፡ መንቀሳቀስ እንዳለብኝ ይሰማኛል፡ ማለትም፡ ለመሄድ። ምክንያቱ እዚህ ያሉት ሰብሰባዎች፡ ብዙም ውጤታማ አይደሉም። በሁሉም ቦታ እንደሚገኙ ስኬት የላቸውም፡ እና በሰብሰባ ላይ ያለ ማንኛውም ሰው ያ እውነት መሆኑን ያውቃል፡ ምክንያቱም ይህ የእኔ ከተማ ስለሆነ ነው። ይኸው።

909 ኢየሱስ ሲመጣም ተመሳሳይ ነገር ተናግሯል።

910 እነርሱም፡ "ይህ ሰው ማን ነው? የአናጺው ልጅ እዚህ አይደለምን? በየትኛው ትምህርት ቤት ተማረ? ይህ እውቀት ከየት አገኘው? እንዲህ ስታደርግ ማየት እፈልጋለሁ... በዚህ ቦታ ተአምራትን ስርቻለሁ ብለሃልና፡ እዚህም ተመሳሳይ ነገር ስታደርግ ማየት እንፈልጋለሁ። በቅፍርናሆም ያደረግከው፡ እዚህ ስታደርግ ማየት እፈልጋለሁ።"

911 ኢየሱስም... "ባለማመናቸው ተደነቀ።" ዘወር ብሎ፡ "እውነት፡ እውነት፡ እላችኋለሁ፡ ነብይ በራሱ አገር ውስጥ ከህዝቡ መካከል በቀር ሳይከበር አይቀርም።" ልክ ነው?

912 ደግሞ እንደምናውቀው... እነ... ፊነይን፡ ሳንኬይ፡ እና እነ ሙዲን፡ እነ ጆን ዌስሊን ውስዱ፡ አገራቸውን ለቀው እስኪወጡ ድረስ፡ አያችሁ፡ መዝለቅ አልቻሉም ነበር። ሙዲን እዩት—ተ—ተ—ተመልከቱት። የቦስተን የጫማ ስሪ የነበረው፡ ሙዲ፡ ምንም መሄድ ሳይችል ሲቀር፡ ታዋቂ ከመሆኑ በፊት ወደ ቺካጎ መጣ። አያችሁ? ከራሱ ሁሉ መራቅ ነበረበት። እናንተም ሁሌ እንዲህ ማድረግ አለባችሁ።

913 አሁን ግን፡ እዚህ ጋር፡ ዊልያም ብራንሃምን ዞር ካደረጋችሁት እግዚአብሔር ጸሎታችሁን ይሰማል (ገባችሁ?)፡ ዊልያም ብራንሃም ከዚህ ጋር የሚያገናኘው ነገር እንደሌለ፡ ሰለ እናንተ ለመጸለይ የሚቆም መሆኑን ብቻ ከገባችሁ። የለመናችሁትን ሁሉ ያደረገላችሁ፡ የፈጸመው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። አያችሁ? እንጂ ከኔ ጋር ምንም ግንኙነት የለውም... እኔ ከእሱ ጋር ምንም ግንኙነት የለኝም፡ ሰለ እሱ ከመመስከር በስተቀር። ነገር ግን እዚህ ከእናንተ ጋር በማደጌ ምክንያት፡ ድክመቶቼንና፡ ስህተቶቼን ሁሉ የምታውቁ... እግዚአብሔርም በዚህች ከተማ ያደረገውን; ታውቃላችሁ።

914 ይህች ከተማ; በፍርድ ቀን፡ አንድ ቀን ታላቅ ዋጋ ትከፍላለች፡ ምክንያቱም በመቶዎች እና በመቶዎች የሚቆጠሩ አስደናቂ ፈውሶች እዚህ ሰለተደረጉ (በትክክል።)፡ እዚሁ ተደርገዋልና። ተአምራትና ድንቆች፡ የመልአኩም መገለጥ በዚህ ታይቷል፡ ጋዜጦች እና ሌሎች ነገሮች ሁሉ ቢያስተጋቡም፡ ህዝቡ እስካሁን ድረስ ኮሽ አላለውም... ለምንድነው?

915 ስለዚህ አንድ ቀን፡ ከዚህ እርቃለሁ። እኔም እደነቃለሁ፥ "ወደፊት ምን እሆናለሁ? አልቆ ይሆን? ወይስ ገና ነውን? አርባ-ሰምንት ዓመቴ ነው። ሁሉንም ነገር አልቆ ይሆን? " ይህ ይገርመኛል። ከሆነም...

916 ይኸውላችሁ፡ ዓለም ይሄንን ሰዕል ለምን ሊያስተውል አልቻለም? ለምን ፈጥነው አልተረዱትም? ለምን እነዚህን ሌሎች ነገሮች አይረዱም? ለምን እነዚህን ትንቢቶች እና ነገሮች አይረዱትም? ይኸውላችሁ፡ አሁን አገነዘቡትም፡ አንድ ቀን ግን ዓለሙን ትቼ እሄዳለሁ፡ እኔ ሰሄድም፡ ያኔ ያውቁታል። አንዳንዶቻችሁ ወጣቶች እኔ ከሄድኩ በኋላ ያንን ትገነዘባላችሁ። አያችሁ? እግዚአብሔር ግን አሁን እንዲሆን አልፈቀደም። ምን እንደሆነ አያችሁ... ምን ማለቴ እንደሆነ ገብቷችኋል። [በቴፕ ላይ ባዶ ቦታ—እርታዒ።]

917 ... የህጻን ልጅ የእጅ አምባር የጠፋበት። አንድ ሰው ካለ ይውሰድ። ወንድም ሶትማን ባለፈው እዚህ በነበረ ጊዜ መጽሐፍ ቅዱስ ረስቶ እንደሄደ ተናግሯል፡ ይመስለኛል። መጽሐፍ ቅዱስ ያገኘ ሰው አለ፡ የ—የጠፋ መጽሀፍ ቅዱስ ያገኘ ካለ? ያገኘ ካለ፡ የካናዳዊው ወንድማችን የወንድም ፍሬድ ሶትማን ነው። አሁን እንጸልይ።

918 ጌታ ሆይ፡ ማረን፡ ሙዚቃው በለስላሳ ሲጫወት እና ወንድም ኔቪል በዘይት እየቀባ፡ እኔ በኢየሱስ ሰም በሽተኛ ላይ እጄን ለመጫን እመጣለሁ። ጌታ ሆይ፡ ፈውሳቸውን፡ ሰጣቸው። ኣሜን።

919 ሁላችሁም ጸልዩ፡ አሁን፡ ሁሉም ሰው። ጥሩ።

ጌታ ሆይ፡ ይህ ብላቴና፡ አያቱ ለእሱ እዚህ ቆመዋል። ለወተት፡ ለማንኛውም ዓይነት ወተት አለርጂ ነው። አንተ ግን ሙሉ ኃይል አለህ ህጻናትም የራሳቸው እምነት ሊኖራቸው አይችልም። ስለዚህ፡ ጌታ ሆይ፡ ከወላጆቹና ከአያቶቹ ጋር በመሆን፡ እምነቴን ለእርሱ አደርጋለሁ፡ እናም ይህ ሕፃን ወተት ጠጥቶ ለእግዚአብሔር ክብር እንዲኖር፡ በኢየሱስ ስም እናውጃለን። ኣሜን። እንደዚያ ይሆናል።

አምላኬ፡ ሆይ፡ ስለ አባቷ ትጸልያለች። አባቷን እንድትፈውስ እና የሚፈልገውን እንድትሰጠው፡ በክርስቶስ ስም አብሬያት እጸልያለሁ። ኣሜን።

920 ይኸው፡ ቀላል ነው አይደል? ሰዎች ይጸልያሉ፡ ይሁን እንጂ ነገራቸው ሁሉ... ታላላቅ ነገር በማስመሰል ውስብስብ ያደርጉታል። እግዚአብሔር ቀላል ያደርገዋል። እናንተ ውስብስብ በማድረግ ትስታላችሁ። አያችሁ? ልክ... ልክ እንደ እግዚአብሄር ቀላል ይሁንላችሁ እርሱም፦ “ያመኑትን እነዚህ ምልክቶች ይከተሉአቸዋል፥ እጃቸውን በድውዮች ላይ ቢጭኑ፡ ይድናሉ፡” እግዚአብሔር እንዳለው።

921 በዚህች ሴት ላይ እጃችንን እንዘረጋለን፡ ጌታ ሆይ፡ እዚህ ቆማለች እህታችን፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እንለምናለንና፡ ትፈወስ። ኣሜን።

922 አባት ሆይ፡ በእህታችን ላይ እጃችንን ስንጭን፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ መጽሐፍ ቅዱስን እና የጌታን ትምህርት ማስታወሻነት፡ ትፈወስ።

አባት ሆይ፡ በክርስቶስ ስም፡ የእህታችንን ፈውስ እንለምናለን፡ ቃልህን ስንታዘዝ ጤነኛ እንድታደርጋት እጸልያለሁ፡ ምን ልትሆን እንደምትችል ምንም ጥርጥር የለኝም... ? ... አሜን።

923 አባት ሆይ፡ በእህታችን ላይ እጃችንን እንዘረጋለን፣ እናም እንድትፈውሳት፡ እና ጤነኛ እንድታደርጋት፡ በጌታ በኢየሱስ ስም እንጠይቃለን። አሜን።

በጌታ በኢየሱስ ስም በወንድማችን ላይ እጃችንን እንጭናለን፡ እና ለእግዚአብሔር ክብር እንድትፈውሰው እንለምንሃለን።

አባት ሆይ፡ በጌታ በኢየሱስ ስም፡ እህታችንን ቀባን፡ እጃችንንም በላይዋ ጭነን በኢየሱስ ስም እንድትፈወስ እንለምናለን።

እግዚአብሔር አባታችን ሆይ፡ በወንድማችን ላይ፡ እጆችን እንጭናለን፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ አንተ ጤነኛ ታደርገው ዘንድ ቀባነው።

አባት ሆይ፡ ይህች፡ የተወደደች ሚስቱ... ? ... ቀባናት እጃችንንም ጫንንባት፡ አንተን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ እንለምናለን።

924 ጌታ እግዚአብሔር ሆይ፡ እጆቻችንን በእሷ ላይ በመጫን፡ ህጻን ኢዲትን ቀባናት፡ እናም ልመናዋን እንድትፈጽም በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እንለምንሃለን።

አባት ሆይ፡ እናቷንም ቀባን፡ እና እጃችንን ጫንባት ፈውሷንም እንለምናለን፡ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ ትፈወስ።

925 አባት ሆይ፡ የዚህን ቤተሰብ ውድ የሆነች ትንሽ ጌጥ፡ ትንሽ የልብ ምት፡ በጌታ በኢየሱስ ስም ቀባናት፡ ከዚህ በፊት በፊቱ አደራ ተሰጥታለች፡ አንተም ትፈውሳት ዘንድ እለምንሃለሁ... ? ...

926 አምላክ ሆይ፡ የእህታችንን ልመና አንተ ታውቃለህ እና ስለ መልካም እምነቷ እናመሰግናለን። እንግዲህ፡ እነዚህ የጠየቀቻቸው ነገሮች ይህ... ? ... ህጻን ሳለች የተጫወተችባቸው ነገሮች፡ አምላኬ ሆይ፡ ጠላት እጁን ያንሳ፡ ጌታ ሆይ ወደ ቤቷም ትግባ። እኛም እንደ ቃል ኪዳንህ፡ ለዚህ ሰው፡ የለመነችውን፡ እንጸልያለን፡ "ማንኛውንም ነገር በስሜ ብትለምኑ፡ አደርገዋለሁ።" ይህን ልመና እንድትሰጠን፡ በኢየሱስ ስም እጸልያለሁ። ኣሜን። እግዚአብሀር ይባርክህ።

927 ጌታ ሆይ፡ ይህ የፊት ነርቭ ከወንድሜ ግንባር ላይ ሲሞት፡ ህይወት እንደገና እንዲወለድ እንለምናለን፡ ምክንያቱም ይህ ነርቭ እንዲፈወስ፡ በኢየሱስ ስም በመጠየቅ፡ በእርሱ ላይ እጃችንን ጫንን።

እግዚአብሔር አባታችን ሆይ፡ እህታችንን በዘይት ከቀባናት በኋላ እጃችንን ጫንን፡ አንተም በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እንድትፈውሳት፡ እንለምናለን። ኣሜን።

928 የሰማይ አባት ሆይ፡ እህታችን አንተ ባመጣሃቸው ብዙ ስኬቶች እዚህ እንደቆመች፡ እዚህ ከአገልጋዮችህ፡ ለአንዱ ሰባኪ በጣም ቆማለታለች፡ ጭንቀት ይዞታልና፥ በልባችን ውስጥ ለእርሱ ብዙ አዘኔታ ይሰማናል። አምላኬ ሆይ፡ በዚህ ስለቆመችለት እህታችንን እና ፈውሱን እንዲቀበል እንድትቀባው፡ እለምንሃለሁ። በክርስቶስ ስም፡ እጸልያለሁ። አሜን... ? ... ጌታ ያውቃል... ? ...

929 መልካም። እጅግ ደስ ብሎኛል። በእውነት የጌታ ቅባት ነው። ጌታ እግዚአብሔር ሆይ፡ ይህች ሴት ለዓመታት ሲዋጋት ከነበረው ጋኔን ተገላግላለች፡ አንድ ቀን ወደዚያ ቤት እንድትመጣ አደረግሃት፡ ከዚያም "**የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል**" የሚል መንፈስ ወረደ፡ ካለቀሰች በኋላ፡ በመሠዊያው ላይ ተኛች፡ ማድረግ የምትችለውን ሁሉ አደረገች፡ ይሁን እንጂ የ**ሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል** አስፈለገ። አሁንም፡ በቱከት ስለታመመው የእህቷ ልጅ መጥታለች፥ አንድ አመት አልፎታል፡ መራመድ ግን አልቻለም። ጌታ ሆይ፡ የእግዚአብሔርን በረከቶች እንድትሰጣት በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እንድትሰጣት፡ እጸልያለሁ። ስለዚያች እህትም፡ እጅግ ደስ ብሎኛል፡ እሷም፡ ልዩ ሆናለች። አሁን ከሞት እጅግ ርቀሻል፡ አይደለም እንዴ?

እግዚአብሔር አባት ሆይ፡ እህታችንን እንደቀባናት እንድትባርካት እንፀልያለን እጃችንን በመጫን አንተ ባልከን መሰረት ለመንን፡ "ያመኑትን እነዚህ ምልክቶች ይከተሉአቸዋል። እጃቸውን በድውዮች ላይ ይጭናሉ፡ ይድናሉ።" አማኞች መሆናችንን እንመሰክራለን፡ ጌታ ሆይ፡ ስለዚህ አንድ ነገር እንድታደርግ፡ በኢየሱስ ስም እንጸልያለን... ? ...

930 እግዚአብሔር አባታችን ሆይ፡ የዚችን ታናሽ ሴት ልብ ስለምናውቅ፡ እንዳጫወተችንም፡ አንተ እንድትምራት እና የጠየቀችውን እንድትፈጽምላት እንጸልያለን። አቤቱ አባታችን፡ ለቤተሰቦቿ፡ ለልጆቹ በተለይም ለልጁ፡ አቤቱ እነዚህን ነገሮች እንድትሰጥ፡ አሁን እጸልያለሁ፡ እግዚአብሔር ሆይ፡ እነዚህን ነገሮች እንድትሰጥ አሁን እጸልያለሁ... ? ... በሙሉ ልቤ፡ በኢየሱስ ስም፡ እጠይቃለሁ። ኣሜን።

እግዚአብሔር አባታችን ሆይ፡ ይህችን ሴት በዘይት ቀባናት፡ በጌታ በኢየሱስ ስም፡ እንድትፈውሳት እና ለእግዚአብሔር ክብር እንድትመልሰላት ጸለይን።

931 ስምሽ ምዕራብ ሊሆን አይችልም፡ አይደል?

አባት ሆይ፡ ለዚች ወጣት ሴት እንጸልያለን። ስለ አባቷ ጠይቃለችና። አሁንም፡ አባቷን እንድትሰጣት፡ ልቡን ንካው፡ ጌታ እንድትሰጣት እጸልያለሁ። እንዲድን ትፈልገዋለችና። አሁን ባለበት በኡኣለም ነገር እንዲቀር አትፈልግምና፡ ይህችም፡ የገዛ ልጁ፡ ዘሩ ናት። አባት ሆይ፡ በክርስቶስ ስም፡ እንድትምርላት፡ እጸልያለሁ።

932 እግዚአብሔር ይባርክሽ፡ ልጄ ሆይ፡ የጠየቅሽውን ይስጥሽ።

አምላክ ሆይ፡ ምህረትህን በእሷ ላይ እንለምናለን፡ እሷን በዘይት ሰንቀባት፡ ምህረትን እንድታደርግ እንለምንሃለን... ? ...

57-1006 ጥያቄ እና መልስ በዕብራውያን ላይ ክፍል III
ብራንሃም ተበርናክል
ጀፈርሰንቪል, ኢንዲያና ዩ.ኤስ.ኤ

AMHARIC

©2024 VGR, ALL RIGHTS RESERVED

Voice Of God Recordings
P.O. Box 950, Jeffersonville, Indiana 47131 U.S.A.
www.branham.org

## የቅጂ መብት ማሳሰብያ

ይህ መጽሐፍ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ይሰፋ ዘንድ፣ በቤት ለግል ጠቀሜታም ሆነ ለሌሎች ሰዎች ያለ ክፍያ ለማበርከት፣ በቤት ማተሚያን መጠቀም ይቻላል። ይህ መጽሐፍ ያለ ቮይስ ኦፍ ጋድ ሪከርዲንግስ በጽሑፍ የተደገፈ ህጋዊ ፈቃድ መሸጥም ሆነ፣ አብዝቶ ማተም፣ በዌብ ሳይት ላይ ማስቀመጥ፣ በማከማቻ ዘዴዎች ላይ ማስቀመጥ፣ ወደ ሌሎች ቋንቋዎች መተርጎምም ሆነ የድጋፍ ማሰባሰቢያ አድርጎ መጠቀም የተከለከለ ነው። ህጋዊ መብቱም ሁሉ የተጠበቀ ነው®።

ለተጨማሪ መረጃ ወይም ተጨማሪ ግብዓቶች ቢፈልጉ፣ እባኮትን ይህ አድራሻ ይጠቀሙ፡

Voice Of God Recordings

P.O. Box 950, Jeffersonville, Indiana 47131 U.S.A.

www.branham.org